ቅፅ 23 ቁጥር 107 ሚያዝያ 2016

# ዘመን



## ኢትዮጵያ በቀይ ባህር

### አካባቢ ጦሯን ብታሰፍር በአካባቢው አስተማማኝ ሰላም ይሰፍናል

- ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ
ፓርቲ ሊቀመንበር



**የወደብ ጉዳይ እና ኢትዮጵያ**

ፈውስ ፈላጊው የትምህርቱ ዘርፍ

የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ በ«**አሰብ የማን ናት?**›› መጽሐፍ




# በውስጥ ገጾች


1 ኢትዮጵያ በቀይ ባህር አካባቢ ጦሯን ብታሰፍር በአካባቢው አስተማማኝ ሰላም ይሰፍናል
- ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር

10 የወደብ ጉዳይ እና ኢትዮጵያ

18 ፈውስ ፈላጊው የትምህርቱ ዘርፍ

26 የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ በ‹‹አሰብ የማን ናት?›› መጽሐፍ

32 ግብረ ሰዶም - የትውልድ ጠንቅ የዘመን ፈተና

39 ብርሃን

41 በፈተና የአልተበገሩ ወርቃማ እግሮች!



# ርዕሰ አንቀጽ

# ልበ ሰፊነት ያስፈልጋል!

አገራዊ የምክክር መድረክ ግጭቶችን የመፍቻ ቁልፍ መሣሪያ በመሆኑ ለስኬታማነቱ የየበኩላችንን በጎ አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅብናል። አገራዊ ምክክሩ ላይ ኅብረተሰቡን ይወክላሉ ተብለው የሚታሰቡ የተወሰኑ አካላት የሚሳተፉ ቢሆንም፣ ሕዝቡ የአገሩን ጉዳይ የእነዚህ ሰዎች ብቻ ጉዳይ ሳያደርግ በየመሥሪያ ቤቱና መሰብሰብ በቻለባቸው ቦታዎች ሁሉ የተለየ የፖለቲካ አመለካከትና ሐሳብ አላቸው ከሚላቸው ሰዎች ጋር እየተቀራረበ፣ ቁጭ ብሎ መነጋገርና መደማመጥ መቻል አለበት። የማዳመጥ ባህልን ማዳበር ከሕዝቡ የሚጠበቅ መሠረታዊ ነገር ነው፤ ቁጭ ብለን በረጋና በቀና መንፈስ የመነጋገርን ልምድ በአዳበርንበት ሁኔታ፤ ሌሎች ሰዎች መክረው፣ የሆነ ውጤት ይዘው ቢመጡም ውጤቱን ለመቀበል ዝግጁ መሆን አንችልም። ስለሆነም ሁላችንም ለምክክሩ ስኬት ልባችንን ዝግጁ ማድረግ ይኖርብናል።

ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የመንግሥትን ዝግጁነትና በተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችም ዘንድ እየታየ ያለው ድጋፍ ተስፋ ሰጪ ነው። እነዚህ ነገሮች በዚህ መልኩ ቢስተካከሉ የምንላቸውና መንግሥትን የምንተችባቸው ነገሮች ቢኖሩም፣ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽንን ገለልተኛ በሆነ አካል ማቋቋሙ፣ የኮሚሽኑን ኮሚሽነሮችም "በእነዚህ መመዘኛዎች መሠረት ጠቁሙ" ብሎ ለህዝቡ እድል መስጠቱና ኮሚሽነሮችን የመሰየምና ሌሎች በርካታ ሥራዎችን ከሥራ አስፈጻሚው ወደ ሕግ አውጪው ሐላፊነቱን ማሻገሩ በጣም አበረታችና ዋጋ ልንሰጠው የሚገባ ነው። አሁን ያለው መንግሥት ቀደምት መንግሥታት እንደአደረጉት፣ የጨዋታውን ሕግ እኔ ጽፌዋለሁ፤ ይህን የምትከተል ከሆነ "ተከተል" የማትከተል "ሒሳብህን ታገኛለህ" ሳይል፣ ሐላፊነት በተሞላው መንገድ ለአገራዊ ምክክር መደላድል መፍጠሩን ቀላል ነገር አድርገን ልንቆጥረው አይገባም።

በመንግሥት በኩል አገራዊ ምክክርን ለማካሄድ እጁን መዘርጋቱ፤ ቅድመ ዝግጅቶችንም እያካሄደ መሆኑ ለምክክሩ ስኬታማነት ያለውን ፍላጎት ያሳያል። ከዚህ ቀደም የነበሩንን የውይይት ዕድሎችና የተዘረጉ የሰላም እጆችን በይሁንታ አለመቀበላችን ለበርካታ ችግሮች ዳርጎናል። መንግሥት አገራዊ ምክክር እንዲደረግ መሥመሩን ሲዘረጋ፣ "እንመካከር፤ መፍትሔ እናምጣ" በሚልበት ጊዜ፣ የተዘረጉ የሰላም እጆች እንዳይታጠፉ ሰላም የሚፈልግ ሁሉ ተባባሪ መሆን አለበት።

ለምክክሩ ስኬታማነት ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል። የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ ሌሎች የምክክሩ ተሳታፊዎች የሌላውን ፓርቲ አመለካከት ያለ ምንም ብያኔ ቁጭ ብለው በማዳመጥ፣ ለሕዝቡ ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በምክክሩ የተለያዩ አመለካከቶች ወደ ጠረጴዛ መምጣታቸው ስለማይቀር የምንሰማቸው ነገሮች የሚቆረቁሩ የጫማ ውስጥ ጠጠር ሊሆኑ ይችላሉና ልበ ሰፊነት ያስፈልጋል። "ፖለቲካ" የተለያዩ አመለካከቶች ወደ ጠረጴዛ መጥተው የተሻለውን መቀበል በመሆኑ፣ ፖለቲከኞቻችን ሰጥቶ መቀበልን መልመድ አለባቸው።


በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየታተመ የሚወጣ

ኢፕድ

ዋና አዘጋጅ፡- ዐሥራት ከበደ
ፖ.ሳ.ቁ፡- 30145
ስልክ፡- 011-1264207
zemenpress@gmail.com


ማስታወቂያና ደንበኞች አገልግሎት
ስልክ፡- 011 1 56 98 73
ፋክስ፡- 011 1 57 44 40

አዘጋጆች፡- ወንድወሰን ሽመልሰ
እስማኤል አረቦ
አስቴር ኤልያስ
ግርማ መንግሥቴ
መልካምሥራ አፈወርቅ
ቦጋለ አበበ
ዘላለም ተሾመ

ግራፊክስ ዲዛይን
መስከረም እሸቱ

ፎቶግራፍ፡-

ማከፋፈያ፡-
ስልክ፡- 011 1 57 02 70



## የግብጽ

ጫጫታ የተለመደ በመሆኑ ኢትዮጵያ ሥራዋን እንዳትሠራ የሚያግዳት አይደለም

## የባሕር በር

ለማግኘት ሌላ 30 ዓመት መጠበቅ የለብንም

ሥልጣን ላይ ማንም ይኑር ማን የኢትዮጵያን የባሕር በር የማግኘት ጥረት መቃወም ከጤነኛ ሰው የሚጠበቅ አይደለም

**ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ይናገራሉ፡-**

# ኢትዮጵያ በቀይ ባህር አካባቢ ጦሯን ብታሰፍር በአካባቢው አስተማማኝ ሰላም ይሰፍናል

- ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
  የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር

**አስቴር ኤልያስ**

ኢትዮጵያ 120 ሚሊዮን ሕዝብ ይዛ ያለ ባሕር በር መቀጠል ፈተናዋን የማብዛት ያህል የሚቆጠር ነው። በመሆኑም በርቀትም ሆነ በቅርበት ካሉ ጎረቤት ሀገራት ጋር በመሆን ልማትን የምታመጣበትን መንገድ ማረጋገጥ የግድ ነው። ከዚህ አኳያ ዛሬም የባሕር በርን ማግኘት ለኢትዮጵያ የሕልውና ጉዳይ ስለመሆኑ ከሰሞኑ ከሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገልጸዋል።

ትናንት ላይነሳ ተቀብሮ የተረሳ የመሰለው የባሕር በር ጉዳይ ዛሬ ከተቀበረበት ወጥቶ የሚመለከታቸው አካላትና የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲነጋገርበት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ጥሪ መሠረት ጉዳዩ የብዙዎች መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱ ይታወቃል። ከንግግር እና ከውይይት አልፎም ኢትዮጵያ ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደስምምነት እንድትመጣ ተደርጓል።

ዘመን መጽሔትም በዚህ ወር እትሟ ከዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ጋር አያይዛ የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር እና የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን አነጋግራለች። ፕሮፌሰር በየነ፣ ከዛሬ 23 ዓመት በፊት ከዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በዚሁ መጽሔት ላይ "የአሰብ ወደብ ሕጋዊ ባለቤትነት ጥያቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ነው" ሲሉ አስተያየታቸውን ማጋራታቸው ይታወሳል። በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ከዓመት በኋላም በመጽሔቱ "የኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤትነት መብት ለድርድር እንዳይቀርብ ታፍኗል" ሲሉም ተናግረዋል። ዘመን መጽሔት ከእኚህ ጉምቱ እና አንጋፋ ፖለቲከኛ ጋር ያደረገችውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል። መልካም ንባብ።

ፎቶ ሔዱሽ አብርሃ



> ጠቅላይ ሚኒስትሩ የባሕር በር ሊኖረን ይገባል የሚ ለውን ጉዳይ በማንሳት ጥረት ማድረጋቸው አግባብነት ያለው ጉዳይ ነው።

**ዘመን፡- ከዛሬ 23 ዓመት በፊት በዚሁ መጽሔት ላይ ከባሕር በር ጋር በተያያዘ የተናገሩት ነጥብ ነበር፤ በወቅቱ ስለወደብ ሲነሳ "የኤርትራን ሉዓላዊነት መጋፋት ነው" የሚል አካል እንዳለ ሁሉ፤ ዛሬም የሱማሊያን ሉዓላዊነት መጋፋት ነው ያሉ አካላት አሉ፤ እርስዎ ካለፈው ሀሳብዎ ጋር ዛሬ ላይ ያለውን ሲያነጻጽሩት እንዴት ያዛምዱታል?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** አሰብን በሚመለከት ወይም ደግሞ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ላይ የባሕር በር እንዲኖራት የማድረጉን ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝም ብሎ እንደ ቀላል የሚተወው ጉዳይ አይደለም። ከዛሬ 23 ዓመት በፊትም ያልኩት ነገር ቢኖር ይኸው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ባለጉዳይ ሆኖ እንዳይነጋገርና መላ እንዳይፈልግ በወቅቱ የነበረውና የበላይነትን የያዘው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት አፍኖት ያስቀረው ነገር ነው። ይህን አባባሌን ዛሬም የምደግመው ጉዳይ ነው። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በእኔ እምነትም ሆነ የዓለም አቀፍ ተሞክሮ የሚያሳየው እውነታ ቢኖር የባሕር በር የማግኘት መብት እንዳለው ነው። መብት አለው ሲባል በጉልበት የሚደረግ ነገር እንዳልሆነ ግን ልብ ይሏል።

በእኔ እምነት የኤርትራ መንግሥትም ቢሆን አሰብንም ሆነ ምፅዋን ከኢትዮጵያ ጋር በሰላምና በጋራ መጠቀም ፋይዳው ብዙ መሆኑን ተገንዝቦ የመፍትሔው አካል መሆን አለበት። የመፍትሔ አካል ቢሆኑ የሚጠቀሙበት እንጂ የሚጎዱበት ነገር የለም። ምክንያቱም ኤርትራውያንን ስናስተውል ልክ የሀገራቸው ያህል ወደኢትዮጵያ ሲጎርፉ ነው የምናየው። የኤርትራ ሕዝብ ሲቸገር ከየትኛውም ሀገር ይልቅ መርጦ ተንደርድሮ የሚመጣው እዚህ ወደ ኢትዮጵያ ነው። ይህ ተፈጥሯዊ ሂደት ነው። ኢትዮጵያ ለኤርትራውያን ሁለተኛ ቤት ያህል መርጠው የሚመጡባት ሀገር ናት።

ይህንን መልካም የሆነ መንፈስ፣ ሥልጣን ላይ ያለ አካል በድሎት መኖር የለበትም፤ ልክ ሥጋ ከሥጋው መለየት እንደማይሆንለት በማሰብ ለመለየት የሚደረግ ጥረት ባይኖር መልካም ነው። ተፈጥሯዊው ሁኔታ ነውና ኢትዮጵያ የባሕር በር ኖሯት ኢኮኖሚዋ አድጎ እና ከራሷ ተርፋ የኤርትራም ሕዝብ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ መፈጠር አለበት የሚል አቋም አለኝ።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተደረገው ሁኔታ ሰው ሠራሽ ነው እንጂ ተፈጥሯዊ አይደለም። ኤርትራ በራሷ ለብቻዋ መልማት ቢያቅታት ኢትዮጵያ በተሻለ ሁኔታ ላይ ናትና የኢኮኖሚ ብቃት ስላላት ማልማት ትችላለች። ለመሆኑ አሰብን ማን ነው ያለማው? በምሥራቅ አፍሪካ ታዋቂ የሆነ የቤንዚን ማጣሪያ ፋብሪካ ያቋቋመውስ ማን ነው? የኢትዮጵያ መንግሥት ነበር። የነዳጅ ማጣሪያው በወቅቱ በምሥራቅ አፍሪካ የታወቀ ነበር። ኢትዮጵያን የሚያክል ትልቅ ሀገር የነዳጅ ፍጆታንም የሸፈነ ነበር። በወቅቱ የኤርትራንም የነዳጅ ፍላጎት እየሸፈነ የኖረ ነው። በዚያን ጊዜ ሌላ ማጣሪያ ኤርትራ ውስጥ ስለመኖሩ የማወቀው ነገር የለም።

**ዘመን፡- እንደ ኢትዮጵያ ላለ ትልቅ አገር የባሕር በር ማጣት የሚያደርሰው ጉዳት ምንድን ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** ይህ በጣም ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው። የባሕር በር በመታጣቱ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ደርሷል። ከዚህ በኋላም ጉዳቱ እየሰፋ ይሄዳል። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ባለችበት የባሕር በር እጦት የምትቀጥል ከሆነ ጉዳዩ የከፋ ይሆናል። በጂቡቲ ብቻ በሚገኘው አገልግሎት የኢትዮጵያን ፍላጎት ማርካት አይቻልም። ከዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጉዳት እየደረሰባት ይገኛል።

ቀደም ባለው ጊዜ ስለ አሰብ በሚነገርበት ወቅት በወቅቱ "ሰላም እና ዴሞክራሲ" በሚል አዲስ አበባ ውስጥ ሐምሌ 19 ቀን 1983 ዓ.ም በተካሔደው የቻርተሩ ጉባኤ ላይ ተሳትፌ ነበር። በዚያን ጊዜም የባሕር በር ጉዳይ አንዱ የተነሳ ነጥብ ነበር። በወቅቱ የሕወሓት የርዕዮተ ዓለም ኃላፊ የሆኑት አቶ ተወልደ ወልደማሪያም «ኢትዮጵያን የባሕር በር ማሳጣት የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንቁርት መዝጋት ነው። የአሰብን ነገር በአግባቡ ሳንደራደር ኤርትራ ነፃ ትውጣ የሚባለው ነገር አግባብ አይደለም» ሲሉ ተናግረው ነበር።

አቶ ተወልደ፣ በወቅቱ የኤርትራ ጉዳይ ላይ የተወሰኑ ውሳኔዎች በመኖራቸውና በተለይም በአሰብ ላይ የተደረሰ ስምምነት በመኖሩ የጉዳዩን ምንነት በተመለከተ ጉባዔው ያውቀው ዘንድ አቶ መለስን ጥያቄ ሲጠይቋቸው ነበር። ጥያቄው የቀረበላቸው አቶ መለስም፣ የሰጡት ምላሽ "አሰብን በጋራ እንጠቀማለን፤ ደግሞም እናለማለን ተባብለናል። ይህ በሁለት ሀገሮች መካከል የሚሆን ስምምነት ነው። ከዚያ በላይ አልፎ ኢትዮጵያ በአሰብ ላይ የተለየ ወይም ከዚህ ያለፈ መብት ይኖራታል ብሎ ማሰብ የጦረኞች አመለካከት ነው።" የሚል ነበር። ውይይቱ ቀጣይነት እንዳይኖረውም በማሰብ ሀሳብ እንዳይንሸራሸር የዘጉት ወዲያውኑ ነበር።

እኔም ከዛሬ 23 ዓመት በፊት በዚሁ በዘመን መጽሔት ላይ በሰጠሁት ቃለ ምልልስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉዳዩ እንዳይወያይበት ጉዳዩ የተዘጋና የታፈነ ነው ያልኩት ለዚህ ነው። ከዚህ ባለፈም በአቶ መለስ አማካይነት ስለጉዳዩ ማንሳት የጦረኞች አጀንዳ ነው ተባለ። እንደተፈራውም የኢትዮጵያን

ሕዝብ ማንቁርት የዘጋ ጉዳይ ሆነ። ከዚህ የተነሳ በርካታ ጉዳት ደርሶብናል። መፍትሔ ካላገኘም ጉዳቱ ደግሞ ከዚህ በበለጠ እየሰፋ ይሄዳል።

**ዘመን፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ያጣችበትን የታሪክ ሂደት እንዴት ይመለከቱታል? በዚህ ጉዳይ የሚቆጩበትስ ነገር አለ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** በወቅቱ ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ አሜሪካ የራሷን ሚና ተጫውታለች፤ አቶ መለስን "አንተ አዲስ አበባን፣ አቶ ኢሳያስን ደግሞ አንተ አሥመራን ተቆጣጠር" በሚል ስታስማማ ነበር። በወቅቱ ሲሸመግሉ የነበሩት የቀድሞ የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉት ኸርማን ኮኸን የተባሉ ሰው ናቸው። እርሳቸው እንኳ ኢትዮጵያ አሰብ ላይ መብት ሊኖራት ይገባልና በዚህ ጉዳይ ላይ ተስማሙ ሲሉ ነበር። ይህንንም ዕድል ነው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ገፍቶበት መሔድ ያልፈለገው። ሁለቱም ቦታ መንግሥት እንዲቋቋም ያግባባው የአሜሪካ መንግሥት፣ እንደ መልካም ሐሳብ ያቀረበውን ነገር ሕወሓት/ኢሕአዴግ ግን ተቀብሎ መሄድ አልፈለገም።

አሜሪካንን የሚያክል መንግሥት በጉዳዩ ላይ ድጋፍ አሳይቶ እያለ እስከመጨረሻው ገፍቶ መሔድ ይቻል ነበር። እዚህ ላይ ግን ሙሉ በሙሉ ገፍቶ መሔድ ያልፈለገው ሕወሓት/ኢሕአዴግ ነው እንዳልል ከእነሱ መካከል ጉዳዩን የተቃወመ ሰው መኖሩ ግልጽ ነው። የሕወሓት የርዕዮተ ዓለም ኃላፊ ከአቶ መለስ ጋር አንድ አይነት አቋም አልነበራቸውም። ስለሆነም ጉዳዩ የአቶ መለስ አቋም መሆኑ ግልጽ ነበር ማለት ይቻላል። በወቅቱ ኢትዮጵያ አሰብን በተመለከተ ግልጽ የሆነ ድርድር የማድረግ መብት እንዳላት የገለጹ ናቸው። ይሁንና ውይይት እንዳይካሔድ አቶ መለሱ ጉዳዩን ዘግተውት ነበር።

ይህ በእኔ አመለካከት ያመለጠን ታሪካዊ ስህተት ሆኖ ያለፈ ክስተት ነው። ስለዚህ ይህ የሚያስቆጨኝ ጉዳይ ነው። የመጀመሪያው የሽግግር መንግሥት ሲቋቋም ኢትዮጵያ ያመለጣት ዕድል ነው ብዬ አስባለሁ። ኢትዮጵያ በወቅቱ በጉዳዩ ላይ መደራደር የሚያስችላት እድል ብቻ ሳይሆን አቅሙም እያላት ቸል የማለቷ ነገር እኔ ከአቶ መለስ አመራር ትልቁ ችግር የነበረ ጉዳይ ነው። የብዙ ሚሊዮን ሕዝብ መሪ ሆነው ሳለ የአሰብን ጉዳይ እንደ ኢምንት የወሰዱበት ምክንያት ዛሬም ድረስ አልገባ የሚለኝ ነገር ነው። በኋላ ላይ እንደተረዳሁት ከሆነ የግምት ስህተት መኖሩን ነው። ስለዚህ የሚያስቆጨኝ ነገር ቢኖር በአሜሪካኖቹ ዘንድም የተዘጋ እድል ሳይኖር፤ በኢትዮጵያም በኩል የመደራደር ዕድልና አቅም እያለ ኢጋጣሚውን መጠቀም አለመቻላችን ነው። ኢትዮጵያ የአሰብ ወደብ መብት ሊኖራት ይገባል፤ እናንተ የምትገነጠሉት በዚህ አግባብ ነው የሚለውን በመደራደር ማስኬድ የከለከላቸው ምን እንደሆነ ያስገርማል።

**ዘመን፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ካጣች ከሦስት አስር ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያ የግድ የባሕር በር ያስፈልጋታል በሚል የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሀሳብና ተነሳሽነትን አቅርበዋል፤ ይህንንስ እንዴት ተመለከቱት?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** እኔ አንድ ኃላፊነት ያለበት ሰው ወይም መሪ ማንሳት ያለበትን ጉዳይ እንዳነሱ አድርጌ እቆጥረዋለሁ። ከዚህ ውጭ ግን ይህ የባሕር በር ጉዳይ በአሁኑ ወቅት የተነሳው፣ አጀንዳ ለማስቀየር ነው፤ እንዲህ ነው፤ እንዲያ ነው እያሉ የሚናገሩ አካላት ሃሳባቸው አልባሌ መሆኑን ነው መናገር የምችለው። ኢትዮጵያን በመምራት ውስጥ ያለው ኃላፊነት እነርሱ እንደሚያዩት ቀላል አይደለም። ኢኮኖሚን ለማንቀሳቀስና ለማሳደግ ተብሎ የሚደረገውን ሩጫ እያየን ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህም በዚያም ብለው የሚያስጀምሯቸው ሥራዎች ውጤታማ ሲሆኑ እያየን ነው።

በዚህ ሁሉ ሩጫ ውስጥ ትልቁ የማይሸር ቁስል ለወደብ የምንገብረው ጉዳይ ነው። ፈረንጅ ሲናገር "ያለህን ሁሉ በአንድ ከረጢት ውስጥ አታድርገው" ይላል። ለምሳሌ በጂቡቲ መስመር ላይ አንድ ከፍተኛ የሆነ ችግር ቢገጥመን ሊመጣ ያለውን ፈተና ማሰቡ ብቻ በቂ ነው። ባለፈው መንግስት ከሕወሓት ጋር ባካሔደው ጦርነት ላይ ይህ መሞከሩ የሚታወስ ነው። ኢትዮጵያ የውጭ እቃ የምታስገባበትን መስመር በመዝጋት ማንቁርቷን ለመያዝ ጥረት መደረጉ ይታወቃል።

ነገር ግን የአፋር ልጆች እንዲሁም ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት ከፍለው ጉዳዩን ማስቆም ችለዋል። ይህን በምሳሌነት ያመጣሁልሽ የውስጥ ግጭት እንኳን ምን አይነት ሐሳብ ሊያመጣ እንደቻለ ለማስገንዘብ ነው። ከዚያ የበለጠ አቅም ያለው የውጭ ኃይል ቢመጣ ደግሞ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ማሰብ የሚከብድ አይመስለኝም። የጠላት ችግር የለብንም፤ እዚህም እዚያም ሞልቷል። ስለዚህ ጉዳዩ ዝም ተብሎ የሚተኛበት አይደለም። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ተይዞ በአንዲት መስመር ብቻ መተማመን በፍጹም የማይቻል ጉዳይ ነው። ከዚህ የተነሳ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የባሕር በር ሊኖረን ይገባል የሚለውን ጉዳይ በማንሳት ጥረት ማድረጋቸው አግባብነት ያለው ጉዳይ ነው።

**ዘመን፡- ብዙ ሀገራት ከሩቅ መጥተው ቀይ ባሕርን እየተጠቀሙ ሳለ ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር ያካሔደችው የባሕር በር ስምምነት አንዳንዶችን የሚያስቆጣቸው ስለምንድን ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** የሚያስቆጣቸው ምን ያመጣሉ በሚል ንቀውን ነዋ! ድሃዎች ናቸው በሚል ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ከእንዲህ አይነት ፍረጃ መውጣት አለባት። ከዚህ ንቀት ለመውጣት ደግሞ አስፈላጊውን ርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው። እንዲህ ስል ጦርነት ለማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ሰብሮ ለመውጣት መሥራት ያስፈልጋል። በአሁኑ ወቅት ከዚህ ከባሕር በር ጋር ተያይዞ የጂቡቲ መስመር አንድ ነገር ቢሆን ይህ ብቻውን የማያስተኛ ስጋት መሆኑ ሊታበል አይገባም።

እኛ የባሕር በርን ለ30 ዓመት ያህል አጥተናል፤ ስለሆነም የትኛውንም አካል ቢያስቆጣውም የባሕር በር ለማግኘት ሌላ 30 ዓመት መጠበቅ የለብንም። መንግሥት ለሕዝቡ ኃላፊነት አለበት። እንግሊዞች በፓርላማቸው ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ገብተዋል። የቀድሞ መከላከያ ሚኒስትሩ ለሶማሌላንድ እውቅና እንስጥ በሚል ጥብቅና እየቆሙ ናቸው። ከዚህ በላይ የሚጠበቀው ምንድን ነው በማለት ላይም ይገኛሉ።

ሶማሊያ ወይ ራሷን ችላ አልተገለለችም፤ ራሷን በአግባቡ ማስተዳደር አልቻለችም። በዚያድባሬ አገዛዝ ዘመን በሱማሌላንድ ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ ተካሂዶባቸዋል። በአየር ድብደባ ጭምር ሱማሌላንድን ፈጅቷል። በዚህ መካከል ሱማሌላንዶች ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ ተቃውሞ ጀመሩ። እንዲያም ሆኖ ሶማሊያ ብትንትኗ ሲወጣ ሱማሌላንዶች ግን ጠንካራ ሆነው የራሳቸውን መንግሥት ማቋቋም ቻሉ። ስለዚህ የሞቃዲሾ መንግሥት ከሐርጌሳው መንግሥት ይልቅ ፍርክርኩ የወጣ ነው ማለት ይቻላል። የሶማሊያ መንግሥት ሠላም ማምጣትም ሆነ ራሱን ማረጋጋት ያልቻለ መንግሥት ነው። ቤተ መንግሥቱ ሳይቀር በየቦታው ፍንዳታ ሳይደመጥ የሚውልበት ሀገር ነው። እንዲያውም የሱማሊያ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት ባለውለታው መሆኑን ሊገልጽ ሲገባው መልሶ የኢትዮጵያን መንግሥት ወራሪ ሲል መደመጡ የሚያሳዝን ነው።

እንደተባለው ሌሎቹ ሀገራት የተለያየ ድርድር ሲያደርጉ እንደ ጉዳይ

አይታይም፤ ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ ደግሞ ብዙ ያወራሉ። ሶማሊያ ራሷ ኢትዮጵያ ቀደም ባሉ ጊዜያት በዚሁ አይነት ሐሳብ ለምሳሌ በበርበራ ወደብ ድርድር ባደረገችበት ጊዜ የት ነበረች? በወቅቱ የኢትዮጵያ ድርሻ በበርበራ ወደብ ላይ 19 በመቶ ብቻ ስለሆነ ነው? አሁንስ ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?

ኢትዮጵያ አሁንም ቢሆን አፍሪካ ቀንድ ላይ ስትታይ ከሌሎቹ ጋር የምትነጻጸር ሀገር አይደለችም። በብዙ ትበልጣቸዋለች። ስለሆነም እውነታው ልትበልጥ ትችላለች የሚል አይነት ሳይሆን አሁንም ቢሆን የምትበልጥ ሀገር መሆኗ ነው።

አንድ መታወቅ የሚገባው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር ያደረገችው ድርድር ሶማሊያ ተሳክቶላት ራስ ገዟን ሱማሌላንድ ከራሷ ጋር ብትቀላቅላት ውሉ ቀጣይ መሆኑ ነው። ከዚህ የተነሳ ተጠቃሚ የምትሆነው ራሷ ሶማሊያም ናት። ስለሆነም ኢትዮጵያ የገባቸው ውል ለእነሱም የሚጠቅም መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ከዚህ ያለፈው ነገር የሚመነጨው ከምቀኝነትና ጥላቻ ነው።

ሌላው መታወቅ ያለበት ሱማሊያና ሱማሌላንድ ቢታረቁ ኢትዮጵያ አትታረቁ አትልም። ኢትዮጵያ የምትፈልገው በትብብር መሥራት ነው። ነገር ግን እነርሱ ተስማምተው እስከሚታረቁ ድረስ ኢትዮጵያ መቆየት አትችልም፤ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት መልማትና በኢኮኖሚ ማደግ ለኢትዮጵያ አጣዳፊ ጉዳይ ነው። የሞቃዲሾ እና የሐርጌሳ ቁርሾን ለመፍታት መቶ ዓመት የሚፈጅ ከሆነ የኢትዮጵያ ችግር ደግሞ የዚያን ያህል ዓመት መጠበቅ አይችልም። ስለሆነም ፈቃደኝነት ካሳየው አካል ጋር በመልካም ጉርብትና እና በሰጥቶ በመቀበል መርሕ መጠቀም እንችላለን። ይህ ደግሞ ዓለም አቀፋዊ አሠራር ነው። ስለዚህ ከዚህ አንጻር ማየት ሲገባቸው እዚህና እዚያ መራወጣቸው ተገቢ አይሆንም።

ባይሆን ሶማሊያን የሚያዋጣት ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነቷን ማጠናከር ነው። ኢትዮጵያ ለሶማሊያ በብዙ ዋጋ የከፈለች ሀገር ናት። አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ ወታደር ሶማሊያ ውስጥ ሠላምን በማስከበር ረገድ መስዋዕትነት እየከፈለ ነው።

**ዘመን፡- ግብፅን ጨምሮ አንዳንድ ሀገራት የባሕር በር ስምምነቱን ተከትሎ የሶማሊያን አቋም መደገፋቸው ምክንያቱ ምንድን**



“

**ኢትዮጵያ**
አሁንም ቢሆን አፍሪካ ቀንድ ላይ ስትታይ ከሌሎቹ ጋር የምትነጻጸር ሀገር አይደለችም።



**ኢትዮጵያ** ለሶማሊያ ብዙ ዋጋ የከፈለች ሀገር ናት። አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ ወታደር ሶማሊያ ውስጥ ሠላምን በማስከበር ረገድ መስዋዕትነት እየከፈለ ነው።

**ነው? ኢትዮጵያ ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖስ ይኖር ይሆን?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** የግብፅ አቋም ያልሠለጠነና ካፈርኩ አይመልሰኝ አይነት አካሄድ ነው። ግብፅ ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጀምሮ ስታካሒድ የነበረው ነገር የሚታወቅ ነው። ከግድቡ ጋር ተያይዞ የአሜሪካ መንግሥት ብቻ ያደረገላት ድጋፍ ቀላል የሚባል አልነበረም። ኢትዮጵያ ግድቡን እንዳትሠራ ጫና ለማሳደር ያልተኬደበት ርቀት የለም። ከዚያ የበለጠ ድጋፍ መስጠት አይችልም።

ከሱማሌላንድ ጋር የተገባው ውል ከሕዳሴ ግድብ ጋር ሲተያይ ኢምንት ነው። እንዲያውም ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር ያደረገችው ውል የእነ አሜሪካም ጥቅም ያለበት ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያ እዚያ አካባቢ ጠንካራ መሠረት ማስቀመጥ የአካባቢውን ሠላም በማስከበሩ በኩል ሚናው የጎላ ነው። ሶማሊያ ያንን ያህል ሠላም ማስከበር አትችልም። የሶማሊያ መንግሥት ጦር ኖሮት አሊያም ደግሞ ባሕር ኃይል ኖሮት የዚያን ያህል ድጋፍ ሊሰጥ አይችልም። ሶማሊያ ለባሕር ላይ ነፃ እንቅስቃሴ ድጋፍ መስጠት የማይችል መንግሥት ነው።

ኢትዮጵያ ግን እዛ አካባቢ የባሕር ኃይሏን ብታሳርፍ ያንን አካባቢ ሠላም ይሆን ዘንድ መቆጣጠር ትችላለች። ያንን ድጋፍ ደግሞ የበለጸጉ ሀገራት ይፈልጉታል። ከበርቴ ሀገራት የንግድ መስመራቸውን የተሳለጠ ለማድረግ የኢትዮጵያን እዚያ መኖር የሚፈልጉት ነገር ነው።

ስለዚህ የሶማሊያ ሉዓላዊነት ይከበር ይበሉ እንጂ ከዚህ አልፈው ሔደው ኢትዮጵያን ለመኮነን ያደረጉትም የሚያደርጉትም እንቅስቃሴ የለም። እነዚህ ሀገራት ማለት ስላለባቸው ብቻ “የሶማሊያ ሉዓላዊነት ይከበር!” ከማለት በዘለለ የፈጠሩብን ጫና የለም። ሉዓላዊነት ይከበር ማለታቸው ደግሞ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ስለሆነ እና ማለት የሚገባቸውን ለማለት እንጂ ኢትዮጵያን በመቃወም አይመስለኝም።

እውነት ለመናገር አገራቱ ከሶማሊያ የሚጠቀሙት ምንም ነገር የለም፤ ሶማሊያ ላይ ወጪ የሚያስወጣቸው ነገር እንጂ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ነገር እንደሌለ ያውቃሉ። አሜሪካውያኑ አልሸባብን እንወጋለን በሚል የሚያባክኑት ሀብት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። አሜሪካኑ ጂቡቲ ላይ ካላቸው የጦር ቤዝ እየተነሱ አልሻባብን ለመምታት በብዙ ከስረዋል። ኢትዮጵያ ግን በዚያ አካባቢ ብትሆን በብዙ እንደምትደግፋቸው አሳምረው ያውቃሉ። ስለሆነም ይህ ሁሉ ከጂኦፖለቲክሱና ከሀገራቱ ጥቅም አንጻር መታየት ይኖርበታል።

ስለዚህ ግብፅ ገና ለገና ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ትጣላለች፤ አትጣላም በሚል ክፍተት ፍለጋ የምታደርገው ጥረት ነው እንጂ ግብፆች በታሪክም ሆነ ሁሌ ኢትዮጵያን ኃይል ለማሳጣት ያልሞከሩት ነገር የለም። ይህ ሴራቸው የጀመረው ዛሬ ሳይሆን ከድሮ ጀምሮ ነው። ብዙ ጊዜ የዓባይን ምንጭ እንቆጣጠራለን በሚል ሲባክኑ እንደነበር የሚታወስ ነው። ስለዚህ የግብፅ ጫጫታ የተለመደ በመሆኑ ኢትዮጵያ ሥራዋን እንዳትሠራ የሚግዳት አይደለም።

**ዘመን፡- ኢትዮጵያ እስካሁን የመጣችበት ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ ለባሕር በር ስምምነቱ ምን ያህል አግዟል ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** በእርግጥ እኛ ዝርዝር ዲፕሎማሲያዊ አካሄዱ ምን እንደሚመስል አናውቅም። ይሁንና እኔ የምረዳው ኢትዮጵያ ይህንን ስምምነት ስትፈጽም ያለምንም ነገር ዘላ ገብታበታለች የሚል እሳቤ የለኝም። ያንን ስምምነት ለመፈጸም ግራ ቀኙን እይታ እንደሆነም አልጠራጠርም። እንዲያውም በአሁኑ ወቅት የሶማሊያ ሉዓላዊነት ይከበር የሚሉና ያሉ ሀገራት ሁሉ ጉዳዩን እንደሚያወቁ ነው መረጃው ያለኝ። በርግጥም አንድ አስተዋይ መንግሥት ጉዳዩ ምን አይነት ፋይዳ እና ፈተና እንደሚያመጣ ሳይመዝንና ከሚመለከታቸው ጋር ሳይመክር ዝም ብሎ ውሳኔ አይወስንም።

የዲፕሎማሲ አካሄድ ደግሞ ለኢትዮጵያ እንግዳ የሆነ ነገር አይደለም። ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ታሪክ ውስጥ ብዙ ዘመን የፈጀች እና በዚያም መንገድ ያለፈች አገር ናት። ከዚህ የተነሳ መንግሥት ስምምነትን ሲያደርግ በግብታዊነት አይደለም። አንዳንዶች እንደሚሉት ሳያቅድ እና አጀንዳ ለማስቀየር ሲልም ጉዳዩን አልጀመረም። ኢትዮጵያ ከዓረብ ኢምሬቶችም ጋር የቆየ ግንኙነት ያላት አገር ናት።

እዚህ ላይ አንድ ነገር መጥቀስ እፈልጋለሁ። ፈረንሳይ የኢትዮጵያን ባሕር ኃይል በማደራጀቱ ረገድ ትልቅ አበርክቶ እንዳደረገች ይታወቃል። በማሠልጠኑ፣ በማደራጀቱ እና መርከቦችን ዘመናዊ በማድረጉ በኩል ትልቅ ሚና ነበራት። እሷም ብትሆን ይህን ያህል ኢንቨስት ማድረጓ ምንም ጥቅም ሳታገኝበት በባዶ ሜዳ ይሆናል ማለት የዋህነት ነው የሚሆነው።

እነቻይናም ቢሆኑ በመስታወት ውስጥ ያለ ድንጋይ አይወረውርም እንዲሉ ሆኖባቸውና የታይዋን ነገር ስላለ ነው። ይህ ደግሞ የፖለቲካ ጨዋታ ነው። ስለዚህ እኔ የተካሄደበትን ዝርዝር ጉዳዩን ባላውቅም፣ ነገር ግን ጉዳዩ ቅድመ ዝግጅት ሳይደረግበት የሚወሰን እንዳልሆነ እገነዘባለሁ። ምክንያቱም ኢትዮጵያ የምትሠራውን ነገር ጠንቅቃ ታውቃለች፤ ዲፕሎማሲም ለእኛ እንግዳ ነገር አይደለም። ስለሆነም አካሄዱ ዲፕሎማሲያዊ የሆነ መንገድንም የተከተለ ነው ባይ ነኝ።

**ዘመን፡- ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ከመሆኗ ባሻገር ትልቅ ቁጥር ያለው ሕዝብ እንደመያዟ የሚያስፈልጋት አንድ የባሕር በር ብቻ አይደለም የሚሉ አካላት አሉ፤ እርስዎ እዚህ ላይ ያልዎ አመለካከት ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** ይህ ብዙ ክብደት ያለው ጥያቄ አይደለም። እንደ ኢትዮጵያ ያለ የባሕር በር የሌለው ሰፊ ሕዝብ የያዘ ሀገር ወደባሕር የሚገባባቸውንና የሚወጣባቸውን በሮች ማስፋት ይኖርበታል። ምክንያቱም አንዱ ላይ ችግር የሚፈጠር ከሆነ ወደሌላ ደግሞ መሄድ ይችላል። ምክንያቱም የዛሬ ወዳጅ ነገ ባልተጠበቀ ጊዜ ሊቀየር ይችላል። "ይህ የባሕር በር የራሴ ነው" በሚል እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። በእጅ የተያዘ ምንም ነገር በሌለበት ሁኔታ በርከት ያለ የባሕር በር መኖሩ የግድ ነው።

ሌላው ደግሞ የባሕር በር ያለው ሀገርም ቢሆን ወደቦቹ የተለያዩ የዕቃ አይነቶች የሚመጡባቸውና የሚገቡባቸው እንዲሆኑ ይደረጋል። ለምሳሌ በአንዱ ወደብ ነዳጅ ብቻ የሚገባ ሊሆን ይችላል። ሌላው ወደብ ደግሞ ምግብ ነክን የሚያስገባ ሊሆን ይችላል። ሌላው እንዲሁ የንግድ ሸቀጥ የሚገባበት ሊሆን ይችላል። ከዚህ የተነሳ ወደቦቹ የሎጂስቲክ ፀባያቸው ሊለያይ ይችላል እንጂ እንደ የዕቃዎቹ አይነት ሊለያዩ ይችላሉ። ለምሳሌ ሳውዲ ወደብ ያላት ብዙ ቦታ ነው። ሌላውም ሀገር እንዲሁ ነው። ስለዚህ ይህ ጥያቄ መነሳቱ ራሱ ይገርመኛል። ኢትዮጵያ ከአንድ በላይ ወደብ የግድ ያስፈልጋታል። እንኳን እኛ የባሕር በር ያላቸውም ብዙ ወደብ አላቸው።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ምንም እንኳ ተግዳሮት ያለባት አገር ብትሆንም ለኢኮኖሚ እድገቱ ዋና ቁልፍ የሆነው የባሕር በር የሚያስፈልጋት ስለመሆኑ አከራካሪ አይሆንም።

**ዘመን፡- ኢትዮጵያ ባደረገችው የባሕር በር ስምምነት በተለያየ ምክንያት ተቃውሞ ያላቸው ኢትዮጵያውን መኖራቸው አይታበልም፤ ለእነዚህ አካላት ያልዎት መልዕክት ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** እነዚህ አካላት እስከሚገባኝ ድረስ ኢትዮጵያ ያሳደገቻቸው እና ያስተማረቻቸው ናቸው። በተለይም ብቃት አለን ብለው ከኢትዮጵያ ወጥተው በየውጭ ሀገሩ የሚኖሩ ናቸው። በተለያየ የትምህርት ዘርፍም ሙያቸውን ያሳደጉና አንቱ የተባሉ ምሑራን ናቸው። የሕግ ባለሙያ፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ፣ በፖለቲካውም ዘርፍ ዕውቀቱ ያላቸው ናቸው። የሚያስገርመው ደግሞ ኢትዮጵያ በድህነቷ ያስተማረቻቸው እና አሁን ላሉበት ማዕረግም ያበቃቻቸው ናቸው።

እኔ በፖለቲካ ሕይወቴ ያየኋቸውና በብዙም የደገፉን አካላትም ያሉበት ነው። በተለይም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሂደት ደግሞ የደርግ ሥርዓት መውደቅ አለበት በሚል አብረውን የቆሙ ሰዎችም ጭምር አሉበት። እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያ የተፈራረመችውን ሰነድ ሲያጣጥሉ እሰማለሁ። የሰው ልጅ ማሰብ ሲያቅተውና ሲስት ምንም ማድረግ አይቻልም።

ማሰብ ያቃታቸውና ያሳታቸው ጉዳይ እንደሚመስለኝ ምናልባት ይህ ስምምነት በእኛ እጅ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ከእኛ ፈቃድ ውጭ የሆነውን ነገር ሁሉ እንበትነዋለን የሚል የምቀኝነትና የጥላቻ አካሄድ ነው። ይህ ደግሞ የታመመ አይነት አስተሳሰብ ነው ባይ ነኝ፡፡ ሥልጣን ላይ ማንም ይኑር ማን ኢትዮጵያ የባሕር በር ሊኖራት ይገባል በሚል የሚደረግን ጥረት መቃወም ከጤነኛ ሰው የሚጠበቅ ሐሳብ አይደለም።

ዛሬ ሀገራቱን እያስተዳደሩ ያሉ ዕድሜ ልካቸውን በቦታው የሚቆዩ አይደለም። የሰው ልጅ የእድሜ ገደብ እንዳለው ሁሉ ሥልጣንም የቆይታ ገደብ አለው። መንግሥት ይሄዳል፤ መንግሥት ይመጣል። ያለፉት መንግሥታት ከነገሥታቱ ጀምሮ አቅማቸው እና ዕውቀታቸው በፈቀደ መጠን በባሕር በር ጉዳይ ሲያስሰባቸው ኖረዋል። በዚህም ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉ አሉ።

ቀደም ባለው ጊዜ እነጣሊያን መርከባቸው ቆሞ ቤንዚን የሚቀይሩበትን ትንሽ ቦታ እንድንፈቅድላቸው በወዳጅነት ጠይቀውን ቀስ በቀስ ግዛታቸውን ያስፋፉበት ሁኔታ ተፈጥሮ እንደነበርም የሚታወስ ነው። በጂቡቲም በኩል ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። በጂቡቲ ፈረንሳዮች ከ1999 ዓ.ም በኋላ በአፄ ምኒሊክ ጊዜ ተጠቀሙ ተብሎ የተተወ ቦታ ነው። በኋላ ጊዜው ሲደርስ እንደሚመለስ ዓይነት የነበረም ጭምር ነው።

ጂቡቲ መንግሥት ሆና የተቋቋመችው በደርግ ጊዜ ነው። ይህ ደግሞ ፈረንሳዮች ጂቡቲን ትተው ወጥተው የጂቡቲ መንግሥት የተቋቋመው በቅርቡ ነው። እንዲያውም በመሐሉ ፈረንሳይ ወጥቶ ባዶ በሆነበት ጊዜ አሰብ አካባቢ የነበረው የኢትዮጵያ ወታደር ወደ ጂቡቲ ሔዶ ተቆጣጥሮ ነበር። ይሁንና የወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ፣ "ትታችሁ ውጡ" ብለው ባስተላለፉት መልዕክት ትተው ለመውጣት ተገደዋል። በወቅቱ የጂቡቲ መንግሥት የሚባል ነገር አልነበረም። እርሳቸውም በወቅቱ እንደዚያ ያሉት ከኤርትራ ተቃዋሚዎች ጋር ባላቸው አለመግባባት የተነሳ ሲሆን፣ ጦሩን ወደዚያ እንዲሄድ ለማድረግ አስበው ይመስለኛል። ጂቡቲ መንግሥት ያቋቋመችው ከዚያ በኋላ ነው።

ስለዚህ አሁን ላይ ኢትዮጵያ ያደረገችውን ስምምነት የሚያጣጥሉ አካላት

እውነት ለመናገር እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም። በማኅበራዊ ትስስር ገጽ የዕለት ጉርሳቸውን የሚጋግሩ ናቸው። ማኅበራዊ ትስስር ገጹን መተዳደሪያቸው ያደረጉ አካላት ናቸው። ነገራቸው ሁሉ አልባሌ በመሆኑ እሱ ሊያሳስበን አይገባም። ከኢትዮጵያ እቅድ ጋር ሲነጻጸሩም ምንም አይነት ለውጥ የማያመጡና ከግምት የሚገቡም አይደለም። በጥቅሉ ጫና መፍጠር የሚችሉ አይደሉም። ስለዚህም የባሕር በርን በተመለከተ የሚንጫጫው አካል ይንጫጫ፤ ኢትዮጵያም ሥራዋን ትቀጥል። ሥራ በመሥራት ለቀጣዩ ትውልድ የተረጋጋች እና ከስጋት ነፃ የሆነች ሀገርን ለማስረከብ በተነደፈው እቅድ ላይ ጠንክሮ መሥራት ነው። ስለዚህ በየማኅበራዊ ትስስር ገጽ ላይ ገጼን ውደዱ፤ ሰብስክራይብ አድርጉ እያሉ ወደፊትም ኑሯቸውን በዚህ ሊገፉ በወደዱ አካላት የሚቀለበስ እድገት የለም፤ ሊያሰጋም አይገባም። በተመሳሳይ በፖለቲካ ሕይወቴ እንዲህ አይነት ነገር ደርሶብኝም ስለማውቅ እሱን አካሄድ ንቆ በመተው ቁም ነገሩ ላይ ማተኮር አዋጭ ነው።

**ዘመን፡- ፖለቲካንና ብሔራዊ ጥቅምን ያለመለየት ችግር ከምን የመነጨ ነው ይላል? መፍትሔውስ ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** ይህ አስተሳሰብ አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በእኔ እጅ ካልሆነ ሌላው የሚያደርገው ነገር ሁሉ ውድቅ መደረግ አለበት ከሚል አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው። እኔ የሌለሁበት ነገር ጥላሸት መቀባት አለበት የሚል ነው። ከዚህ አልፎ ጠንካራ መረጃ ኖሮት የሚረታ ነገር የላቸውም። ለራሳቸው በተሰደዱበት ሀገር ለራሳቸው አቅም ስላጡ የዕለት ጉርሳቸውን የሚያሳድዱ በመሆናቸው ጭምር ነው። እንዲህ ስል የሰውን ልጅ ጨርሶ ለማጣጣልና ለማንቋሸሽ ፈልጌ አይደለም፤ ይሁንና በአሁኑ ወቅት እያሳዩ ያለው ባሕሪ ግን ከዚህ የተለየ ሆኖ አላገኘሁትም።

**ዘመን፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ስምምነት ማድረጓ የቀጣናዊ ትስስርን ለማሳለጥ ምን ሚና ይኖረዋል? ይህ ስምምነት ለአፍሪካና ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የሚኖረውን ፋይዳስ እንዴት ይገልጹታል?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** በመጀመሪያ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚዋም ሆነ በጦሯ የጎላች ሀገር መሆን ለአካባቢው መረጋጋት ብዙ ጠቀሜታ አለው። እስካሁንም ድሃም እየተባለች በአካባቢዎቹ ለሚፈጠሩ አለመረጋጋቶች ላይ በሠላም አስከባሪነት እየገባች ብዙ ሚና እየተጫወተች ነው።

ኢትዮጵያን እንደ ጠላት የሚያየው የሞቃዲሾ መንግሥት መቼ አመስጋኝ እንደሚሆን አላወቅም እንጂ ኢትዮጵያን ሲከስ መስማቱ በጣም የሚያሳፍር ነው። በአንድ ወቅት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ሠራዊት ሠላምና መረጋጋት እንዲያመጣ ወደ ሶማሊያ ልናስገባ ነው ባሉበት ጊዜ እኔ የፓርላማ አባል ነበርኩ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሠራዊት አይግባ፤ ምክንያቱም ከሕዝቡ ጋር ያጣላናል በሚል እና በመቃወም ከረር ያለ ክርክር አስነስተን ነበር። ምክንያቱም ከሶማሊያ ሕዝብ ጋር ያጣላናል በሚል ነው። ይሁንና "አይሆንም!" ብለው ሠራዊቱን አስገቡ። ይህ ሠራዊት ወደሶማሊያ ገብቶ ሞቃዲሾ ከተማን ነፃ አውጥቷል። ስለዚህ ኢትዮጵያ ጠንካራ ሀገር ናት። በቀጣዩም ጥንካሬዋ ይበልጥ እንዲጎላ ወደብ ያስፈልጋታል።

ደቡብ ሱዳን ነፃ ሆና ስትቋቋም የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ኃይል ነው ድጋፍ ሰጥቶ መንግሥቷ እንዲቋቋም ያበቃው። ስለዚህ ኢትዮጵውያን እስከ ሩዋንዳም ድረስ ለሠላም ማስከበር የሄዱ ናቸው። የኢትዮጵያ ጥንካሬ ከቀጣናውም ያለፈ ስለመሆኑ ዓለም ያውቀዋል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የበለጠ ጠንካራ ሀገር መሆን በቀጣናው ላሉ ሀገራት ሁሉ አለኝታ ነው። በእስካሁኑ ሒደትም ዝም ብሎ ሔዶ ለአንዱ ወግኖ ያደረሰው ጥፋትም የለም። አዳዲስ መንግሥታት ሲቋቋሙ ሀገር እንዳይጎዳ ሕዝቡ ላይ መከራ እንዳይደርስ ድጋፍ ከማድረግ ውጭ የሠራው ጥፋት የለም።

**ዘመን፡- ከዚሁ ከባሕር በር ጋር አያይዘው ማስተላልፍ የሚሹት መልዕክት ካልዎ ሐሳብዎን ይግለጹልን?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ የውስጥ ችግሮች እንዳሉበት ይታወቃል። በጥቂቱ ለማንሳት ያህል ኦሮሚያ እና አማራ ክልል ያለ ችግር መጥቀሱ በቂ ነው።

ዝም ብለው በመመኘት ብቻ መንግሥት እንዲፈርስላቸው የሚፈልጉ አካላት አሉ። መንግሥት ፈርሶ ቦታው ላይ ምን ለማስቀመጥ እንደፈለጉ አናውቅም። መንግሥታዊ ሥርዓትን በማጠናከርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ድረስ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ አድርጎ እና በሀገር ውስጥም አመራር ሰጥቶ መኖር ብዙ አቅም፣ ጥበብና ብቃትን የሚሻ ጉዳይ እንጂ በምኞት የሚመጣ አይደለም።

ዝም ብሎ ብቻ በወሬ መንግሥት ለመሆን ማሰብ አዋጭም አይደለም። "እነ እንትና እዚህ ደርሰዋል፤ እዚያ ደርሰዋል" እየተባለ የሚባለውን ነገር መስማት ያስገርማል። ይህ አካል ወደየአዕምሮ ቢመለስና ቢያጤነው መልካም ነው እላለሁ። በዚህ አካሄድ ውስጥ በብዙ የተማሩና በሥራቸው አንቱ የተባሉ አካላት በስሜት ተገፍተው ሲገቡ ተስተውለዋል። ሀገር ደግሞ በስሜትና በእልህ ሊመራ አይችልም። አመራር ላይ ያሉ አካላትን ምክንያትና ሰበብ እየፈለጉ ማጥላላት ትርጉሙ ምን እንደሆነ አይገባኝም።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግስት ባያጣ መልካም ነው። ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ የዓለም መጨረሻ አድርጎ መቁጠሩም ተገቢ አይሆንም። ያለው ፈተና እንደማይስተካከል አድርጎ በአዕምሮ ውስጥ ማስረጽ አይበጅም። የማይካደው ነገር ችግሮች መኖራቸው ነው፤ እንደሚታወቀውም አንዳንድ መንገዶችም ተዘግተዋል። የሚሰሙ ነገሮች ሁሉ ነውር የሞላባቸውም ጭምር ናቸው። በእያንዳንዳችን ቤተሰብ ላይ የሚደርስ ነገርም አለ።

ይሁንና የብርሃን ፍንጣቂ ሊታየን ይገባል። ሁሉንም ጨለማ አድረገን መሳል የለብንም። እንዲያ ካደረግን ጨለምተኛ እንሆናለን። ተስፋ ማድረግ መልካም ነው። እናም እኔ ተማጽኖዬ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ተረጋጋ የሚል ነው። ስሜታዊ አትሁን፤ አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርገው ማንቋሸሽ ኢትዮጵያዊነትን የሚመጥን ስላልሆነ ከዚያ ድርጊት ተቆጠብ። በመሰዳደብና አንዱ ሌላውን በመግፋት የሚመጣ ጥቅም የለም። ይልቁኑ ሕዝቡም አገርም ይጎዳል። በሬ ወለደ ወሬም የትም አያደርስም። መንግሥት አንድን ሕዝብ ሆነ ብሎ አይጎዳም። ሠላም ማስፈን ተቀዳሚ ዓላማው ስለሆነ በሚያደርገው እንቅስቃሴም «አትንኩኝ» አትበል። እዚህ እና እዚያ ሆኖ የጎበዝ አለቃ ተደራጅቶ ቢከርምም ሀገር መምራት እና ቡድን መምራት ለየቅል ናቸውና ከስሜታዊነት መውጣት ያሻል። እንዲያ ማድረጉ የሠላማዊውን ሕዝብ ኑሮ እንደመበጥበጥ ይሆናል። መንግሥት ደግሞ እንደእሱ አይነት አካሄድ ሲያጋጥመው ቆሞ የማይመለከት መሆኑን መገንዘብ ያዋጣል። በተለይ ተምሬያለሁ የሚል አካል ቆም ብሎ ማሰብ ይጠበቅበታል። እኔ በበኩሌ ግን ኢትዮጵያ በዚህ አይነት ግርግር ትፈርሳለች የሚል እምነት የለኝም። እኛም ባለን አቅም እንንከባለላለን እንጂ ኢትዮጵያ ስትፈርስ ቆመን አናይም ባይ ነኝ። ስለዚህ አገራችን በተፈጥሮም ጠንካራ የሆነች አገር አድርጌያት ነው የማስበውና ስሜታዊ አንሁን መልዕክቴ ነው።

**ዘመን፡- ለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ በዘመን መጽሔት ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# የወደብ ጉዳይና ኢትዮጵያ





© 2011 Encyclopædia Britannica, Inc.

# የወደብ ጉዳይና ኢትዮጵያ

እስማኤል አረቦ

ኢትዮጵያ በታሪኳ የአሳለፈቻቸው መነሣትም ሆነ መውደቅ በቀጥታ ከባሕር ጋር ይያያዛል። በቀይ ባሕር ላይ በነገሡቻባቸው ዘመናት ከአራት በላይ ሰፋፊ ወደቦች ነበሯት። የባሕር በሯና ወደቦቿ በአጎናጸፏት ዕድልም ከአክሱም ጊዜ ጀምሮ በዓለም በኃያልነታቸው እና በዘመኑ ሥልጣኔ ከሚጠቀሱ ጥቂት አገሮች አንዷ ለመሆን የቻለች አገር ነበረች።

በአንጻሩ ኢፍትሐዊ በሆነ መንገድ ወደብ አልባ ስትሆን ደግሞ ከሥልጣኔዋ አሽቆልቁላ፤ ብትናገር የማትደመጥ፣አቅሟ የደበዘዘ፣ ኢኮኖሚዋ የተዳከመ፣ ሰላም የራቃት አገር ለመሆን በቅታለች።

ለመሆኑ በታሪክ አጋጣሚ ኢትዮጵያ ከነበረችበት የኃያልነት መድረክ ወርዳ እንዴት ቁልቁል ልትጓዝና የዓለም ጭራ ልትሆን በቃች? ይህ ጽሑፍ እነዚህንና ሌሎች ተጓዳኝ ሐሳቦችን ይመልሳል። የኢትዮጵያ የገናናነት ምንጭ ከሆነው ከቀይ ባሕር እንጀምር።

## ቀይ ባሕር

ቀይ ባሕር ከደቡብ ሶርያ ተነሥቶ በእስራኤልና ዮርዳኖስ የሳይናይ በረሓን አቋርጦ ወደ ቃባ ሰላጤ የሚገባና 2ሺሕ 250 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን አካባቢ ነው። ከሕንድ ውቅያኖስ፣ ከኤደን ባሕረ ሰላጤና ከዐረብ ባሕር ጋር ይገናኛል።

ቀይ ባሕር በሜዲትራንያን በኩልም ሆነ በሕንድ ውቅያኖስ የነዳጅ ዘይት ለሚጭኑ መርከቦች ዋና የባሕር መንገድ ነው። በዚሁ ባሕር ላይ በዓመት ከ3ሺሕ በላይ መርከቦች የተለያዩ ዕቃዎችን ጭነው ይመላለሳሉ። በአጠቃላይም ቀይ ባሕር ከአለው ስትራቴጂክ ስፍራነት በተጨማሪ 40 በመቶ የሚሆነው የዓለም የንግድ ልውውጥ በዚሁ ባሕር ላይ እንደሚከናወን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአሁኑ ወቅትም ሳዑዲ ዐረቢያ፣ የመን፣ ግብጽ፣ ሱዳን፣ እስራኤል፣ ዮርዳኖስ፣ ኤርትራና ጅቡቲ በጋራ የቀይ ባሕር ባለቤቶች ናቸው። ኢትዮጵያ ከዚህ መድረክ ከተገለለች ከ32 ዓመታት በላይ ተቆጠሩ።

ኢትዮጵያ ለሺሕ ዓመታት የቀይ ባሕር ንግሥት ሆና የኖረች አገር ነበረች። ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ‹‹አሰብ የማን ናት? በሚለውና ስለ ቀይ ባሕርና የወደብ ጥያቄ በስፋት በተነተኑበት መጽሐፋቸው እንደአሰፈሩት፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት እንደነበረች በመጀመርያ የታወቀው ከ100 እስከ 150 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር።

‹‹ዘ ፐሪፐለስ ኦቭ ዘ ኤርትሪያን ሲ›› በተሰኘው መጽሐፍም የአክሱም መጠነ ሰፊ የንግድ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ዋነኛ የባሕር በር በነበረው በአዶሊስ ይተላለፍ እንደነበር ያትታል። በወቅቱ የነበረው ንጉሡ ነገሥት ዐፄ ካሌብ እጅግ የዳበረ የባሕር ኃይል እንደነበረውና ቀይ ባሕርንም ተሻግሮ የመንንና ደቡብ ዐረቢያን ይቆጣጠር እንደነበር ይኸው መጽሐፍ ያብራራል።

ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በሁሉም ዘርፎች ላይ አስደናቂ ለውጥ የታየበት ስለመሆኑ የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት የሚያስረዱት ሐቅ ነው።

ስለወደብ የሚያነሡ ሰዎች እንደጸብ ጫሪና ጦርነት ናፋቂ እየተቆጠሩ ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ላይ ያላት መብት ተድበስብሶ እንዲቀር ተደርጓል።

እነዚህ የአልተቋረጡ የታሪክ አካኼዶች ደግሞ ዛሬም ድረስ የአልደበዘዙ የታሪክ ዐሻራዎች ናቸው። እነዚህ ነባራዊ ሐቆችም ኢትዮጵያን በዓለማች ላይ ከሚገኙ ጥንታዊና የአልተቋረጠ የሥነ መንግሥት ታሪክ ከአላቸው አገሮች መካከል አንዷ እንድትሆን አስችሏታል።

በተለይም በኢዛና እና በካሌብ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በነበራት ከወርቅ፣ ከብርና ከነሐስ በተሠሩ መገበያያ ገንዘቦች በቀይ ባሕር ላይ እጅግ ብዙ የጦርና የንግድ መርከቦችን ታንቀሳቅስ ነበር። በእነዚያ ከፍተኛ ቁጥር የአላቸው የጦርና የንግድ መርከቦች በመታገዝ ከደቡብ ዐረብ አገሮች እስከ ሕንድ ውቂያኖስና የአሁኗ ቻይና ድረስ በሰፊው የተዘረጋ የግንኙነት መሥመር ነበራት። በዚህ ሁኔታ ዘርፈ ብዙ በሆነው የኢኮኖሚ፣ የንግድ፣ የዲፕሎማሲና የመንግሥታት ግንኙነት በተጠናከረ መልኩ ታካኺድ እንደነበረ ከጥንት ሥልጣኔዋ የከፍታ ልኬት አንጻር የተሰነዱ ነባራዊ የታሪክ ድርሳናት አስረጂዎች ናቸው።

ኢትዮጵያ ለአያሌ ዓመታት ታስተዳድረው በነበረው የቀይ ባሕርና የባሕር በሮቿ ግዛቶችም ከላይ ከተጠቀሱት አገሮች ጋር የዝሆን ጥርስ፣ የቅመማ ቅመም ምርቶችን፣ የሙጫ ተክሎችን እንዲሁም ሌሎች ወጪና ገቢ ሸቀጦችን፣ አልባሳት፣ ሽቶና ጌጣጌጦችን በመላክና ወደአገር ውስጥ በማስገባት የተቀላጠፈ የንግድ እንቅስቃሴ ታካኺድ እንደነበርም ታሪክ ይነግረናል።

ቀይ ባሕርን በሰፊው ትናኘበት በነበረበት ጊዜ ከየመን እስከ ሕንድ፣ ከሶሪያ እስከ እስራኤል፣ ከሳኡዲ ዐረቢያ እስከ ግብጽ፣ ከቻይና እስከ አውሮፓና ኢዤያ ድረስ ጠንካራ የመንግሥታት ግንኙነትን ፈጥራ ቆይታለች። በዚህ የተነሣም የልዕለ ኃያልነት አስፈሪነቷን ለዓመታት እንደቆየችበት የአገሪቱ የዲፕሎማሲ ታሪክ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው እውነት ነው።

ታዋቂው ምሁር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ‹‹አደጋ የአንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ›› በሚለው መጽሐፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል። ‹‹ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤት በነበረችበት ዘመን በመርከቦቿ ከሕንድ እስከ ኢየሩሳሌም ከነበሩ አጋሮቿ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ነበራት። አንዳንዴም ጭቆና የደረሰባቸውን ወገኖች ለመርዳት የጦር ኃይል በመላክ ሁኔታዎችን ትቆጣጠር ነበር።›› ሲሉ ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ የጥንካሬ ምንጭ እንደነበረ ያትታሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ዋና ዳይሬክተር ሆነው

ለረዥም ዘመን የአገለገሉት ረዳት ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካርያ እንደሚሉትም፣ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕርን የንግድ እንቅስቃሴ በመቆጣጠሯ ምክንያት በወቅቱ የአክሱም ሥልጣኔ እንዲያብብ ምክንያት ሆኗል። በወቅቱ በዓለም ላይ ከነበሩት ሥልጣኔዎች አንዱ ሆኖ ለመውጣቱም ምክንያቱ የባሕሩ ንግድ ነው። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔና ገናናነት ከቀይ ባሕር ጋር የተያያዘ ነው።

## ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር የማግለል ሴራዎች ከድሮ እስከ ዘንድሮ

ከአክሱም ሥልጣኔ ጀምሮ የቀይ ባሕር አካባቢ ትኩረት የአገኘ ስፍራ ነው። በየዘመናቱ የነበሩ ኃያላን ቀይ ባሕርን ሳይዙ ኃያልነታቸውን ማረጋገጥ የሚታሰብ አልነበረም።

ቀይ ባሕር በተለይ ከስዊዝ ካናል መከፈት ጋር ተያይዞ የዓለም የንግድ ኮሪደር ለመሆን ችሏል። ቀይ ባሕርን የመቆጣጠር ፍላጎት የዓለም ኃያላን አገሮች ሁሉ ምኞት ነው። እነዚህ አገሮች ኢትዮጵያ እንዳትቀናቀናቸው በየዘመናቱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ከአካባቢው እንድትርቅ አድርገዋታል።

ረዳት ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካርያ እንደሚገልጹትም፣ በተለይ ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት በኋላ የዓለም ነባራዊ ሁኔታ መቀየር፣ በራሷ በአገሪቱም የመሪዎች መለዋወጥ ምክንያት አገሪቱን ከአለ ወደብ በሚያስቀር ውል ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ሆነ። ይህ መሆኑ ደግሞ የአገሪቱን ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ኩነቶች በመቀያየር አገሪቱን ወደብ አልባ ከማድረጉም ባሻገር ከቀይ ባሕርና ከኤደን ባሕረ ሰላጤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነቷ ውጪ እንድትሆን አስገድዷታል።

በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ወደብ አልባ አገር በመሆኗ በወጪ ገቢ ምርቷ ላይ የሌላ አገር ጥገኛ እንድትሆን አስገድዷታል። ይህም ለራሷ ታውሎው የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ በማቀጨጭ በኢኮኖሚዋ ላይ ዕድገት እንዳይመዘገብ የፊጥኝ አስሯታል። ከቀይ ባሕር በ 60 ኪሎ ሜትርና ከሕንድ ውቂያኖስ በ ሁለት መቶ ኪሎሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ቢሆንም፣ እነዚህን አካባቢዎች ተጠቅማ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን እንዳታደርግ የማግለል ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።

«በተለይም ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ የሚባለው ግብጻዊ የተባበሩት መንግሥታትን ለአራት ዓመት በመሪነት ወቅት ኤርትራም ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ትልቅ ሚናን የተወጣ ነው። እኔም በወቅቱ አብሬያቸው ስለነበርኩ ስለሁኔታው በደንብ ዐውቃለሁ። ይኽንን ተግባሩን ለመፈጸምም ከጅቡቲ እስከ ሱዳን ድረስ በጀት አስሶ አዲስ በምትወለደው የዐረብ ሊግ ላይ ኤርትራን አባል ማድረግ አለብን በማለት ብዙ ሠርቷል።» ሲሉ ረዳት ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካርያ ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም «አሰብ የማናት?» በሚለው መጽሐፋቸው፣ ግሬንሬ ኮፕሌይ የተባለ የአፍሪካ ኤክስፐርት ጋዜጠኛን ጠቅሰው የሚከተለውን አስፍረዋል።

«የግብጽ የአፍሪካ ቀንድ ዋነኛ ፖሊሲ ኢትዮጵያ በአካባቢው የበላይነት እንዳይኖራት ከባሕሩ ዙርያ ማግለል ነው። ግብጽ የኤርትራ ነጻ አውጪዎችን በመርዳት እና የቀይ ባሕርን ደቡብ ክፍል ከኢትዮጵያ እጅ በማውጣት ኤርትራ ነጻ እንድትወጣና ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር አካባቢ ተገልላ በተፈጥሮም ሆነ በባህል መቼም የኤርትራ አካል ሆና የማታውቀው አሰብን እንድታጣ አደረገቻት»

አቶ ሀብተ ሥላሴ የተባሉ ምሁር፣ «ኢትዮጵያዊነት፣ ኢኮኖሚያዊ ልማትና እንቆቅልሾቹ» በሚል መጽሐፋቸው ወስጥ የሚከተለውን አስፍረዋል።

«ሕውሐት ሥልጣን ላይ ቂብ እንዳለ የመጀመርያ ሥራው አድርጎ የወሰደው ለኤርትራ መገንጠል ሕጋዊ ዕውቅና መስጠት ነበር። ይህ አቋም ሲፈጸም የኢትዮጵያ ሕዝብን አቋም ሳያካትት ነበር። የአሜሪካ የአፍሪካ ጉዳዮች ምክትል ጸሐፊ በነበረው ሄርማን ኮህን ሊቀመንበርነት በ1983 ዓ.ም. ለንደን ላይ «የለንደን የሰላም ጉባኤ » ተካኺዶ ነበር። ምንም እንኳን አቶ ኮህን ኢትዮጵያን ለሕውሐት አሳልፎ በመስጠቱ ቢወቀስም በስብሰባው ሒደት ላይ ኢትዮጵያ የባሕር በር እንደሚያስፈልጋትና አሰብን እንድትወስድ የሻዕቢያን መሪ አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂን ጠይቀው ነበር። በሚያስገርም መልኩ በጊዜው ሕወሐትን ወክሎ የቀረበው የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ጉዳዩን ሳይቀበለው ቀርቷል።» ሲሉ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችበትን ምክንያት ያስረዳሉ።

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት መሪ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር አሚረ ቀናው እንደሚሉት፣ በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ስለወደብ ማውራት የተወገዘ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። ስለወደብ የሚያነሡ ሰዎች እንደጸብ ጫሪና ጦርነት ናፋቂ እየተቆጠሩ ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ላይ ያላት መብት ተድበስብሶ እንዲቀር ተደርጓል። በዚሁ የልብ ልብ የተሰማቸውም የዐረብ እና የቀጠናው ሀገሮች ኢትዮጵያን ከነጭራሹ ከአካባቢው ገሸሽ የሚያደርጉ ስምነቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል። የቀይ ባሕር ጥምረት (Red sea Alliaince) ወይም ደግሞ የጂቡቲ የሥነ ምግባር ደንብ (Code of conduct) እና የቀይ ባሕር ደኅንነት ተለዋዋጭነት መድረክ (Red sea security dynamics forum) ኢትዮጵያን የአገለሉ ስምምነቶች ተመሥርተዋል።

በተለይም ኢትዮጵያንና እስራኤልን የአገለለ የቀይ ባሕር ደኅንነት ተለዋዋጭነት መድረክ (Red sea security dynamics forum) ተመሥርቷል። ይህ መድረክ ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር ጋር ያላትን ትስስር የካደና ከነጭራሹም የዘነጋ ነው። ይህ እና ሌሎች ከላይ የተፈረሙት ስምምነቶች ኢትዮጵያውያን በቀይ ባሕር ላይ የአላቸውን መብቶች በአንድነት ለማስከበር እስከአልተነሡ ድረስ አገሪቱን ከቀይ ባሕር የማራቁ ጉዳይ የበለጠ እየተጠናከረ እንደሚሄድ አመላካች ነው፣ ሲሉ ሁኔታውን ያብራራሉ።

## የኢትዮጵያ መሪዎችና የባሕር በር ጥያቄ

የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄን በተመለከተ በዝርዝር የጻፉት ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም እንደሚተነትኑት፣ በዘመነ መሳፍንት ማዕከላዊ መንግሥት ከመዳከሙ ቀደም ብሎ በዐፄ ፋሲል ሞትና በዐፄ በካፋ መንገሥ መካከል ለ65 ዓመታት የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ ይዞታ እየተዳከመ ቢሔድም በዐፄ በካፋ፣ በዐፄ ኢያሱ ሁለተኛ፣ በዐፄ ኢዮአስ እስከ 1769 ዓ.ም. ድረስ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ጠረፍ የተጠናከረ ይዞታ እንደነበራት ታሪክ ይገልጻል።

ነገር ግን ኢትዮጵያ ከ1769 ዓ.ም. በኋላ የተለያዩ ሴራዎች እየተሠሩባት በቱርኮች፣ በግብጾች፣ በጣልያኖችና በፈረንሳዮች አማካኝነት የሰሜን ግዛቶቿ እና የባሕር ጠረፎቿን የምታጣበት ሁኔታ ተፈጠረ። ዐፄ ቴድሮስ፣ ዐፄ ዮሐንስ፣ ዐፄ ምኒልክ፣ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሁሉም የባሕር በር የማስመለስ ጉዳይን በውጪ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ግዙፍ እና ቀዳሚ ጉዳይ አድርገው ብዙ ጥረት ሲያደርጉ እና ተግተው ሲሠሩ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ዋቢ ናቸው።

ዐፄ ቴዎድሮስ እ.ኤ.አ. ጥቅምት 20 ቀን 1855 ለእንግሊዟ ንግሥት ኤልሳቤጥ በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ብለው ነበር።

«ቱርኮች የአባቶቼን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገለው ነው። ቱርኮች በባሕር ላይ ሆነው መልእክተኛዩን አላሳልፍም ብለው ችግር ፈጥረውብኛል» ሲሉ ቱርኮችን ከቀይ ባሕር ለማስወጣት መወሰናቸውንና የእንግሊዝ መንግሥትም ድጋፍ



**ዐፄ ቴድሮስ**



**ዐፄ ምኒልክ**



**ዐፄ ኃይለ ሥላሴ**

እንዲያደርግላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን የሚያሳይ ደብዳቤ በሰነድ መልክ ይገኛል።

በተመሳሳይም ዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ቀይ ባሕርን ከወራሪዎች ለማስለቀቅ ብዙ ደክመዋል። ዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ሥልጣን ላይ ሲወጡ ኢትዮጵያ በቱርኮች፣ በግብጾች፣ በጣልያንና በእንግሊዝ ሴራ ከአክሱም ነገሥታት ጀምሮ የነበሯትን የባሕር በሮች ተነጥቃ ሙሉ ለሙሉ ወደብ አልባ የሆነችበት ጊዜ ነበር። ዐፄ ዮሐንስም የተነጠቁትን የባሕር በርና ወደቦች ለማስመለስ ጠንካራ ትግል ያደርጉ ነበር።

ሰኔ 10 ቀን 1872 ለእንግሊዝ ንግስት ቪክቶርያ በጻፉት ደብዳቤም ምጽዋን ለማስመለስ በሚያደርጉት ጦርነት እንዲያግዟቸው መልእክት ልከው ነበር።

‹‹የምጽዋ በር የአባቶቼ የነገሥታት ኢትዮጵያውያን ነው። አሁንም እንበለ በር ቤተ መንግሥት አይቀርምና በእርስዎ ወኪልነት ርዳታ የምጽዋን በር እንድይዝ ያድርጉልኝ ብዬ አምናለሁ።››

ዐፄ ሚኒልክም እንዲሁ የኢትዮጵያን የባሕር በር ለማስጠበቅ ብዙ ደክመዋል። በተለይም ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ስትገለገልበት የነበረውን የዘይላን ወደብ ለማስመለስ በሚያደርጉት ትግል የጣልያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ እንዲያግዛቸው በ1876 ዓ.ም. ደብዳቤ ጽፈው ነበር።

‹‹የዘይላን በር ነገር በሚቻልዎ ነገር ሁሉ ተጣጥረው በእኔ እጅ ቢሆን እንኳን በሐረርጌ፣ በአርሲ፣ በከንባታ፣ በጅማና በከፋ ያለውን ንግድ ሁሉ በዘይላ አደርገው ነበር። ስለዚህ ጠንቅቀው ቢያስለቅቁልኝ እወዳለሁ.... ››

በዐፄ ኃይለ ሥላሴ የንግሥና ዘመን የዓለም አቀፍ ሕግና የዲፕሎማሲ ምሁር በሆኑት ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ እና ሌሎችም በአደረጉት ጥረት በ1952 ዓ.ም. በኤርትራ ሕዝብ ተወካዮች ፍላጎትና በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቀለች። ለዘመናት ትግል ሲደረግበት የቆየው የባሕር በር ጥያቄ ከአንድም ሁለት የምፅዋ እና የአሰብ የባሕር በር ባለቤት እንትሆን ማድረግ ተቻለ።

በሒደት ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ተቀላቀለች። ነገር ግን የፌዴሬሽኑ መፍረስ ሻቢያ እና ጀበሃን በኋም ሕውሐትን የመሳሰሉ ነፃ አውጪ ነን የሚሉ ድርጅቶች ተፈጠሩ። በመጨረሻም በድጋሚ ኢትዮጵያ ወደብ የሌላት የባሕር ጠረፍ አልባ እስረኛ አገር ሆነች።

“

በአጠቃላይ
**የኢትዮጵያ**
ሥልጣኔና ገናናነት ከቀይ
ባሕር ጋር የተያያዘ ነው።

## ከብዙ ወደብ ባለቤትነት ወደ ወደብ አልባነት

ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ላይ ነግሣ በቆየችባቸው ወቅቶች የበርካታ ወደቦች ባለቤት ነበረች። ከእነዚህ ውስጥ በዋነኛነት አዶሊስ፣ ምጽዋ፣ አሰብ፣ ዘይላ ተጠቃሾች ናቸው።

ዘይላ ሶማሊያ እንደአገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባሕር በር ነበረ። ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች።

አሰብ፤ ምጽዋ እና አዶሊስ ኢትዮጵያ በብቸኛነት ስትጠቀምባቸው የነበሩና ኤርትራ ስትገነጠል አብረው የሄዱ ናቸው። በተለይም አሰብ ኢትዮጵያዊ አፋሮችን ጨምሮ ከነወደቡ ኢፍትሐዊ ባልሆነ መልኩ ተላልፈው የተሰጡ የኢትዮጵያ ሃብቶች ናቸው። ይህ ኢፍትሐዊ ውሳኔም ባለብዙ ወደቦች ባለቤት የነበረችውን አገር ከነጭራሹ ወደብ አልባ አድርጎ አስቀርቷታል።

የባሕር በር ወይም ወደብ ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ወሳኝ ከመሆኑ ባሻገር ፖለቲካዊ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ባለሙያዎች ይናገራሉ። በአሁኑ ወቅት ጂቡቲ ከአራት በላይ ወደቦች አሏት። ይኸች ትንሽ አገር ተፈላጊነቷም ከአውሮፓ እስከ አሜሪካ እንዲሁም ከአሜሪካ እስከ እስያ ድረስ ደርሷል። የተወሰኑ አገሮች ቻይናን ጨምሮ በአሁኑ ወቅት በዚች ትንሽ አገር ወታደራዊ ቤዝ ገንብተዋል። እነዚህ አገሮች ወደዚች ትንሽ አገር መጥተው ወታደራዊ ቤዝ

እንዲኖራቸው ከአስፈለጓቸው ምክንያቶች መካከል የአካባቢው ተፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ እንደሆነም ባለሙያዎች ያብራራሉ ፡፡

በሌላ በኩልም ሳውዲ ዓረቢያ ከአሰብ ወደብ ከፊሉን ከኤርትራ በሊዝ ገዝታ ለብዙ ዓመታት ለማስተዳደር ፈቃድ አግኝታለች፡፡ በአሁኑ ወቅት የአሰብና የምፅዋ ወደቦች የዐረብ አገሮች በተደጋጋሚ ጊዜ ወደዚህ አካባቢ ሲሄዱና ወታደራዊ ሠፈር ሲያቋቁሙ ታይቷል፡፡ የእነዚህ ወደቦች ታሪካዊ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ግን ወደብ አልባ ሆና የበይ ተመልካች ሆና ቀርታለች፡፡

## ወደብ አልባነትና የአለፉት 32 ዓመታት አገራዊ ሽክሞች

በኢትዮጵያና በዐማፅያን መካከል የነበረው የ17 ዓመታቱ ጦርነት ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያን ለዘመናት ትገለገልበት ከነበረው የቀይ ባሕር ይዞታዋ ተነቀለች፡፡ ወደብ አልባ አገርም ሆነች፡፡

ባለፉት 32 ዓመታትም ወደብ አልባ አገር ሆና እና ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ይዞታዋ ከነበረው ከቀይ ባሕር ተገልላ ኖራለች፡፡ በዚህም ወደብ አልባ አገሮች የሚያጋጥማቸውን ፈተና ለመጋፈጥ ተገዳለች፡፡ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ፈተናዎች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የመጀመርያው ኢኮኖሚያዊ ጫና ነው፡፡ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም «አሰብ የማን ናት?» በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንደአሰፈሩት፤ እንደ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆኑ አገሮች ከዋና ዋና የገበያ ማዕከሎች የተገለሉና ከገበያ ማዕከል የራቁ ሲሆኑ ወደብ አልባነት ለኢኮኖሚ ዕድገታቸው ከፍተኛ ማነቆ ሆኖባቸዋል፡፡

ዶክተር ያዕቆብ፤ ቻውድሪና ኤርዳነቢልግ የተባሉ ምሁር የአደረጉትን ጥናት ጠቅሰው እንደጻፉት፤ ወደብ አልባና ወደብ ያለው በሁሉም ነገር ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት አገሮች በኢኮኖሚ ዕድገታቸው ሲነጻጸሩ፤ ወደብ አልባው አገር 1 በመቶ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ወደ ኋላ ይቀራል፡፡ ይህም ማለት ወደብ ያለው አገር ኢኮኖሚውን በእጥፍ ለማሳደግ 24 ዓመታትን ሲፈጅበት፤ ወደብ አልባው አገር ኢኮኖሚውን በእጥፍ ለማሳደግ 36 ዓመታት ይፈጅበታል፡፡ በሌላም በኩል ወደብ አልባ መሆን ብቻ የአንድ አገር የውጭ ንግድ መጠንን ከ33 በመቶ እስከ 43 በመቶ ሊቀንሰው ይችላል፡፡

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪም ሆነ የእርሻ ውጤቶች የሚመረቱት ከወደብ በራቀ አካባቢ በአብዛኛው በመሐሉና በምዕራቡ የሀገሪቱ ክፍል ስለሆነ እነዚህን ምርቶች ወደ ወደቡ ለማዝለቅ ብዙ ወጪ ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ከባድ ዕቃ ለማምረት ለሚፈልግ ኢንቬስተር ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ የመጀመርያ ምርጫ ልትሆን አትችልም፡፡

በዓለም የበለጸጉ ጥቂት ወደብ አልባ ሀገሮች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ አካባቢ ያሉ ሰፋፊ ገበያና የዳበረ ኢኮኖሚን በመጠቀም የወደብ አገልገሎት አለመኖር የሚያስከትለውን ጉዳት መቀነስ ችለዋል፡፡ ሆኖም ወደብ አልባ ሆኖ በዓለም ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን የቻለ አንድም አገር እንደሌለ ዶክተር ያዕቆብ ገልጸዋል፡፡

በአገር ደረጃ ከላይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ወደብ አልባነት ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የቀን ተቀን ኑሮ ጋር ቁርኝት አለው፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ለተከሠተውና በየቀኑ እንደ ሮኬት ለሚወነጨፈው የኑሮ ውድነት አንዱ ምክንያት የወደብ አለመኖር ነው፡፡ በየጊዜው በወደብ ላይ የሚጣለው ታሪፍና ቀረጥ መናር ወደ አገር ውስጥ የሚገባውንና የሚወጣውን ሸቀጥ ዋጋ እንዲንር እያደረገው ይገኛል፡፡ በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ በምትጠቀምበት የጅቡቲ ወደብ ላይ በአንድ ቅጽበት እስከ 25 በመቶ የዋጋ ጭማሪ መደረጉ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ስለ ቀይ ባሕርና ስለ ወደብ አስፈላጊነት በሰጡት ማብራርያም ወደብ የሌላቸው አገሮች ዓመታዊ ዕድገታቸው በ 25 በመቶ የተገታ መሆኑን አስረግጠው መናገራቸው የሚታወስ ነው፡፡

ፖል ኮሊየር የተባሉ ምሁር እንዳሉትም፤ ወደብ አልባ አገሮች ወደ ውጭ የሚልኳቸው ምርቶች በአብዛኛው በአንድና ሁለት ምርቶች ላይ ብቻ የተወሰኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከድህነት የመላቀቅ ዕድላቸው በጣም የመነመነ ነው፡፡ የውጭ ባለሃብቶችም አይመርጧቸውም፡፡ በወደብ ኪራይ እና በትራንስፖርት ምልልስ ለተጨማሪ ወጪ ስለሚዳረጉም ለሸቀጦች ዋጋ መናርና ለኑሮ ውድነት የተጋለጡ ናቸው፡፡

የባሕር በር ያለው አገር ከዓለም ጋር ይገበያያል፡፡ ወደብ የሌለው አገር ግብይቱ ከጎረቤቱ ጋር ብቻ ነው፤ ሲሉም ፖል ኮሊየር ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህም ወደብ አልባ አገሮች የጎረቤቶቻቸው እስረኞች ናቸው፤ ሲሉም ጽፈዋል፡፡

በአጠቃላይ የባሕር በር አለመኖር ለኢኮኖሚና ለልማት ዋነኛ ዕንቅፋት መሆኑን ሁሉም ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ከሆነች ጀምሮም በየቀኑ ለወደብ ኪራይ ከ 3 ሚሊዮን ዶላር በላይ (በዚያን ጊዜ ስሌት) እንደምታወጣ ዶክተር ያዕቆብ ያስረዳሉ፡፡ ይህንኑ ሐቅ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ ለወደብ ኪራይ የሚወጣው ወጪ በርካታ የሕዳሴ ግድቦችን ለመገንባት ያስችለን ነበር፤ ሲሉ በቁጭት መናገራቸው የሚታወስ ነው፡፡

ሌላኛው የወደብ አልባነት ጉዳት ደግሞ ከዲፕሎማሲ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ወደብ የአላቸውና የሌላቸው አገሮች እኩል ተደማጭነት አይኖራቸውም፡፡ ኢትዮጵያም ከቀይ ባሕር ከተወገደች ጀምሮ በዓለም ላይ ያላት ተሰሚነት እየተቀዛቀዘ እንደመጣና በምትኩ ጅቡቲን የመሳሰሉ ትንንሽ አገሮች የበለጠ ተሰሚነትን እያገኙ መምጣታቸውን ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ያስረዳሉ፡፡

ሦስተኛው ችግር ደግሞ፤ ወደብ አልባ አገሮች የሚገጥማቸው የሉዓላዊነት ፈተና ነው፡፡ ወደብ አልባ አገሮች ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል ይቸገራሉ፡፡ የራሳቸውም ምስጢር አይኖራቸውም፡፡ ሰሞኑን ከአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ጋር የቀይ ባሕርና ወደብ ጉዳይን በተመለከተ ቆይታ የአደረጉት በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዶክተር ዳር እስከ ዳር ታዩ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር ከአጣችበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ዋጋ ከፍላለች፡፡

በየዓመቱ ለወደብ ከምታወጣው በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በተጨማሪ ለአገር ስትራቴጂክ የሆኑ ዕቃዎችን ለማስገባት ስትፈልግ የግድ ወደብ የሚያከራየው አገር ማወቅና መፍቀድ አለበት፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ እንደ አገር ምስጢር ነው ብላ የምትደብቀው ነገር አይኖራትም ማለት ነው፡፡ እንደ አገር የምትይዛቸው ምስጢሮቿ ሁሉ በወደብ ሰጪው አገር ዕውቅና ውስጥ የሚያልፉ ናቸው፤ ብለዋል፡፡

ለምሳሌ አስፈላጊ የጦር መሣሪያዎች ኢትዮጵያ ማስገባት ብትፈልግ ከወደቡ ባለቤት ዕውቅና ማግኘት ያስፈልጋታል፡፡ በአጠቃላይ ጉዳቱ ከኢኮኖሚ እስከ ሉዓላዊነት ድረስ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፤ ሲሉ ጉዳቱን አብራርተዋል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያለች ከ120 ሚሊዮን ሕዝብ እና በየጊዜው እያደገ የመጣ ኢኮኖሚ ያላት አገር እነዚህን ሁሉ ችግሮች ተሸክሞ እንደአገር ለመቀጠል ትቸገራለች፡፡ ልቀጥል ብትልም አትችልም፡፡ ባለፉት 30 ዓመታት ስትጓዝበት በነበረው ሁኔታ በአንድ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆና መኖር ከማትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡ ስለዚህም መፍትሔ መፈለጉ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አልሆነም፡፡ ስለዚህም መፍትሔው ምንድነው? የሚለው ጉዳይም ሁሉንም የሚያሳስብ ጥያቄ መሆን ጀምሯል፡፡

የምሥራቅ አፍሪካ ቀጠና በአጠቃላይ 8 አገሮች አሉ። እነዚህ አገሮችም በሚጠቅማቸውቅና በሚያዋጣቸአው አካሄድ ላይ እየተመካከሩ ያለውን ችግር ለመፍታት በቂ ዕውቀትም ችሎታም ያላቸው ናቸው። ኢጋድ መጀመሪያ ሲቋቋም ዓላማው ረኃብንና ድርቅን መቋቋም ነበር። ነገር ግን ይህም ሌላኛው ድርቅ በመሆኑ የተፈጥሮ ሀብታችንን አብረን የምናለማበትን የምንጠቀምበት ሁኔታ ሊመቻች ስለሚገባው ይህንንም አብሮ ማየት ሳያስፈልግ አይቀርም።

ኢትዮጵያም ለጎረቤቶቿ በሙሉ ውሃ ታቀብላለችና ይህንን የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ሂደቷን ደግሞ በባሕር ወደቡ በኩልም በማምጣት ከጎረቤቶቿ ጋር ተስማምታ መጠቀምን ማስቀደም ይገባታል።

## የለውጡ መንግሥት እና የወደብ አማራጭ ትልሞች

ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም፤ «አሰብ የማናት?» በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ከ13 ዓመታት በፊት አንድ ትንቢት የሚመስል ሐሳብ አስፍረው ነበር። «ኢሕአዴግ የአሰብን ጉዳይ ማንሣት ባይፈልግም ከኢሕአዴግ ቀጥሎ የሚመጣው መንግሥት ይህንን ጥያቄ እንደሚያነሣና ኢሕአዴግንም እንደሚወቅስ አምናለሁ።» ሲሉ የዛሬውን አገራዊ ሁኔታ አስቀድመው ተንብየው ነበር።

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ስለቀይ ባሕር እና የወደብ ጉዳይ ገለጻ በማድረግ ኢትዮጵያውያን እንደገና ፊታቸውን ወደ ቀይ ባሕር እንዲያዞሩ ሐሳብ ፈንጥቀዋል። አይነኬ የሚመስለው የቀይ ባሕር እና ወደብ ጉዳይ ቢያንስ የውይይት አጀንዳ እንዲሆን በር ከፍተዋል።

በ2030 ዓ.ም. 150 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በጂኦግራፊ ታሳሪ ሆኖ መኖር የማይችል በመሆኑ መወያየት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል። ከኢትዮጵያ ውሃን የማይወስድ ጎረቤት አገር አለመኖሩን ጠቅሰው፤ ኤርትራ ተከዜን፣ ሱዳን ተከዜን እና ዓባይን፣ ደቡብ ሱዳን ባሮን፣ ኬንያ ኦሞን ጨምሮ፣ ሶማሊያ ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ወንዞችን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል።

ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ በቀይ ባሕር ጉዳይ የማንወያይ ከሆነ በስንዴም፣ በአረንጓዴ ዐሻራም፣ በገቢው ጉዳይ መወያየት ትርጉም የለውም። እንደ አገር የሚታሰበውን ሰላም፣ አንድነትና ብልጽግና በቀይ ባሕር ምክንያት የሚታጣ ከሆነ ዋጋ እንደሌለው ገልጸዋል።

«ለኢትዮጵያ አንድ ሊትር ውሃ የሚሰጥ አገር የለም። ሁሉም ተቀባይ ነው፤ ይገባቸዋል በደንብ አብዝተን እንሰጣቸዋለን። ግን የእናንተን እንካፈል የእኛን እንዳትጠይቁን ማለት ግን ትክክል አይደለም» ብለዋል። አብሮ መኖርና ሰላም ከታሰበ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ በመጋራት መኖር እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው ከአንዱ ወገን ብቻ የሚጠየቅ ከሆነ ፍትሐዊነት የጎደለው ውሳኔ መሆኑን አስረድተዋል።

ስለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩም እንዳሉት፤ በሰጥቶ መቀበል መርሕ ከአካባቢው አገሮች ጋር ቁጭ ብሎ መነጋገር እና ፍላጎትን ማጣጣም ከተቻለ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርጉ በርካታ አማራጮችም አሉ። ወቅቱ የሚጠይቀውም ይህንኑ ትብብር ነው።

ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው በውጭ ጉዳይ ኢንስትቲዩት መሪ ተመራማሪና የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር ጀነራል የሆኑት ዶክተር አማረ ቀናው እንደተናገሩት፤ የባሕር በር ለማግኘት በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል። አንደኛው ሙሉ በሙሉ ከባሕር ጋር የሚያገናኘው ወደብ በባለቤትነት ወይም የራስ የሆነ መሬት ማግኘት ነው። ሁለተኛው ደግሞ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የባሕር በር ተጠቅሞ የአንድን አገር ብሔራዊ ጥቅም ማስጠቅ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ናቸው።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ወደብ የላትም። እየተገለገለች የምትገኘው የሌሎችን ወደብ ተከራይታ ነው። በዚህ መልኩ መቀጠል የሚያስከፍለው መሥዋዕትነት ብዙ ነው። ከዚህም የተነሣ አሁን ጉዳዩ ተነሥቷል። ጥያቄው ቀድሞም ቢሆን ተዳፍኖ በእያንዳንዱ ልብ የተቀመጠ ነው፤ ሲሉ ዶክተሩ ይናገራሉ።

እንደ ዶክተር አማረ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት የምትችለው በቀጣናዊ ትብብር ነው። ለዚህ ደግሞ ኮንፈረንሶችን ማዘጋጀትና በጉዳዮች ላይ መነጋገር መልካም ነው። በተለይም ተፈጥሯዊ የሆነው ይህን ሀብት በእኩልነት እንዴት ማስተዳደር እንችላለን? የሚለውን ለማጠናከር ቀጣናዊ ትብብሮችን በአግባቡ ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

ለዚህም ኢትዮጵያ ሰሞኑን ቀይ ባሕርን እና ወደብን አስመልክቶ የመጀመርያውን ምክክር መድረክ አዘጋጅታለች። አይነኬ ይመስል ስለነበረው የባሕርና ወደብ ጉዳይ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች ጭምር በተገኙበት ግልጽ ውይይት ማድረግ መጀመሩን ዶክተር አማረ ተናግረዋል።

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት መሪ ተመራማሪ እና የኢስያ ፓስፊክ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር ጄኔራል ዶክተር ዳር እስከ ዳር ታዬ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ እያደገ ከሚሄደው የሕዝብ ቁጥሯና ኢኮኖሚዋ ጋር ተያይዞ የባሕር በር ያስፈልጋታል፤ ይላሉ። ከፍ ያለ የሕዝብ ቁጥር ያላት ኢትዮጵያ በአንድ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆና መቀጠል እንደማትችልም ይናገራሉ።፡

እርሳቸው እንደሚያብራሩትም፤ ኢትዮጵያ ከአለፉት 30 ዓመታት ጀምሮ በአንድ ወደብ ላይ ጥገኛ ሆና ዘልቃለች። ይህ ከነበረው የሕዝብ ቁጥርና የኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር ብዙም ተጽዕኖ ሳያመጣ ዛሬ ላይ መድረስ ተችሏል። አሁን ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ጨምሯል። ኢኮኖሚዋም በምሥራቅ አፍሪካ አገራት መካከል ፊተኛውን መሥመር ይዟል። ስለዚህም አሁን ከአለውና በቀጣይ ከሚኖረውም ግዙፍ ኢኮኖሚ አንጻር አንድ ወደብ ብቻ ገቢና ወጪ ዕቃዎችን ሊያስተናግድ አይችልም።

ኢትዮጵያ የባሕር በር ያስፈልጋታል ሲባል ብዙዎች ጉዳዩን ከጦርነት ጋር ያያይዙታል የሚሉት ዶክተር ዳርእስከዳር፤ እንደዚያ ማሰቡ አግባብነት የሌለው መሆኑን ያመለክታሉ። አማራጮቹ በርካታ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ ለአብነት ያህል በኪራይ ተጨማሪ ወደቦችን ማግኘት አሊያም ወደብ በጋራ ማልማት ወይም ደግሞ የአካባቢ ልውውጥ በማድረግ እንደሚቻል ያስረዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ እያከናወነቻቸው ካሉ ልማቶች ውስጥ የተወሰኑትን በመስጠት እና በምትኩ ወደብ በማግኘት ማካካስ ይቻላል፤ ሲሉም ይገልጻሉ። እንዲያም ሲባል ከሕዳሴ ግድብ ተርባይኖች ውስጥ የተወሰኑትን በመስጠት በምትኩ ወደብ ማግኘት ተጠቃሽ እንደሆነ ይናገራሉ።

ለአብነትም ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባሕር በር አላት። ግን ይህ ሁሉ ኪሎ ሜትር ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም። ስለዚህም ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች ወደብ ከኢትዮጵያ ጋር ማልማት ትችላለች። ወይም ደግሞ ለም መሬት ወስዳ በምትኩ ወደብ ልታቀርብልን ትችላለች በሚል በርካታ አማራጮች እንዳሉ ዶክተር ዳር እስከ ዳር ያመለክታሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ ከአሏት የወደብ አማራጮች መካከል በተለይም በቀዳሚነት የአስቀመጡት ዘይላን ሲሆን፤ ዘይላ ወደብ በሶማሌ ላንድ ግዛት በምዕራባዊ አውደል ግዛት ውስጥ የሚገኝ እና የኤደን ባሕረ ሰላጤን መሠረት ያደረገ እንደሆነ ተናግረዋል። በሁለተኛ አማራጭ ነው ያሉት የጂቡቲ ወደብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኤርትራ የሚገኘው የአዱሊስ ወደብንም ጠቅሰዋል።

**ኢትዮጵያ በቀይባሕር ላይ ነግሣ በቆየችባቸው ወቅቶች የበርካታ ወደቦች ባለቤት ነበረች። ከእነዚህ ውስጥ በዋነኛነት አዶሊስ፤ ምጽዋ፤ አሰብ፤ ዘይላ ተጠቃሾች ናቸው።**

ኢትዮጵያ የምትፈልጋቸውንና የሚያመቻትን የወድብ አማራጮችን ብቻ አልዘረዘሩም። በምትኩ ደግሞ ኢትዮጵያ ወደብን ለማግኘት በምላሹ ከሕዳሴ ግድብ፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲሁም ከኢትዮ-ቴሌኮም ድርሻ ለመስጠት ፍላጎት እንዳላትም አብራርተዋል።

ዶክተር ዳር እስከ ዳር ታዬ በአሁኑ ወቅት የቀይ ባሕርና የወደብ ጉዳይ መነሣቱ ወቅታዊ ከመሆኑም ባሻገር የለውጡ መንግሥት አንዱ ገጸ በረከት መሆኑን ያስረዳሉ።

የለውጡ መንግሥት ሠራቸው ብዬ ከማስባቸው ታላላቅ አገራዊ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ላይ የነበራትን ተሰሚነት ለማስመለስ እያደረገው ያለው ጥረትን ነው። ኢትዮጵያ ኢፍትሐዊ በሆነ መልኩ ከቀይ ባሕር እንድትርቅ ተደርጋለች። ይህ ደግሞ እንደ አገር የሚያስቆጭና የሚያንገበግብ ነው።

የለውጡ መንግሥት ይኸንኑ በመረዳት አይነኬ የሚመስለውን የቀይ ባሕር ፖለቲካን ቢያንስ በአሁን ደረጃ የመወያያ አጀንዳ ማድረግ ችሏል። ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠንም ኢትዮጵያ ወደ ቀይ ባሕር መመለሷ አይቀርም። ከአምስት ዓመታት በፊት እኮ ስለ ባሕር በር ማውራት እንደተስፋፊነት እና ጠብ ጫሪነት ነበር የሚቆጠረው። ስለቀይ ባሕር ማውራት ራስን ለጦርነት እንደማዘጋጀት፤ ጦርነትን እንደመቆስቆስ ነበር የሚታሰበው።

ዘይላ ሶማሊያ እንደአገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባሕር በር ነው። ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች። ለኢትዮጵያ ቅርበት አለው። ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት አትችልም። ስለዚህም መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበትና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም አገሮች አሸናፊ መሆን ይችላሉ።

በተመሳሳይም ከኤርትራ ጋር በተፈጠረው መልካም የሰላም አጋጣሚ የአሰብን ወደብ በሰላማዊ አማራጭ ለመጠቀም ውይይት ማድረግ ይቻላል። ኤርትራ ከኢትዮጵያ የምትፈልጋቸው አቅርቦቶች ይኖራሉ፤ እነሱን በመስጠት አሰብን መጠቀም ይቻላል።

ወደ ሶማሌ ላንድ ስንመጣ የበርበራ ወደብን በጋራ ማልማትና መጠቀም ይቻላል። ከዚህ ቀደም የኢምሬት መንግሥት 51 በመቶ፣ የሶማሊ ላንድ አስተዳደር 30 በመቶ እና የኢትዮጵያ መንግሥት 19 በመቶ ድርሻ ወደቡን በጋራ የማልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። ይህ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚችል ነው።

በአጠቃላይ ግን የኢትዮጵያ ማደግ ለጎረቤት አገሮች ዕድል ይዞ የሚመጣ ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እያደገ ሲመጣ ተጨማሪ ወደቦች ያስፈልጓታል። ጎረቤት አገሮችም ወደቦችን በማከራየት፣ በጋራ በማልማት ወይም ከኢትዮጵያ በሰጥቶ መቀበል መርሕ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በማግኘት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

ሆኖም በአሁኑ ወቅት 120 ሚሊዮን ሕዝብ በ2050 አካባቢ ደግሞ በእጥፍ የሚያድግ ሕዝብ ተይዞ "ስለቀይ ባሕር እና ስለ ወደብ ኣታንሣ፤ ዝም ብለህ ተቀመጥ" የሚል አፋኝ አመለካከት ሊኖር አይገባም።

ኢትዮጵያ ወደብ ያስፈልጋታል። ወደብ ለማግኘትም በርካታ አማራጮች አሏት። በእነዚህ አማራጮች ላይ ግን መነጋገር፣ መወያየትና መግባባት ያስፈልጋል። መፍትሔው ቀጣናዊ ትብብር ነው። እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን በእኩልነት እንዴት ማስተዳደር እንችላለን? የሚለውን ለማጠናከር ትብብርን በአግባቡ ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

በተለይም ዶክተር አማረ እንደሚሉት፤ የትብብር ማሕቀፎችን ዲዛይን ማድረግ ያስፈልጋል። ተጠቃሚነትም መኖር አለበት። ጉዳዩ ገና ሲነሣ «ውሃችንን ልትወስዱ ነው» ከመባባል በአለፈ የጋራ ተጠቃሚነታችንን ጉዳይ እንዴት አድርገን ማጠናከር አለብን? በሚለው ላይ መወያየት መልካም ነው።

የጋራ ተጠቃሚነት ከሌለ ግጭቶች ይኖራሉ። ይህ ደግሞ ከቀጣናው ውጭ ያሉትን አካላት ተጠቃሚ ያደርጋል። በውክልናም በመግባት መንግሥት እስከመመሥረት ያደርሳል። ስለሆነም ይህንን ጉዳይ ሁሉ ለመቆጣጣር ቀጣናዊ ትብብር ወሳኝ ነው። ከማጠናከር አኳያ ሲታይ ደግሞ ከዚህ በፊት ጠንካራ ሚና ስትጫወት የነበረች ኢትዮጵያ ተነሣሽነቱን ወስዳ ቀጣናዊ ትስስሩ እንዲጎለብት የማድረግ ብቃት ያላት ናት ይላሉ።

ኢትዮጵያ በቅርቡ የመጀመሪያው የቀይ ባሕር የትብብር መድረክ ነው። ቀጣዩ ኢትዮጵያ ውስጥ አሊያም የተባበሩት ዐረብ ኢመሬቶች ውስጥ አሊያም እስራኤል ወይም ደግሞ ሳውዲ ዐረቢያ ውስጥ ሊካኼድ ይችላል። ዋናው ነገር ግን ጀማሪዎቹ እኛ ነን። ተነሣሽነቱን ወስደናል፤ መድረኩ በዚህ ሁኔታ ቀጥሎ ፖሊሲ አውጪዎች ላይ ጫና ማድረግ አለብን። ወደ ጋራ ተጠቃሚነትና ወደ ጋራ ድል የሚወስደውን መንገድ ለመጓዝ እንሞክራለን።

ለዓመታት ተዳፍኖ የቆየው የባሕር በርና ወደብ ጉዳይ መነሣት መጀመሩ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ስሜት መፍጠር ጀምሯል። ከዚህ አልፎም አንዳንድ የውጭ ምሁራንና ፖለቲከኞች ጭምር ኢትዮጵያ የአነሣችውን የፍትሐዊነት ጥያቄ መደገፍ ጀምረዋል። ሰሞኑን አሜሪካዊው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ተንታኝ ላውረንስ ፍሪማን የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ በአዎንታዊ መልኩ ሊያዩት እንደሚገባ መናገራቸው የዚሁ እሳቤ አንዱ መሳያ ነው።

ሎረንስ ፍሪማን የኢትዮጵያ የባሕር በሮችን የመጠቀም ፍላጎትና መሻት ተገቢነት ያለውና የአፍሪካ ቀንድ ሕዝብ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለመጨመር አስተዋፅኦ አለው፤ ሲሉም ገልጸዋል። የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ በአዎንታዊ መልኩ መገንዘብ አለባቸው፤ ሲሉም ተናግረዋል።

# ፌውስ ፌላጊው የትምህርቱ ዘርፍ

ወንድወሰን ሽመልስ

## መነሻ ሐሳብ

“ትምህርት የዕውቀት መሠረት ነው” ይሉት ተለምዷዊ ብሂል፤ ከይትበሃልነት ባሻገር የትምህርትን የዕውቀት መሠረትነት መግለጥ ከአልቻለ የንግግር ማድመቂያ ከመሆን የዘለለ ረብ አይኖረውም። ለዚህ ማረጋገጫ ሊሆን የሚችል ዐቢይ ማሳያ ከአስፈለገ ደግሞ ተምረው ያወቁ፤ አስተምረውም ያሳወቁ ማኅበረሰቦች እና አገሮች ዛሬ ላይ በዓለማችን በምን መልኩ ተገልጠዋል? ተገኝተዋል? የሚለውን ጠይቆ ለመረዳት መሞከር በቂ ነው።

ትምህርት የዕውቀት መሠረት የሆናቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች/ሀገራት ማወቃቸው ለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችም ጉዳዮቻቸው መፍትሔ የማፍለቅ ልዕልናን ሲያጎናጽፋቸው ተመልክተናል። ስለዐወቁ የሳይንስም፣ የቴክኖሎጂም፣ የሥነ ፈለግም፣ የሥነ ጥበብም፣ የመድኃኒትም፣ የምሕንድስናም፣... ጥበብን መጎናጸፍ ችለው፤ ከራሳቸው የአለፈ ሌሎች የአእምሮ ፍሬያቸው ተቋዳሽ የሚሆኑበትን ዕድል ፈጥረዋል።

በዚህ ረገድ እነ አሜሪካና የአውሮፓ አገሮችን የሥልጣኔና የመበልጸግ ከፍታ መመልከቱ ዕውቀት በሁሉም መስክ ከፊት የሚያሰልፍ መሆኑን ለመገንዘብ ያግዛል። በተመሳሳይ በቅርብ ዓመታት ከነበሩበት የድህነት አረንቋ ወጥተው ከፍተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ላይ የደረሱ ደቡብ ኮሪያ፣ ቻይና፣ ሲንጋፖር፣ ቬትናም፣ ማሌዢያ እና ሌሎችም በፈጣን የዕድገት መንገዳቸው የሚገለጹ አገሮችን ማየት ጠቃሚ ነው። እነዚህ አገሮች ለትምህርትና ሥልጠና በሰጡት ትኩረት የሰው ሀብታቸውን በከፍተኛ ደረጃ በማልማት የሕዝባቸውን ኑሮ ማሻሻል እንደቻሉ ለመረዳት ያስችላል።

ቀድመው የበለጸጉትም ሆነ ዘግይተው ወደ ብልጽግናው ጎዳና ገብተው የሁለንተናዊ ብልጽግና ጉዞ ምጣኔያቸውን የአፋጠኑ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው፤ ትምህርት ምን ያህል በማኅበራዊ ጉዳያቸው፤ በፖለቲካ ንቃተ ኅሊናቸው፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መንገዳቸው ዐቅም እንደሆናቸው ነው። ምክንያቱም በተማሩ ዐውቀዋል፤ በዐወቁ ተመራምረዋል፤ በተመራመሩም መፍጠር ችለዋል። ብቁና በቂ የመፍጠር ዐቅም ያለው ዜጋ ማፍራታቸው ሰፊውን ሕዝባዊ እና አገራዊ ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ፤ የደኅንነት ስጋታቸውን ለማቃለል፤ የኃይል ሚዛናቸውን ለማስጠበቅ እና በሁሉም መስክ ቀድመው ለመገኘት አስችሏቸዋል።

“
አገሮች ብቁና በቂ የመፍጠር ዐቅም ያለው ዜጋ ማፍራታቸው ሰፊውን ሕዝባዊ እና አገራዊ ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ፤ የደኅንነት ስጋታቸውን ለማቃለል፤ የኃይል ሚዛናቸውን ለማስጠበቅ እና በሁሉም መስክ ቀድመው ለመገኘት አስችሏቸዋል፤

አገራችን ኢትዮጵያም የዜጎችን የዕውቀት አድማስ ለማስፋት ዘመናዊውን የትምህርት ሥርዓት ዘርግታ፣ ትምህርት ቤት ገንብታ ማስተማር ከጀመረች ከምዕተ ዓመት የዘለለ ዕድሜን አስቆጥራለች። ቀደም ሲል በቤተ እምነቶች ሲሰጥ የነበረውን የፊደል ቆጠራ ሂደት ከፍ ወዳለ ደረጃ ያሸጋግረዋል ተብሎ የተተገበረው ዘመናዊው ትምህርትም አንቱታን የአተረፉ ዐዋቂዎችን ማፍራትም የተቻለበት ዕድል ተፈጥሯል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ከትናንት እስከ ዛሬ አንድም ስለ ትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት፤ ሁለተኛም፣ በትምህርት ጥራትና ተገቢነት ላይ የሚሰነዘሩ ስል ትችቶች አልጠፋም። ይኼም በቀደምት ሥርዓቶች በተደራሽነት፣ በቅርቦቹ ሥርዓቶች ደግሞ በጥራት ላይ አመዝነው የሚሰነዘሩ ሐሳቦች የበረቱበት ነው። የእነዚህን ሐሳቦችና ትችቶች ምክንያትም ሆነ ጭብጥ ለመረዳት ታዲያ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ከትምህርት ጥራትና ተደራሽነት አኳያ ከየት ተነሥቶ ወደየት የደረሰ ነው? የሚለውን ቀድሞ በወፍ በረር መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል።

### የትምህርት ጥራት እና ተደራሽነት ከየት ወደ የት?

በኢትዮጵያ ምንም እንኳን ቀለም በጥብጦ፣ ብራና ዳምጦ፣ ፊደል ቀርጾ፣ ማስቆጠር የተጀመረበት ዘመን ከሩቅ የሚጠቀስ ቢሆንም፤ “ዘመናዊ ትምህርት” የተጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ስለመሆኑ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎች ያስረዳሉ። በወቅቱ የነበረው የትምህርት ዓላማም

በጅምር ደረጃ የነበረውን ፊውዳላዊ ቢሮክራሲ የሚያገለግልና በተለይ በአስተርጓሚነት የሚሠራ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፈራት እንደነበርም ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት።

በወቅቱም ሥርዓተ ትምህርቱም ከውጭ የተቀዳ፣ መምህራኑም የውጭ ዜጎች ነበሩ። በሒደትም ሥርዓተ ትምህርቶቹ በአገር ውስጥ እንዲቀረጹ ቢደረግም፣ ከውጭ ተጽዕኖ ሙሉ በሙሉ ተላቅቀው የሀገሪቱን ችግር የሚፈታ ተደራሽነት፣ ተገቢነት፣ ፍትሐዊነትና ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓት ሊዘረጋ አልተቻለም። ይኸንንም ለትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ዝግጅት ሲባል "የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች" በሚል ርእስ በ2010 ዓ.ም. በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ጊዜያዊ የሴክቴሪያት ጽ/ቤት የተከናወነ ጥናት ሰነድ ያመለክታል።

በዚህ ሰነድ ላይ እንደተመለከተው፤ እስከ ንጉሣውያን ዘመን ማብቂያ ድረስ የነበረው የትምህርት ተደራሽነት ውስን ሲሆን፤ ትምህርት ቤቶችም በዋና ዋና ከተማ ብቻ ነበር የሚገኙት። ሴቶች፣ ልዩ ፍላጎት የአላቸውና አርብቶ አደር ዜጎች ደግሞ የዕድሉ ተቋዳሽ አልነበሩም።

ከትምህርት ተገቢነትና ጥራት አኳያ ሲታይም በወቅቱ ከ85 በመቶ በላይ የነበረውና በግብርና የሚተዳደረውን ሕዝብ ግብርናውን በማዘመን የኑሮ ደረጃውን አላሻሻለም። በደርግ ዘመንም ቢሆን ተደራሽነቱ እምብዛም አይደለም። በመሆኑም በእነዚህ ጊዜያት የነበረው የትምህርት ሥርዓት የሀገሪቱን ትምህርት ከተደራሽነት፣ ከፍትሐዊነት፣ ከተገቢነትና ከጥራት ችግሮች ሊያላቅቅ አልቻለም።

በአንጻሩ ከ1983ቱ የሥርዓት ለውጥ በኋላ፣ በ1986 ዓ.ም. የተቀረጸው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መነሻ በማድረግ በተሠሩ ሥራዎችም ውጤት ማግኘት እንደተቻለ መረጃው አመላክቷል። ለዚህም የትምህርት ተሳትፎን፣ ፍትሐዊነትና ጥራትን በማስጠበቅ በኩል የትምህርት አመራሩንና አደረጃጀቱን በወሳኝነት በሕዝብ ተሳትፎ እንዲመራ ሥርዓት በመዘርጋት እንዲለወጥ መደረጉን ይጠቅሳል።

ከሥርዓት ለውጡ በፊት በመላው አገሪቱ አራት ሺሕ በሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃና 278 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፤ በአጠቃላይ ከሁለት ሚሊዮን የአልበለጡ ተማሪዎች ብቻ ይማሩ እንደነበር ሰነዱ በአብነት ጠቅሷል። ይኼም ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በዝቅተኛ የትምህርት ተሳትፎ ከሚጠቀሱ አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ የአደረጋት እንደነበር ያትታል።

በአንጻሩ ከ1983ቱ የሥርዓት ለውጥ በኋላ፣ በ1986 ዓ.ም. የተቀረጸው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መነሻ በማድረግ በተሠሩ ሥራዎችም ውጤት ማግኘት እንደተቻለ መረጃው አመላክቷል።



ዶክተር ፍርዲሳ ጀቤሳ

ሆኖም ከሥርዓት ለውጡ ማግስት በተሠሩ ሥራዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በሁሉም የአገሪቷ አካባቢዎች ለማዳረስ መቻሉን፤ በዚህም ከ28 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን እያስተማሩ ያሉ ከ39 ሺሕ በላይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና ሦስት ሺሕ 300 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመንግሥት ተደራሽ ማድረግ እንደተቻለ በሰነዱ ተገልጿል።

በተመሳሳይ መልኩ በጥቂት ተቋማትና የትምህርት ፕሮግራሞች ተወስኖ የነበረውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተደራሽነት ከሁለት ወደ 46 ማሳደግ ተችሏል። ወደ 130 የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል። ይሄም ከፍተኛ የሆነ የሠለጠነ የሰው ሀብት በማፍራት ለአገራዊ ዕድገቱ መሣለጥ ጉልህ ድርሻ አድርጓል።

የትምህርት ጥራት እና ተደራሽነትን በተመለከተ ከዚህ ሰነድ በተጨማሪ፣ በትምህርት ሚኒስቴር ከ2008 - 2012 ዓ.ም. እንዲተገበር በተዘጋጀው አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ ግብር ሰነድ፤ ከ2013 - 2022 ዓ.ም. እንዲተገበር በተዘጋጀው የዓሥር ዓመት የልማት ዕቅድ ሰነድ፤ እንዲሁም በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ሰነድ ላይም ተመሳሳይ ሐሳቦች ናቸው የተጠቀሱት።

ሁሉም ሰነዶች ላይ ከ1983 ዓ.ም. የሥርዓት ለውጥ በፊት የትምህርት ተደራሽነት እምብዛም አለመሆኑን፤ ከ1986ቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መቀረጽ በኋላ በተሠራው ሥራ ግን የትምህርት ተደራሽነትን እና ፍትሐዊነትን ከማረጋገጥ አኳያ ብዙ ውጤት የተገኘበት ስለመሆኑ ያብራራሉ።

በዚህ መልኩ የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ላይ አበረታች ሥራ የተሠራ መሆኑን የሚጠቅሱት እነዚህ ሰነዶች፤ ከዚህ በተቃራኒው ግን የትምህርት ጥራት ጉዳይ ብዙ ችግር የአለበት ስለመሆኑ ነው የሚያትቱት። ለምሳሌ፣ በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ሰነድ ላይ እንደተመለከተው፤ በ1986 ዓ.ም. ተቀርጾ ሲተገበር የቆየው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ የትምህርት ተደራሽነትንና ፍትሐዊነትን በማረጋገጥ በኩል ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም፤ የትምህርት ጥራትን ግን ማረጋገጥ አልቻለም።

ይልቁንም በእነዚህ ዓመታት የትምህርት ጥራት እያሽቆለቆለ የመጣ ሲሆን፤ በየደረጃው ያለው አብዛኛው ተማሪ የትምህርት ውጤት በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን 50 በመቶና በላይ ውጤት መሆን አለመቻሉ ለትምህርት ጥራቱ ማሽቆልቆል እንደ ማሳያ ተደርጎ ነው በሰነዶቹ የተጠቀሰው።

በዚህ መልኩ ለትምህርት ጥራት መውረድ እና ውጤት ማሽቆልቆል እንደ ምክንያት ሆነው በሰነዱ ከተጠቀሱ ጉዳዮች መካከል፤ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በንድፈ ሐሳብ የታጨቀ እና ለተግባር ትምህርት ተገቢውን ትኩረት የአልሰጠ መሆኑ አንዱ ነው። በቴክኖሎጂ የተደገፈ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርትም ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ሆኖ በሰነዶቹ ቀርቧል። ይኼም ከውጤት ማሽቆልቆል በተጓዳኝ ከኢንዱስትሪው ጋር የተሳሰረና የአገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ የአገናዘበ ትምህርትና ሥልጠና አለመተግበሩ፤ ሠልጥነውና ተመርቀው የወጡ ዜጎች የሥራ ፈጣሪ መሆን አለመቻላቸውም ተመላክቷል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም ተባባሪ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶክተር ፍርዲሳ ጀቤሳ፣ ከትምህርት ጥራትም ተደራሽነትም አኳያ በሰነዶቹ የተመለከቱትን ሐሳቦች ይጋራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ቀደም ባሉት ሥርዓቶች የትምህርት ተቋማት ቁጥርም፤ ተደራሽነታቸውም ትንሽ ነው፤ የቅበላ ዐቅማቸው እና ተሳታፊዎችም ትንሽ ነበር።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የትምህርት ተቋማት ቁጥር በእጅጉ አድጓል። የተማሪዎች ቁጥምር ሆነ የመምህራን ብዛት ጨምሯል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ተደራሽነቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው። ይሄ ተደራሽነት ደግሞ ከፍትሐዊነት አኳያም የሚታይ ሲሆን፤ ቀደም ሲል በተወሰኑ ቦታዎች ተገድቦ የነበረው ትምህርት አሁን ወደ ሕብረተሰቡ ሁሉ ደርሷል። በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ እና በየኒቨርሲቲም ደረጃ ተደራሽነቱ በጥሩ ሁኔታ ነው ያለው።

ይሁን እንጂ፣ በዚህ መልኩ ተደራሽነቱ እያደገ ሲሄድ፤ ይሄንን ተደራሽነት የመጠነ/ ማዕከል ያደረገ ለትምህርት አስፈላጊ የሆነ ግብዓት(ሪሶርስ)ን ከማሟላት አኳያ እጥረት አለ። ትምህርት ደግሞ ግብዓት ይፈልጋል። ግብዓት ሲያጥር ደግሞ የትምህርት ጥራት ላይ የራሱን አሉታዊ ጫና ያሳድራል። ከዚህ አኳያ የተሠራው ሥራ በተደራሽነት ጥሩ ቢሆንም፤ በጥራት ግን ተጎድቷል።

በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻያ ዴስክ ሐላፊ አቶ ታዬ ግርማ በዚህ ሐሳብ ይስማማሉ። አቶ ታዬ እንደሚሉት፤ ባለፉት ሁለትና ሦስት ዐሥርት ዓመታት፣ ለትምህርት ተደራሽነትም ሆነ ጥራት በተሠሩ ሰፋፊ ሥራዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በሁሉም ቦታ ማዳረስ፤ በዚህ ደረጃ ያለው ጥቅል ተሳትፎም ወደ 98 በመቶ ማሳደግ ተችሏል። በዚህ ረገድ በአለፉት ዓመታት ሲሠራ የነበረው ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ማምጣት ላይ ነው። በዚህም ብዙ የተሠራ ሲሆን፤ ከቁጥር አኳያም ትምህርት ቤቶች የመንግሥትና የግሉን ጨምሮ ከ56 ሺሕ በላይ ደርሰዋል።

በዚህ መልኩ በጥቅል ተደራሽነቱ ሲታይ ጥሩ ደረጃ ላይ ነው ቢባልም፤ ተደራሽነቱ ጥራትን በሚያረጋግጥ መልኩ ነው ወይ? የሚለው ሲታይ፤ መልሱ አይደለም ነው። አንድ ትምህርት ቤት ሲገነባ/ሲከፈት ምን ምን ነገሮችን ማሟላት አለበት? የሚለው ታሳቢ አልተደረገም። ተደራሽነቱ ላይ ሲሠራ፤ አንደኛ፣ ትምህርት ቤቶቹ ደረጃቸውን (ስታንዳርዳቸውን) ጠብቀው አይደለም የተሠሩት። ምክንያቱም በወቅቱ በሕብረተሰቡ ፍላጎት እንዲሁም በፖለቲካው ጫና የተነሣ ብቻ ደረጃውን በአልጠበቀ ሁኔታ በዘፈቀደ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶች ብዙ ናቸው።

ለምሳሌ፣ ትምህርት ቤቶቹ ሲሠሩ የግብዓት ደረጃ (ስታንዳርድ) አሟልተው አይደለም። ተማሪዎች የሚማሩበት ክፍል ብቻ በመገንባት የተከፈቱ ትምህርት ቤቶች አሉ። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ግን በቂ መቀመጫ እንኳን የሌላቸው፤ ጥቁር ሰሌዳ የሌላቸው፤ ቤተ ሙከራ እና ቤተ መጻሕፍት የሌላቸው፤ ውሃ እና መጸዳጃ ቤት የሌላቸው፤ የልጆች መጫወቻ ሜዳ የሌላቸው ናቸው።

በዚህ በኩል፣ በተደረገ የፍተሻ ሥራ ከአሉት ከ56 ሺሕ በላይ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ86 በመቶ በላዩ ከደረጃ በታች ናቸው። ይሄ ማለት ደግሞ ለመማር ማስተማር ሥራ ብቁ አይደሉም። በዚህ መልኩ ደረጃውን በአልጠበቀ ሁኔታ (ያለ ስታንዳርድ) ለማዳረስ ሲባል የተከፈቱ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት ሳያገኙ እንዲቀሩ ስለሚያደርጉ ለትምህርት ጥራት መጓደል የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

## ታዲያ በኢትዮጵያ ትምህርት ወድቋል?

በትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ላይ ታየ የተባለው ውጤት ከጥራት አኳያ በተቃርኖ መንገድ መገለጹ፣ እንደ አገር የትምህርት ጥራት እንዲወርድ ማድረጉን መረጃዎችም፣ የዘርፉ ባለሙያዎችም ይናገራሉ። ይኼ የትምህርት ጥራት ችግር ከፍ ብሎ መታየት ደግሞ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው የሚገባቸውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ይዘው እንዲወጡ እያደረጋቸው አይደለም።

ይሄ ያለመሆኑ ማሳያ ደግሞ የተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል፤ እንዲሁም ሠልጥነውና ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በገበያው ላይ ተወዳዳሪ ያለመሆን፤ አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን ያለማፍለቅ ችግር አሳድሮባቸዋል። አሁን በአለው ሁኔታም ትምህርት የሚጠበቅበትን ግብ መምታት በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ገብቷል፤ ወይንም ወድቋል። ይኼም የትምህርት ጥራት ችግሩም ወደ ትምህርት ሥርዓቱ ውድቀት መሸጋገሩን ማሳያ ነው፤ ሲሉ የሚከራከሩ አካላትም ተፈጥረዋል።

በእርግጥ የትምህርትና ሥልጠና ሂደቱ በርካታ የሰው ኃይል አስተምሮ ማስመረቅ የተቻለበት ቢሆንም፤ ተምረውና ሠልጥነው የሚወጡ ዜጎች የሚፈለገውን ዐቅም መፍጠር አልቻሉም። ይሄ በመሆኑም በቂና ተገቢ የሰው ኃይል ለገበያው ማቅረብ አለመቻሉን፤ ሰልጥነውና ተመርቀው የወጡ ዜጎችም ቢሆኑ ሥራ ፈጣሪ መሆን አለመቻላቸውን በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ላይም በግልጽ ተመላክቷል። ትልቁ ጉዳይ ግን በዚህ መልኩ የሚገለጸው የትምህርት ጥራት ችግር በኢትዮጵያ ትምህርት ወድቋል በሚያስብል ደረጃ ላይ ነውን? የሚለው ጉዳይ ነው።

ይኸንን በተመለከተ አቶ ታዬ እንደሚናገሩት፤ ለትምህርት ጥራት መጓደል ብዙ ማሳያዎች አሉ። ዋናው ጉዳይ ግን አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት የሚያገኛቸው ነገሮች በዕውቀቱ፣ በክህሎቱ፣ በአመለካከትና አስተሳሰቡ ምን ለውጥ አመጡለት? የሚለው ነው። ምክንያቱም ይኼ ተማሪ በትምህርት ቤት ቆይታው በዚህ ረገድ ማግኘት የሚገባውን ነገር ከአልተሰጠው ትምህርት ወድቋል ማለት ነው።



በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻያ ዴስክ ሐላፊ አቶ ታዬ ግርማ

ሆኖም ትምህርት ወድቋል ወይም የትምህርት ጥራት ችግር አጋጥሟል ስንል በደፈናው ሳይሆን፤ የቱጋ ነው ችግሩ የተፈጠረው የሚለውን መለየት ያስፈልጋል። አንዱ መለኪያው፣ የትምህርት ቤቶች ደረጃ (ስታንዳርድ) ነው። በዚህ በኩል፣ ከ86 በመቶ በላይ ትምህርት ቤቶቻችን ከደረጃ በታች ናቸው።

ከትምህርት ቤቶች ደረጃ (ስታንዳርድ) ችግር ባለፈ፤ በቂ ዝግጅት ያላቸው በቂ መምህራን ሳይኖራቸው የተከፈቱ በርካታ ትምህርት ቤቶች አሉ። በተመሳሳይ በአንድ ክፍል ውስጥ ከደረጃው (ስታንዳርዱ) በላይ የተማሪ ቁጥር እንዲማር ይደረጋል። ለምሳሌ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስታንዳርዱ በክፍል 40 ተማሪ ቢሆንም፤ እስከ 120 ተማሪ ተቀምጦ ይማራል። ይሄ ደግሞ መምህራን እንደየተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ችሎታ ተማሪዎችን እንዳያግዙና እንዳያበቁ ያደርጋል።

የመጻሕፍት አቅርቦት ችግር፤ መምህራንም የትምህርት ካሪኩለሙን ተረድቶ ከማስተማር አኳያ ያለ ክፍተት፤ የትምህርት አመራሩ በአግባቡ ሥራው ላይ ያለማተኮር ድክመት፤ ወላጆች ከትምህርት ቤቶች ጋር ያላቸው ቁርኝትና ልጆቻቸውን የመከታተል ጉዳይ፤ የትምህርት አመራሩ ኢንስትራክሽናል ሊደር ሺፕ ያለመሆን፤ የተማሪዎች ለመማር ፍላጎት ማጣት፤ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች፣ የሰላምና ጸጥታ ችግር፤ በትምህርት ቤቶች የሚንጸባረቀው የፖለቲካ አመለካከት፤... የመሳሰሉ ጉዳዮች ለትምህርት ጥራት መጓደል የየራሳቸው አበርክቶ አላቸው።

ጥራት አመራር ይጠይቃል። በየደረጃው (ከትምህርት ቤት እስከ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት) ያለው መሪ ጥራትን ከአልመራ ለጉዳዩ ማንም ትኩረት አይሰጠውም። ሥራው ሪፖርት ብቻ ሆኖ ይቀራል። ... በምርምር እንደታየውም 85 ከመቶው የአመራሩ ጊዜ እሳት በማጥፋት ላይ ነው የሚባክነው። ስብሰባዎች ላይ፣ ሪፖርቶች ላይ፣ ዕቅዶች ላይ ነው የሚያተኩረው እንጂ ጥራትን መምራት ላይ አይደለም፤

እንደ አቶ ታዬ ማብራሪያ፤ በእነዚህና መሰል ምክንያቶች የትምህርት ጥራት ችግር ተፈጥሯል፤ የተማሪዎች ውጤት አሽቆልቁሏል። ይሄ ማለት ግን ትምህርት ፈጽሞ ወድቋል ማለት አይደለም። ምክንያቱም ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም፣ ዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሆኑ ሰዎችን ማፍራትም፤ ማግኘትም ተችሏል። እነዚህን የፈጠረው ደግሞ ይኼው የትምህርት ሥርዓት ነው። ይሄ የሚያሳየው ደግሞ መሥራት የሚገባውን ባለመሥራት የተፈጠረ የትምህርት ጥራት መጓደሉን እንጂ ትምህርትም ሆነ የትምህርት ሥርዓቱ መውደቁን አይደለም።

ይኼው የአቶ ታዬ ገለጻ በዶክተር ፍርዲሳ ማብራሪያም ተቀባይነት አለው። እርሳቸው እንደሚሉትም፤ ትምህርት ለአንድ ዓላማ፣ ግብና ራእይ ነው የሚሰጠው። ይኼም ተማሪዎች ሠልጥነው ለአገር አገልግሎት እንዲበቁ ማስቻል ነው። ሆኖም ተማሪዎች በትምህርት ቆይታቸው ለዚህ ደረጃ ካልበቁ (በዕውቀታቸው፣ በክህሎትና በአመለካከታቸው) እና የታሰበው ቦታ ሳይውሉ ሲቀር ትምህርት ወድቋል ማለት ይቻላል።

በዚህ ረገድ ትምህርት በሚባለው ልክ አልወደቀም ሊያስብሉ የሚችሉ ነገሮች አሉ። ምክንያቱም ዜጎች የመማርና ራሳቸውን የማብቃት፣ ተገቢውን ዕውቀትና ክህሎት የማግኘት፣ ራሳቸውንም ለሥራ የማዘጋጀት ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። ስለዚህ እስከአሁን ካለው ሁኔታ አኳያ በትምህርት ሙሉ በሙሉ ወድቀናል ለማለት አይቻልም።

ይህ ሲባል ክፍተቶች የሉም ማለት አይደለም። ክፍተቶቹ ደግሞ ከሥርዓተ ትምህርቱ ብቻ የመነጩ አይደሉም። ይልቁንም ከአተገባበር የሚመነጩ ክፍተቶች ናቸው። እስከአሁንም ድረስ የአልተፈታ የትምህርት አመራር ክፍተት አለ። ምክንያቱም የትምህርት አመራር በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው ለፖለቲካዊ አስተዳደሩ ነው። ሙያው ላይ አተኩሮ የሚሠራ አመራር (ኢንስትራክሽናል ሊደርሺፕ) አልተተገበረም።

እንደ ዶክተር ፍርዲሳ ገለጻ፤ ጥራት አመራር ይጠይቃል። በየደረጃው (ከትምህርት ቤት እስከ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት) ያለው መሪ ጥራትን ከአልመራ ለጉዳዩ ማንም ትኩረት አይሰጠውም። ሥራው ሪፖርት ብቻ ሆኖ ይቀራል። ስለዚህ ለትምህርት ጥራት ችግር መፈጠር አንዱና ትልቁ ክፍተት እዚህ ላይ ነው። በምርምር እንደታየውም 85 ከመቶው የአመራሩ ጊዜ እሳት በማጥፋት ላይ ነው የሚባክነው። ስብሰባዎች ላይ፣ ሪፖርቶች ላይ፣ ዕቅዶች ላይ ነው የሚያተኩረው እንጂ ጥራትን መምራት ላይ አይደለም።

ኢንስትራክሽናል ሊደርሺፕ ሲባል፤ በትምህርት

ይዘቶች ላይ ዕውቀት ያለው፣ሐሳብና አስተያየት የሚሰጥ፤ ድጋፍ የሚሰጥ፣ ስሕተት ካለም የሚተችና የሚያርም ማለት ነው። ምክንያቱም የትምህርቱ ሂደት ድጋፍ የሚሰጥ፤ ምክረ ሐሳብ የሚያቀርብ፤ ሂደትን የሚገመግምና ገንቢ ኂስ የሚሰጥ መሪ ይፈልጋል።

ይኽ ባለመሆኑ ነው አሁን ሆነ እየተባለው የትምህርት ጥራት ችግር የተፈጠረው፤ የትምህርት ውድቀትም አለ ለማለት ዕድል የፈጠረው። እንዲህ ዓይነት መሪ ቢኖር ኖሮ ችግሮቹን በሂደት እያየና እየገመገመ አስፈላጊውን የእርምትና ማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ስለሚያስተካክል ጥራቱ በዚህ መልኩ አይወርድም፤ አደጋውም አይፈጠርም ነበር።

ነገር ግን አሁን ያለበት ሁኔታ ሲታይ፣ ሰዎችን ከማብቃት፣ በገበያው ላይ ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጠሩ ከማብቃት፣ የራሳቸውን የፈጠራ ዐቅም እንዲያዳብሩ ከማድረግ አኳያ ሙሉ በሙሉ ውጤት የለውም የሚባል አይደለም። በተወሰነ ውጤትም አምጥቷል። ለምሳሌ፣ በሁሉም የሀገሪቱ አከባቢዎች የፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች መፍጠር ተችሏል። ድሮን እስከመፍጠር ደረጃ የደረሰ ወጣት ትውልድን ማፍራት ተችሏል። ሆኖም ግን ጥራትን በዓለም መመዘኛ መሠረት ከታየ ተጎድቷል።

## የውድቀቱ ተጽዕኖ እና ተጠያቂነት

የትምህርት ጥራት ችግር ላይ ሲወድቅ እና ትውልድ ከትምህርት ገበታ ማግኘት የሚገባውን ነገር ማግኘት ሳይችል ሲቀር፤ በምላሹ እንደ አገርም ሆነ እንደ ሕዝብ የሚፈጠር ማኅበራዊም፣ ኢኮኖሚያዊም፣ ፖለቲካዊም፣ አጠቃላይ ከሰላምና ደኅንነት እና ሌሎችም ዘርፎች ላይ ከፍ ያለ ዋጋን የሚያስከፍል ነው። በኢትዮጵያም በትምህርት ጥራት ችግር ምክንያት ይኸን ያህል ተብሎ የሚገለጽ መጠን ጉዳትና ተጽዕኖ አይጠቀስ እንጂ፤ በኢኮኖሚውም፣ በማኅበራዊ መስተጋብሩም፣ በሰላምና ደኅንነቱም፣ በፖለቲካውም፣... ዘርፎች ለሚታዩ ችግሮች አንዱና ቀዳሚው ምክንያት ይኸው የትምህርት ጥራት ችግር ስለመሆኑ በርካቶች ይናገራሉ።

ቀደም ሲል በተጠቀሱት ሰነዶች የተመላከተውም ይሄው እውነታ ነው። ምክንያቱም ያላወቀ ተማሪ በተሰማራበት መስክ ውጤታማ አይሆንም፤ ክህሎት ያልጨበጠ ተማሪ የፈጠራ ዐቅምም ተነሣሽነትም አይኖረውም፤ በአመለካከቱ መልካም ሰብእናን የአልተላበሰ ትውልድ ለሀገሩም ለሕዝቡም የሚሆን የሞራል ልዕልናን ገንዘቡ አያደርግም። የእነዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ሕዝብን እንደ ሕዝብ፤ አገርንም እንደ አገር ለፍቶ መና የሚያደርግ ነው።

ይኽ እንዲሆን ደግሞ የትምህርት ዘርፉን የሚመራው አካል ሐላፊነቱ የጎላ ሊሆን ቢችልም፤ በርካታ አካላት ግን ድርሻ አላቸው። ወላጆች፣ የየአከባቢው ማኅበረሰቦች፣ ቤተ እምነቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራን፣ ርእሳነ መምህራን፣ ተማሪዎች፣... ሁሉም ድርሻቸው ይለያይ እንጂ ለችግሩ መፈጠር፤ ለአገራዊም ሆነ ማኅበረሰባዊ ተጽዕኖው መከሠት የየራሳቸው አበርክቶም፣ ተጠያቂነትም አለባቸው።

“አሁን ላይ የትምህርት ጥራት በመውረዱ፤ ችግሩም ወደ ትምህርት ውድቀት እያመራ በመሄዱ ምክንያት አገርም ሆነች ሕዝብ ከትምህርቱ መስክ ማግኘት የአለባቸውን ጥቅም አግኝተዋል ማለት አይቻልም፤” የሚሉት ዶክተር ፍርዲሳ፤ ምናልባት የትምህርት ተደራሽነትን ከማስፋት እና የተማረ የሰው ኃይል በመፍጠር/በማብቃት ረገድ ጥሩ ነገር ተገኝቷል ለማለት ቢያስችልም፤ የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ረገድ እንደ አገርም ሆነ እንደ ሕዝብ ከትምህርት ዘርፉ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ከማግኘት አኳያ የሚጠበቀውን ያህል አለመሆኑን ያስረዳሉ።

እንደ ዶክተር ፍርዲሳ ገለጻ፤ በአለፉት ዓመታት የትምህርት ዘርፉ ዕውቀትን፣ ክህሎትንና አመለካከትን በተማሪዎች ከማሥረጽ አኳያ የሚጠበቀውን ያህል አልሄደም። ለምሳሌ፣ ቀጣሪ ድርጅቶች ተመራቂ ተማሪዎችን መልምለው ያሠለጥናሉ። ይኽን የሚያደርጉትም በትምህርት ተቋማት የሚያገኙት ዕውቀትና ክህሎት የሥራ ቦታው ከሚፈልገው ዕውቀትና ክህሎት ጋር የሚጣጣም በአለመሆኑ ነው።

ይኼ ደግሞ ባለድርሻ አካላት ተናብበው አገር ከዘርፉ በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ምን ትፈልጋለች ብሎ የመምራትም፣ የመሥራትም ባህሉ ያለመዳበሩ ማሳያ ነው። ከዚህ ባሻገር ተማሪዎች ተመርቀው ወደ ሥራ አይገቡም። ይኸም ስናስተምር ለምን እንደምናስተምር ዐውቀን ስለማናስተምር ነው። በዚህ ምክንያት ደግሞ የግብር ከፋዩ ገንዘብ ነው የሚባክነው፤ የአገር ኢኮኖሚ ነው የሚጎዳው፤ ማኅበራዊ ጉዳዮች ናቸው የሚናጉት።

ለዚህ የአንድና ሁለት አካላት ብቻ ሐላፊነትን ያለመወጣት ችግር አይደለም። በዚህ ረገድ እንደ አገርም እንደ አንድ ዜጋም ሁሉም ተጠያቂነት አለበት። ምክንያቱም በአመራሩ (ከትምህርት ቤት ጀምሮ እስከላይኛው ድረስ) ክፍተት አለ። ቁልፍ ክፍተትና ችግሮችን ለይቶ ከማረም ይልቅ፤ በስብሰባ፣ በዕቅድና ሪፖርት ላይ ነው ጊዜውን የሚያሳልፈው። የትምህርት ተቋማትም ቢሆኑ በዛው ልክ ክፍተት ያለባቸው ናቸው።

ይዘቱም ተመሳሳይ ክፍተት አለው። በመማር ማስተማሩም ሂደት የተማሪ ሰዓት ይባክናል። የተማሪዎችም ለትምህርት በልኩ ትኩረት የአለመስጠት ችግር አለ። ሆኖም ተማሪ ድጋፍና ማበረታቻ ያስፈልገዋል። ተምሮ ብቁና ምርታማ ዜጋ የመሆን ተነሣሽነቱ ሊፈጠርለት፤ ለዚህ የሚሆን ከባቢም ሊመቻችለት ይገባል። መምህራንን ያለማብቃት ጉዳይም አለ። መምህራን ላይ ከሕይወታቸው ጋር የተገናኘ፤ ከራእይያቸው ጋር የተገናኘ፤ ከተነሣሽነት /ሞቲቬሽን/ ጋር የተገናኘ፤... በአለመሠራቱ የሚጠበቅባቸውን ያህል ምሳሌ/ሞዴል/ ሆነው እንዳይገኙ ያደርጋል።

በጥቅሉ አካሄዱ ከሕገ መንግሥቱ አንጻር የሰው ኃይሉን ስናስተምር ከዚህ ተነሥተን እነዚህ እንደርሳለን፤ እናደርሳለንም ተብሎ ሊተገበር ያስፈልጋል። ለምሳሌ፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት የታየው የፈተና ውጤት የተማሪዎች ውድቀት ሊመስል ይችላል። ሆኖም የተማሪው ውድቀት ብቻ አይደለም፤ ተማሪ የወደቀው በሁሉም አካል ውድቀት ነው። በፈተና 97 በመቶው ተማሪ ወደቀ ሲባል፤ ውድቀቱ የተማሪው ብቻ ነው ሊባል አይገባውም። አጠቃላይ ውድቀቱም፣ ተጠያቂነቱም የጋራ ነው።

አቶ ታዬም፣ በዶክተር ፍርዲሳ ሐሳብ ይስማማሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ፈተና አንዱ የችግሮች መመልከቻ መንገድ እንጂ ብቸኛ የጥራት ጉድለትን መለያ መሣሪያ አይደለም። በመሆኑም በፈተና የተገለጠው ችግር፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ ሲፈተሽ ታይቷል። ውጤቱም የሂደቱ ፍሬ መሆኑን መመልከት ተችሏል። ሆኖም ችግሩ በአንድ ጀንበር የመጣ እንደአልሆነ ሁሉ በአንድ ጀንበር ሊፈታ አይችልም፤ ሂደት የሚጠይቅ፣ ሥራና ጊዜም የሚፈልግ ነው።

የትምህርት ጥራትን ለማምጣት የተማሪ የመማር ፍላጎት ወሳኝ ነው። ለመማር ዝግጁ የሆነ ተማሪ በሌለበት ይኼን ማሰብ አይቻልም። ይኸንን ዓይነት ተማሪ ለመፍጠር ደግሞ ወላጆች፣ የየአከባቢው ማኅበረሰብ፣ ትምህርት ቤቶች፣ የትምህርት አመራሩ፣... ድርሻው የጎላ ነው። ወላጅና የየአከባቢው ማኅበረሰብ ለትምህርት ፍላጎት ያለው ተማሪን ወደ ትምህርት ቤት ሲልኩ፤ ትምህርት ቤቶችና የትምህርት አመራሩ ደግሞ ለመማር የተዘጋጀውን ተማሪ በፍላጎቱ ልክ የሆነ ዝግጅት አድርገው ሊያስተምሩት፤ በዕውቀት፣ ክህሎትና

አመለካከትም ሊያበቁት ይገባል። የእነዚህ አካላት ሥራ ድምር ውጤት የሚመዘነው ደግሞ በፈተና እንደመሆኑ፤ በፈተናው የታየው ውድቀትም የተማሪውን ችግር ብቻ ሳይሆን፤ የእነዚህን ሁሉ አካላት ችግር አጋልጦ የአሳየ ነው።

በመሆኑም ሂደቱ በዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የበቃ ሰው ማፍራት እንዳይቻል አድርጓል። በዚህም ሀገሩንም፣ ራሱንም በጥቅሉ ሁሉን ነገር ለመለወጥ የሚቸገር ማኅበረሰብ እየተፈጠረ ነው። ይሄ ደግሞ አንድን ሴክተር ብቻ የሚጎዳ አይደለም። የጤናውን ዘርፍ ይጎዳል፤ የግንባታውን ዘርፍ ይጎዳል፤ የፍትሕን ዘርፍ ጎዳል። ስለዚህ ትምህርት ላይ በጋራ ባለመሥራቱ እንደ አገርም፣ እንደ ሕዝብም ብዙ ዋጋ እየተከፈለበት ነው። በመሆኑም ለትምህርት ጥራት ችግር መፈጠርም፤ ጥራቱ በመውደቁ ምክንያትም እንደ አገርም፣ እንደ ማኅበረሰብም ለተፈጠረው ችግር ሁሉም ድርሻ አለው።

## ከውድቀቱ እንዲነሣ ምን እየተሠራ ነው?

በአንድ አገር ትምህርት የሚጠበቅበትን ሚና የሚወጣው፤ በጥራትም፣ በተደራሽነትና ፍትሐዊነትም በኩል የተመጣጠነ ሥራ መሥራት ሲቻል ነው። የእስከ አሁኑ ሂደት ደግሞ ይኼ ባለመሆኑ ምክንያት በተደራሽነት ላይ ውጤት ቢታይም፤ ከጥራት አኳያ የተፈጠረው ስብራት ብዙ ዋጋ የአስከፈለ ስለመሆኑ ከሰነድም፣ ከዘርፉ ባለድርሻዎችም፣ ከሪፖርትም መረዳት ተችሏል።

በመሆኑም ችግሩን እና አደጋውን ከመገንዘብ ባሻገርም፤ ለችግሩ መሻገሪያ፣ ከአደጋውም መውጫ የሚሆን መፍትሔን ማቅረብ፤ በመፍትሔው መነሻነትም በዕቅድ ታግዞ ወደ ተግባር መግባት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ የትምህርት ዘርፉ የሚመራበት አዲስ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ የተቀረጸ ሲሆን፤ ይሄ ፖሊሲ የሚመራበትም፣ ውጤቱ የሚገመገምበትም አገራዊ የዐሥር ዓመት የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለአለፉት ሦስት ዓመታት እየተተገበረ ይገኛል።

ለምሳሌ፣ ከ2013 እስከ 2022 ዓ.ም. እንዲተገበር በተዘጋጀው የዐሥር ዓመት የልማት ዕቅድ፤ ከላይ የተጠቀሱትን የትምህርቱ ዘርፍ ክፍተቶችን በአገናዘበ መልኩ ትምህርት አንዱ ቁልፍ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል። በዚህም የትምህርት ፍትሐዊ ተደራሽነትን እንዲሁም ጥራትና ተገቢነትን ማረጋገጥ ከዕቅዱ ቀዳሚ ጉዳዮች መካከል ተጠቃሾች ናቸው።

በተለይ ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያ ሥርዓተ ትምህርቱ፣ የማስተማር ሥነ ዘዴው፣ የማስተማሪያና የመማሪያ ቁሳቁሶችና የግምገማ ሥርዓቶቹ ከገበያው ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ እንዲሆን ማድረግን ታላሚ አድርጓል። ጥያቄው ታዲያ ይኼንን ዕቅድ ከመተግበር እና የወደቀውት የትምህርት ሂደት ከማንሣት አኳያ ምን ያህል ተጉዘናል? የሚለው ነው።

አሁን ላይ በትምህርት አሰጣጡ ሂደት መገኘት የሚገባቸው የዕውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ጉዳዮች ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን የሚናገሩት ዶክተር ፍርዲሳ፤ ለዚህም የተማሪ ጊዜ መባከን፣ የመደገፍ ዐቅም አለመኖር፣ አመራሩ ለሪፖርት እንጂ ለይዘት ትኩረት አለመስጠት፣ የማስተማሪያ ሥነ ዘዴው እና ሌሎችም ምክንያቶች ችግሩ የተፈጠረ መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደ ዶክተር ፍርዲሳ ገለጻ፤ የትምህርት ሥራ ጥንቃቄ ይፈልጋል። በተለያዩ ፈተናዎች የተማሪው መውደቅም የሁሉም ባለድርሻ ውድቀት ውጤት ነው። በመሆኑም ከዚህ ችግር ለመውጣት መሥራት ይገባል። ይኼን ለማድረግ ግን ትምህርት የአንድ ግለሰብ ወይንም የተወሰነ ቡድን ወይም ፓርቲ ብቻ አለመሆኑን ተገንዝቦ ሁሉም መሥራት ይኖርበታል።

በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ሥራ የትምህርት አስተዳደሩን ማስተካከል ነው። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ከትምህርት ቤቶች ጀምሮ ለትውልዱ አሳቢ፣ ተቆርቋሪ፣ ዕውቀትና ክህሎት ያለው፤ አመለካከቱ ሰፋ ያለ አመራር መመደብ አለበት። ምክንያቱም በዚህ ቦታ ትውልድን እየተገነባ እንደመሆኑ በፖለቲካ አመለካከቱ ብቻ ሊሰየም የሚገባው አመራር ሊኖር አያስፈልግም።

ከስምንት ዓመት በፊት እርሳቸውም በነበሩበት ከጂ.አይ.ዜድ ጋር በመሆን ብዙ ሥራ መሠራቱን የጠቆሙት ዶክተር ፍርዲሳ፤ ከዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ ፍኖተ ካርታ (ሮድ ማፕ) ተብሎ መጀመሩን፤ ይኼም አዲስ ነገር ይዞ የመጣ እና ቀደም ሲል በሰዎች ልብና ሐሳብ ውስጥ የነበረውን ነገር ለማካተት የሞከረ መሆኑን ተናግረዋል።

ሰነዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ትምህርት በሦስት ዓመት መሆን የለበትም፤ የመጀመሪያ ዓመት (ፍረሽማን) ኮርስ መቅረት የለበትም፤ ቢያንስ አራት ዓመት መሆን አለበት፤ የሚለውን ለመመለስ ማስቻሉን በምሳሌነት አንሥተዋል። ሆኖም ሁሉንም ነገር በትክክል ለመሥራት መሞከር እና ትክክለኛውን ሥራ በትክክል መሥራት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል፤ ሲሉ አሁንም በአተገባበር በኩል ያሉ

ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ትምህርት ቤት ሊኖር የሚገባው የክትትልና ድጋፍ ሥርዓትም ችግር የነበረበት ነው። አሁን ይኼንን ለመቀየርና ችግሩን ለማረምም የክትትልና ድጋፍ ሥርዓቱ የሚመራበት አሠራር መመሪያ እየተዘጋጀ ሲሆን፤ በቅርቡም ወደሥራ ይገባል።

ክፍተቶች ስለመኖራቸው ጠቁመዋል።

አሁን እየተሰጡ ያሉ ፈተናዎች መልካም ቢሆኑም፤ ከፈተና በፊት መሠራት የሚገባቸው ብዙ ነገሮች መኖራቸውን ለዚህ በማሳያ በማንሣት፤ በዚህም በትምህርት ቤት፣ በመምህራን ላይ፣ ጊዜ ላይ፣ የማስተማር ሥነ ዘዴ (ሜቶዶሎጂ) ላይ መሠራት እንዳለበት አብራርተዋል። በዚህ ረገድ አሁን ላይ ጥረቶችና መነሣሣቶች አሉ፤ ነገር ግን ትክክለኛ ሥራን በትክክለኛ መንገድ ነው እየተሠራ ያለው? ወይስ ማንኛውንም ሥራ ነው በትክክል ለመሥራት እየሞከርን ያለነው? የሚለው ትኩረት ሊሰጠውና ተፈትሾ ሊመለስ ይገባዋል፤ ብለዋል።

አቶ ታዬ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ አሁን ላይ 12ኛ ክፍል ተፈትነው የወደቁ ተማሪዎች በ2012 ዓ.ም. ላይ ዘጠነኛ ክፍል የነበሩ፤ በኮሮና ምክንያት አንድ ሴሚስተር ተምረው ወደሚቀጥለው ክፍል አለፉ ናቸው። በወቅቱ የማካካሻ ትምህርት ይሰጥ የተባለ ቢሆንም፤ ምን ያህሉ ተሰጥቷል? የሚለው ግን የራሱ ችግር የነበረበት፤ ሁሉም ራሱን ፈትሾ የሚመልሰው ነው። በ2013 ዓ.ም. ም ቢሆን፤ በፈረቃ በሳምንት ሦስት ቀን እንዲማሩ ሆነው ያለፉ ናቸው። ይሄ ከክፍለ ጊዜና መሰል የትምህርት ሰዓትን ከመሸራረፍ ባሻገር ያለ ጉዳይ ነው። ስለዚህ እነዚህ ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ሳያገኙ ያለፉ ናቸው።

ሌላው ችግር መምህርነት ተወድዶና ተከብሮ የሚገባበት ሙያ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ያለው ክፍተት ለትምህርት ጥራት መጓደል ተጠቃሽ ነው። ምክንያቱም ሁኔታው በመምህራን ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ ስለአለ እና የተሻሉ ሰዎች እንዳይገቡበት ስለሚያደርግም ጭምር ነው። የኢንስትራክሽናል ሊደርሺፕ ጉዳይ ደግሞ፣ ከመምህራን ምልመላ ይጀምራል። እነዚህ መምህራን እንዴትና ከየት ተመልምለው መጡ? የሚለው አንዱ ጉዳይ ነው። ሥልጠናውና ስምሪቱም ይሄንኑ የሚገድብ ነው።

የፖለቲካ ጉዳይ አስፈጻሚ በሚመስል መልኩ ተመልምሎና ሠልጥኖ ስምሪት የሚሰጠው ከሆነ፤ ይሄ አካል ኢንስትራክሽናል ሊደርሺፕ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም በምልመላ፣ በሥልጠና እና ስምሪት ላይ ያለው ክፍተት ተለይቶ እየተሠራበት ይገኛል። ይኼም አመራሩ የመማር ማስተማሩን ሥራ ብቻ ይዞ እንዲሄድ ያስችለዋል። ይሄ ሲሆን ደግሞ የዕውቀትም፣ የክህሎትም፣ የአመለካከትም ውጤት የሚገኝ ይሆናል።

ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ትምህርት ቤት ሊኖር የሚገባው የክትትልና ድጋፍ ሥርዓትም ችግር የነበረበት ነው። አሁን ይኼንን ለመቀየርና ችግሩን ለማረምም የክትትልና ድጋፍ ሥርዓቱ የሚመራበት አሠራር መመሪያ እየተዘጋጀ ሲሆን፤ በቅርቡም ወደሥራ ይገባል። ምክንያቱም ጥሩ ጥሩ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተው ወደታች የወረዱ ቢሆንም፤ አብዛኛው ችግር ከአተገባበር ጋር ተያይዞ የተፈጠረ እንደመሆኑ ይኼን ለመተግበር የሚሆን ተነሳሽነትና ቁርጠኝነትን መላበስ ይጠይቃል።

እንደ አቶ ታዬ ማብራሪያ፤ የትምህርት ተደራሽነት ብቻ ሳይሆን ጥራትም ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተለይቷል። ለዚህም ከቅድመ አንደኛ ትምህርት ጀምሮ ጥራትን ማዕከል ያደረገ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። ለምሳሌ፣ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን ከጤና፣ ከሴቶችና ሕፃናት ጋር በመሆን የሚሠራበት ፖሊሲ ተዘጋጅቷል። ይኼም ሕፃናቱ በጤናም፣ በማኅበራዊ መስተጋብርም፣ በተግባቦትም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ብቁ ሆነው እንዲያድጉም ከተጽዕኖ ነጻ ሆነው በአካልም በአእምሮም እንዲጎለብቱ ያስችላቸዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተሳትፎን ከማሳደግም ሆነ፣ በሂደቱ የሚፈጠር የትምህርት ጥራት ችግርን ከመፍታት አኳያ አንድ ሕፃን ቢያንስ የሁለት ዓመት፣ ከተቻለም የሦስት ዓመት ትምህርት ማግኘት አለበት፤ በሚል መንግሥት ሐላፊነትን ወስዶ እየሠራ ይገኛል።

ከዚህ በተጓዳኝ የትምህርት ፕሮግራም ከለሳ ተደርጓል። ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ ከማድረግ በተጓዳኝ፤ የሚገባቸውን ትምህርት እንዲያገኙ አስፈላጊው ሥራ እየተሠራ ይገኛል። ለዚህም የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፤ በዚህ በኩል ኅብረተሰቡን በማሳተፍ በክረምቱ ብቻ 12 ቢሊዬን ብር ኅብረተሰቡ አዋጥቶ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች ተገንብተዋል፤ አዳዲስ ትምህርት ቤቶችም ተከፍተዋል።

የትምህርት ቤቶች ማሻሻል ሥራው ደግሞ አራት መሠረታዊ ነገሮችን ይዞ የሚተገበር ነው። አንደኛው፣ አመራሩ ኢንስትራክሽናል አመራር እንዲሆን ማስቻል ነው። መምህሩም ርእሰ መምህሩንም ለትምህርት ሥራው በአግባቡ መጠቀም፤ ሁለተኛው፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲመራና እንዲከወን ማስቻል፤ ሦስተኛው፣ ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢን የመፍጠር (ምገባ ማከናወንን ጨምሮ ተማሪዎችን የሚያውኩ በትምህርት ቤቶችና ከባቢያቸው እንዳይኖር ማስቻል)፤ አራተኛው፣ የማኅበረሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ (ወላጆች ገንዘብ አዋጥቶ ትምህርት ቤት ከመገንባት ባሻገር ስለ ልጆቻቸው ውሎና የትምህትር ቤት ቆይታ ግድ የሚላቸው እንዲሆኑ ማስቻል) ናቸው።

በዚህም አበረታች ውጤት እየተገኘ ነው። ከተሠራ ደግሞ ለውጥ የማይመጣበት ምክንያት የለም። ሠርተውም ለውጥ ያመጡ ትምህርት ቤቶች አሉ። በሪሚዲያል መርሐ ግብርም ራሳቸውን አዘጋጅተውና አብቅተው ጥሩ የፈተና ውጤት ማስመዝገብ የቻሉ ተማሪዎችም አሉ። ትልቁ ጉዳይ ሥራው የእኔም ነው የሚል የባለቤትነት መንፈስ እና ለሥራው ትልቅ ተነሳሽነትና ቁርጠኛነት ይጠይቃል።

ሆኖም አሁንም ድረስ በአንድኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት የታየው ውጤት በሁለተኛ ደረጃ እና በቅድመ አንደኛ ትምህርት ባለመምጣቱ የሁለተኛ ደረጃ ከ44 በመቶ፤ የቅድመ አንደኛም ከ39 በመቶ የዘለለ ተደራሽ ማድረግ አልተቻለም። በዚህም የሁለተኛ ደረጃ እና የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች ተደራሽነት ጉዳይ ልዩ ትኩረት እንደሚሻ መመልከት ተችሏል።

በአጠቃላይም ተገቢውን ሰው በተገቢው ቦታ አስቀምጦ ውጤት እንዲመጣ ከማስቻል አኳያ የሁሉም አካል ክትትልና ድጋፍ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ተምሮና ተመርቆ መሥራት የማይችል ተማሪን መፍጠር ለማኅበረሰብም፣ ለአገርም ተጨማሪ ሸክም መፍጠር ማለት ነው። አዲስ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲም ይኼንን ችግር በሚቀርፍ መልኩ የተቀረጸና እየተተገበረ ያለ ነው።

## የመውጫ ሐሳብና መልእክት

ትምህርት የአንድ አገር የዕድገት ብቻ ሳይሆን የሁለንተናዊ ብልጽግና መሠረት መሆኑ የታመነ ነው። በኢትዮጵያም ትምህርት ይኼንን ሚናውን እንዲወጣ በማድረግ በኩል በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በዚህም የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ላይ የተገኘ ውጤት ቢኖርም፤ በጥራት አኳያ ግን እጅጉን ችግር የታየበት ስለመሆኑ ተደጋግሞ ተገልጿል፤ ይኼው እውነትም በተለያየ አግባብ ተረጋግጧል።

በተለያዩ ጊዜያት የሚወጡ ሪፖርቶችም ሆኑ በጥናት የተደገፉ ሰነዶች እንደሚያሳዩትም፤ በኢትዮጵያ የትምህርት ጥራትም እያሽቆለቆለ ሲሆን፣ በዚህም በየደረጃው ያለው አብዛኛው ተማሪ የትምህርት ውጤቱ ከ50 በመቶ በታች ነው። ሌላው ቀርቶ የከፍተኛ ትምህርትን የተቀላቀሉ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች ከመግቢያ ፈተናው ዝቅተኛውን የመግቢያ ነጥብ (50 በመቶ) በታች የአገኙ ናቸው። ይኼ ደግሞ

ችግሩ ከመሰረቱ የተበላሸ እና ሥር ነቀል ለውጥ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ አመላካች ነው።

ለምሳሌ፣ በ2002 ዓ.ም. በሁለተኛና ሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በተካኼደ የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ዳሰሳ ጥናት፤ በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በቀጣይ ክፍሎች በአግባቡ ለመማር የሚያስችሏቸውን መሠረታዊ ክህሎቶች ያላዳበሩ መሆናቸው ታይቷል። በወቅቱም፣ ሁለተኛ ክፍል ከሚማሩት ተማሪዎች 34 በመቶ ለደረጃው ከተዘጋጀው ምንባብ ውስጥ አንድም ቃል ማንበብ አልቻሉም፤ 48 በመቶው ደግሞ ከተዘጋጀው አንብቦ የመረዳት ፈተና አንዱንም መመለስ አልቻሉም።

በተመሳሳይ፣ በ2006 ዓ.ም. በተደረገው ዳሰሳ በሒሳብ፣ እንግሊዝኛ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪና ባዮሎጂ ትምህርቶች አማካይ ውጤታቸው 50 በመቶ የደረሰ ዐሥረኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥር 23 በመቶ ነው። ይሄም ተማሪዎች በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃዎች መሠረታዊ ክህሎቶች ከአላዳበሩ፣ በተከታታይ ደረጃዎች ባሉት ክፍሎች በሚማሯቸው የትምህርት ዓይነቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑን አረጋገጠ ሆኗል። በመሆኑም ይኼንን መቀየር እና ትምህርት በአገር ሁለንተናዊ ለውጥ ውስጥ ሚናውን እንዲወጣ መሥራት ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ የቤት ሥራ ነው።

ዶክተር ፍርዲሳ ይኼንን በተመለከተ እንደተናገሩት፤ የትምህርት ጥራት ወረደ፤ ትምህርትም ችግር ውስጥ ገባ ማለት፤ ትውልድ ወደቀ፤ አገርም ችግር ውስጥ ገባች፤ ማለት ነው። ነገ አመራሩን የሚተካ፤ አገር የሚረከብ ትውልድ መፍጠር ከአልተቻለ ደግሞ አገር አትቀጥልም። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ተጠያቂነት አለበት። አሁን የታየው የትምህርት ጥራት ውድቀትም የማይቀረፍ፣ ሙሉ ለሙሉም ጨለማ ነው ብሎ መውሰድ አይገባም። ከዚህ ችግር መውጫ ብዙ አስቻይ ሁኔታዎች እና መልካም ዕድሎች አሉ። ለምሳሌ፣ መንግሥት ትምህርት ላይ ኢንቨስት ያደርጋል። ትኩረት ሰጥቶም መሥራት ጀምሯል። ማገዝ ለሚፈልጉም በሩ ክፍት ነው።

እናም ሁሉም ዜጋ ትምህርት የጋራ ሥራን የሚጠይቅ መሆኑን ተገንዝቦ መሥራት አለበት። ተባብሮ አለመሥራት ለውድቀት እንደሚዳርግ ሁሉ፤ ተባብሮ መሥራትም ከውድቀት መነሻ ዐቅም እንደሚፈጥር መገንዘብ ይገባል። ለምሳሌ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች በትምህርት ጉዳይ ላይ ገለልተኛነት ሊኖራቸው አይገባም። ምክንያቱም ትምህርት ትውልድ መፍጠሪያ ዐቅም ነው። ትውልድ መፍጠር ደግሞ የእኔ ነው፤ የአንተ ነው፤ የሚባል አይደለም። ስለዚህ በትምህርት ጉዳይ አብረው መሥራት ይኖርባቸዋል። ተማሪ የሚኮርጀው በአግባቡ የሚገባውን ነገር ማግኘት ባለመቻሉ ስለሆነ፣ በራሱ የሚተማመንና ስርቆትን የሚጠየፍ ተማሪ፤ ለራሱም ለሥራውም የሚታመን ማኅበረሰብ መፍጠር ከሁሉም ይጠበቃል።

ምክንያቱም ዓለም በዕውቀት፣ በክህሎትና አመለካከት በኩል የደረሰችበት ደረጃ፣ ጊዜው የውድድር እንዲሆን አድርጎታል። ይሄ ትውልድ ደግሞ በዚህ ውድድር ውስጥ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ከዓለም ጋር መዋሐድ አለበት። ስለዚህ ወጣቶችን በጥቅሉም ትውልዱን የዚህ ዕድል ተቋዳሽ እንዲሆን መሥራት ይገባል።

ከዚህ በተጓዳኝ ተማሪ ሊማርም ሆነ የተማረውን ዐውቆ ሊተገብር የሚችለው፣ ሰላም ሲኖር እንደመሆኑ ሰላሙ ላይ መሥራት ይገባል። እነዚህና መሰል ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ደግሞ የትውልዱ የነገ ዕጣ ፈንታ ላይ መወሰን መሆኑን ዐውቆ ሁሉም ሊረባረብ ይገባዋል።

አቶ ታዬ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ትምህርት የአገር ዕድገት መሠረት እንዲሆን፣ አገር ያለችበትን ቦታ ማወቅን፣ የት ለመድረስ ዕቅዳ እየሠራች እንደሆነም መረዳትን ይጠይቃል። እዚህ ለመድረስም የተማረ የሰው ኃይል፣ የተማረ ማኅበረሰብ በእጅጉ ወሳኝ መሆኑንም መገንዘብ ይገባል። ለምሳሌ፣ በመንግሥት ተቋማት ውጤት ለማምጣት የተማረ የሰው ኃይል ያስፈልጋል፤ በንግድ ውጤታማ ለመሆንም ትምህርት ያስፈልጋል፤ በግብርናው ዘርፍ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ዕውቀት ያስፈልጋል፤ የሰከነ ፖለቲካ ለማራመድም ከፍ ያለ ዕውቀትና አመለካከት ይጠይቃል፤ ሰላምና ደኅንነትን ለማስጠበቅም የሥነ ምግባር ከፍታን ይጠይቃል።

በዚህ መልኩ ከታየም የትምህርት ተጽዕኖ የሴክተር ድንበር የለውም። ችግሩ ግን እነዚህ ተቋማት (ግብርናውም፣ ንግዱም፣ ደኅንነቱም፣ ባንኩም፣...) ከትምህርት የሚፈልገውን ያህል ለትምህርት ጥራት መሻሻል እየሠሩ አለመሆናቸው ነው። ለምሳሌ፣ ባንኮች አሠራሮቻቸውን ለማሳለጥ ደንበኞቻቸው ሞባይል ባንኪንግና ሌሎችንም ቴክኖሎጂዎች እንዲጠቀሙ ይገፋፋሉ። ሆኖም ይሄን መጠቀም የሚችል ማኅበረሰብ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሚናቸው ይሄ ነው የሚባል አይደለም። በመሆኑም እያንዳንዱ አካል ከትምህርት ሴክተሩ የተሻለ ሰው መጠበቅን እንጂ የተሻለ ሰው በማፍራት ሂደቱ ላይ ሚናው እምብዛም አይደለም። በመሆኑም ይኼ መታረም እና ሁሉም ለትምህርት ጥራት መሻሻል የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል።

ከዚህ ባሻገር አንድ ልጅ ብዙ ቦታ ይቀረጻል። ይኼም ከቤተሰብ ይጀምራል፤ በማኅበረሰብ ይገነባል፤ በእምነት ተቋማት ይታነጻል፤ በትምህርት ቤት ይቀረጻል። እነዚህ የሚሰጡት መልካም ነገር ካለ መልካም ፍሬን ይዘራል፤ ከአልሆነም ውጤቱ በተቃራኒው ይሆናል። ወጣቶች መልካም ሰብዕናንም፣ መጥፎ ሰውነትንም የሚያገኙት ከእነዚሁ አካላት ነው። ስለዚህ ሁሉም በዚሁ ቅኝት የትውልዱን ሰብእና በዕውቀትም፣ በክህሎትም፣ በአመለካከትም ቀርጸው ማነጽ ይጠበቅባቸዋል።

እንደ አቶ ታዬ ማብራሪያ የትምህርት ጥራት ሂደት ነው። የትምህርት ጥራት ችግር አንጻራዊ ነው እንጂ በአደጉት ሀገራትም አለ። ቁርጠኛነቱ እና መተባበሩም ካለ በአጭር ጊዜ ከችግሩ መውጣት ይቻላል። ከከፋ የትምህርት ጥራት ችግር ውስጥ የወጡ ሀገራት ተሞክሮም የሚያሳየው ከሠሩ ከችግሩ መውጣት እንደሚቻል ነው። በኢትዮጵያም ከችግሩ ለመውጣት የተጀማመሩ ሥራዎችን አጠንክሮ መሄድ ያስፈልጋል።

ለዚህ የሚሆን ተነሣሽነትና ቁርጠኛነትን ለመያዝ ደግሞ፣ አሁን ላይ የሚታዩ ብልሹ አሠራሮችም ሆኑ አገራዊ ችግሮቻችን የትምህርቱ ዘርፍ ውድቀት ውጤቶች መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል። ምክንያቱም የትምህርት ውድቀት የማኅበረሰብም፣ የአገርም ውድቀት ነው። ለምሳሌ፣ አምና ያ ሁሉ ተማሪ ሲወድቅ ሁሉም ቆም ብሎ ወደራሱ ማየት ይገባ ነበር። ይሄ ባለመሆኑ በዚህ ዓመት ተመሳሳይ ችግር ታየ።

በዚህ ረገድ ተማሪው ድርሻውን ወስዷል። ይኼ ግን የችግሩ ትንሹ ክፍል ነው። አብዛኛው በሌሎች ባለድርሻዎች ላይ የሚወድቅ ሐላፊነት ነው። በተለይ የትምህርት ሴክተሩ በዋናነት ወስዶ ሐላፊነቱን በሚገባ መወጣት ይኖርበታል። በተመሳሳይም ወላጅ፣ ትምህርት ቤቶች፣ መምህሩ፣ የትምህርት አመራሩ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣... ሁሉም የየራሱን ወስዶ መስራት ይኖርበታል።

ምክንያቱም ሀገራት በተማሩ፣ በተመራመሩና ቴክኖሎጂን በፈጠሩ ዜጎቻቸው ነው እየተለወጡና እያደጉ ያሉት። እኛም ይሄንኑ ተገንዝበን ከሠራን እንደምንለወጥ፤ ከአልሠራን አሁን በአለንበት ችግር ቀጥለን ለባሰ ችግር እንደምንዳረግ መረዳት ይገባል። ሁሉም ሐላፊነቱን ወስዶ እንዲሠራ ያይጠበቃል። ያሉንን ብዙ ፀጋዎች ማልማት፣ መጠቀምና መለወጥ የምንችለውም ይኼንን ስናደርግ ነው።

የመጽሐፉ ርእስ:-

**አሰብ የማን ናት?**

የመጀመሪያ ዕትም:-

**2003 ዓ.ም.**

የገጽ ብዛት:- **260**

ደራሲ:- **ያዕቆብ ኃይለ ማርያም (ዶ/ር)**




# የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ

# በ«አሰብ የማን ናት?»

# መጽሐፍ

# የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ

# በ«አሰብ የማን ናት?» መጽሐፍ

ግርማ መንግሥቴ

ስለ ባሕር በር የተደረጉ ጥናቶች በርካቶች መሆናቸው ይታወቃል። ይሁን እንጂ፣ ከወቅታዊነት፣ አስተማሪነትና አሳዋቂነት፣ መረጃ ሰጪነት፣ ተጨባጭነት፣ ተነባቢነት፣ ተጽዕኖ ፈጣሪነት፣ ተጠቃሽነት ወዘተ አኳያ ሲፈተሽ ‹‹አሰብ የማን ናት?›› ን የሚያክል ይህ ጸሐፊ አላጋጠመውም።

እያንዳንዱ መሥመር በመረጃ የተሞላ፣ እያንዳንዱ ገጽና ምዕራፎቹ በዕውቀትና እውነት ላይ የተመሠረቱ፤ ጣፋጭና ድግሙኝ፣ ደጋግሙኝ . . . ከማለቱ አኳያ ከተመለከትነው መጽሐፉ ከምር ከብዙዎቹ ይለያል።

ከአዲስ አበባ 882 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ስለሚገኘው፣ 811 ኪ.ሜ የሚሆነው በኢትዮጵያ በኩል ስለአለው፣ ቀሪው 71 ኪሎ ሜትር ደግሞ በኤርትራ በኩል ስለሆነው፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል የተካኼደውን ጦርነት ተከትሎ ለ20 ዓመታት ተዘግቶ ስለነበረው አሰብ ወደብ ለማተት፤ ለኅትመት የበቃው ‹‹አሰብ የማን ናት?›› መጽሐፍ ከሌሎች ይለያል። ከሚለይበትም አንዱ ዓለም አቀፋዊነቱ ሲሆን ዓለም አቀፍ ሕጎችን፣ መርሖዎችን፣ ልምዶችን፣ ስምምነቶችን ወዘተ በርከት አድርጎ ይዞ መቅረቡ ነው።

መታሰቢያነቱን ለዲሞክራሲ፣ ለፍትሕና ለአንድነት ሲታገሉ ለወደቁ ኢትዮጵያውያን የአደረገው ‹‹አሰብ የማን ናት?›› የብዙ ሕዝብ የታፈኑ ድምፆች መተንፈሻ፣ የበርካቶችን ቁጭት ማሳያ በመሆኑ ከሌሎች ይለያል።

ለተደጋጋሚ ኅትመት በመብቃቱ ብቻ ሳይሆን፣ በከፍተኛ ደረጃ በመነበቡ፣ እጅጉን በማከራከሩ፣ ብዙዎችን ያነቃቃ መሆኑ፣ ለብዙዎች የመረጃ ምንጭ በመሆን ማገልገሉ፣ የበርካቶች ብዕር ከአፎቱ እንዲመዘዝና በአሰብ ጉዳይ በስፋት እንዲጻፍ ምክንያት መሆኑ ከመጽሐፉ ጠንካራ ጎን የሚመዘዙ እውነታዎች ናቸው።

ተሸጦ የሚገኘው ገቢ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚውለው ‹‹አሰብ የማን ናት?›› መጽሐፍ 216 ያህል ዋቢ ሥራዎችን፣ ማጣቀሻዎችን (ቃለመጠይቆችን፣ ጥናታዊ ሥራዎችን፣ ታሪካዊና ሕጋዊ ሰነዶችን ወዘተ) በመያዝና በመረጃና ማስረጃነት በመጠቀሙ፤ ለአንባብያንም በራስ መተማመን እንዲፈጠር በማድረጉ ከብዙዎቹ መሰል ሥራዎች ይለያል።

የግርጌ ማስታወሻዎች ያሉትና በተለያዩ ሰንጠረዦች የተደገፈው ‹‹አሰብ የማን ናት?›› መጽሐፍ ከርእሱ ጀምሮ ቀልብ ሳቢና ለውይይትና ክርክር ጋባዥ፣ በራሱ የሚተማመን ተከራካሪ ካለ ወደ አደባባይ እንዲመጣና አሰብ የማን እንደሆነች በአደባባይ መረጃና ማስረጃውን ይዞ እንዲከራከር የሚጋብዝ ወዘተ መሆኑም ለልዩነቱ ተጨማሪ ማሳያ ነው።

‹‹አሰብ የማን ናት?›› (የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ) በደፋርነቱ ከሁሉም ይለያል። ደራሲው "ተዘግቷል የተባለውን ዶሴ ዳግም ወደ አጀንዳነት በመቀየራቸው፣ የተከደነውን በመከፋፈታቸው፣ የተደበቀውን በመገላለጣቸው፤ ከሁሉም በላይ የማናውቃቸውን ገመናዎች በመዘርገፋቸው እርሳቸውና ‹‹አሰብ የማን ናት?›› ሥራቸው ደንቅ ናቸው ማለት ይቻላል።

የወቅቱ መሪዎች ". . . ኢትዮጵያ ያለወደብ ቀረች ብለን የምንቆጭበትና የምናዝንበት ምክንያት የለም። . . .፤ "ተቃዋሚዎች የሚያነት የአሰብ ይገባኛል ጥያቄ፣ ኢሕአዴግ አያምንበትም"፤ "አሰብን ካልያዝን የሚሉ ዘውዳዊ ትምክህተኞች ናቸው"፤ "አሰብ ኢትዮጵያ ከአልተጠቀመችበት የግመል መፈንጫ ይሆናል" (ደራሲው በገጽ 189 ላይ "በአንድ ወቅት የተነሣውን የአቶ መለስ ዜናዊ "አሰብ ኢትዮጵያ ከአልተጠቀመችበት የግመል መፈንጫ ይሆናል" የሚል አቋም ተከትሎ፣ የአካባቢውን ስትራቴጂክነትና ጂኦፖለቲካዊ ፋይዳ የተረዱ ኢትዮጵያውያን፤ የአቶ መለስን ሐሳብ ተቃውመው፣ አሰብ ለኢትዮጵያ በጎ በማይመኙ ኃይሎች እጅ ትወድቃለች በማለት አስጠንቅቀው ነበር።" ማለታቸውን ልብ ይሏል።)፤ ኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤት ከአደረጓት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ (1434 – 1468) ጀምሮ፣ የቀድሞዎቹ "ታሪካዊ የባሕር በር ባለቤትነትዋን አስከብረው ቢያልፉም፤ ይኽ ትውልድ ግን የተረከበውን አደራ መጠበቅ አልቻለም።" የሚሉ ትውልድ ወቃሽ አስተያየቶች በበዙበትና ስለ አሰብ ያነሣ ሁሉ በሚዘለፍበት በዛ ክፉ ጊዜ፤ "ለኢትዮጵያ ወደብ አልባነት ተጠያቂው ኢሕአዴግ ነው" በማለትና ራሱን፣ ኢሕአዴግን ፊት ለፊት በመጋፈጥ፣ ያለ ምንም ፍርኀት ለአደባባይ የበቃ መጽሐፍ በመሆኑ ሁለቱም (መጽሐፉና ደራሲው) ከሌሎች ይለያሉ።

የወቅቱ መሪዎች፣ "ወደብ አለመኖሩ ረኃብ አያመጣም። በጎረቤት አገር ወደብ በመጠቀም መሥራት ይቻላል። ያለ ነገር ነው፤ ስለዚህ ኢትዮጵያ ያለ ወደብ ቀረች ብለን የምንቆጭበትና የምናዝንበት ምክንያት የለም። ወደብ አለመኖሩ አይጎዳንም፣ ሊጎዳንም አይችልም። ወደብ በነበረን ጊዜ ኢትዮጵያ ደሀ ነበረች። አሁን ወደብ የለንም። ዕድገት ግን እያስመዘገብን ነው፤ በማለት አሰብን ለተመለከቱ የሕዝብ ጥያቄዎች የሰጡትን አስገራሚ መልስ ሁሉ ሳይቀር፤ "ያለ ምንም መሸማቀቅ (ያኔ በየስብሰባው ላይ እንዲህ ይባል ነበርና ነው) ለንባብ የበቃ ታሪካዊ መጽሐፍ በመሆኑ፣ ወቅቱንና የወቅቱን መሪዎች ልክ እንደ መስተዋት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መጽሐፍ በመሆኑ፣ ከእስከ ዛሬዎቹና በርካታ ቁም ነገሮችን ሲያስጨብጡን ከኖሩት አሰብን የተመለከቱ ሥራዎች እጅጉን ይለያል የአልኩት።

## እስቲ ስለ አዘጋጁ ጥቂት እንበል፤

መጽሐፉ በመግቢያው ላይ ዓላማው "እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አሰብ የኢትዮጵያ መሆኗን ዐውቆ የባሕር በራችንን ማስመለስ ብሔራዊ ግዴታችን እንደሆነ ለማስታወስ መጣር መሆኑን አስፍሯል። በመጨረሻው ምዕራፍ "አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ ስለሚያስፈልግ ለእነዚህ ሰዎች መጠነኛ ግንዛቤ እንዲሰጥ የተዘጋጀ" እንግሊዝኛ ጽሑፍን አካትቷል። የ‹‹አሰብ የማን ናት?›› መጽሐፍ ደራሲ የሕግ ባለሙያ፣ መምህርና ጠበቃ ናቸው። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሩዋንዳን የዘር ጭፍጨፋ ጉዳይ አስመልክቶ በዐቃቤ ሕግነት ሠርተዋል። በናይጄሪያና በካሜሩን መካከል ተከሥቶ የነበረውን የድንበር ይገባኛል ጥያቄ ለመፍታት በሥፍራው

ከተሰማሩ ባለሙያዎች አንዱ ነበሩ። የሩዋንዳውን የዘር ጭፍጨፋ ተከትሎ በተቋቋመው ችሎት ውስጥ በዳኝነት ከተሳተፉ ባለሙያዎች አንዱ የነበሩ እና ለጉዳዩ ቅርበትና ዕውቀት የአላቸው ምሁር ናቸው። መጽሐፉ በእኒህ ደራሲ መዘጋጀቱ ጸሐፊው ለጉዳዩ ስለአላቸው ብቃት ይመሰክራል። የመጽሐፉ ዝግጅት በስሜት ሳይሆን በዕውቀት፣ በዐይን ምስክርነት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ጠቀሜታው የላቀ ነውና ይለያል ስንል በምክንያት እንጂ ያለ አመክንዮ አይደለም።

የ"አሰብ የማን ናት?ን መጽሐፍ ለአደባባይ መብቃት ተከትሎ ከሸገር ታይምስ ጋር ቆይታ የአደረጉትና ‹‹አሰብ የኤርትራ ግዛት፣ የኤርትራ አካል አልነበረም። ወደ ኢትዮጵያ መቅረት ነበረበት። ግን ጠያቂ አልነበረም።›› የአሉት ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ፖለቲከኛም ናቸው። ሪፖርተር ጋዜጣ "ልዩነትን በውይይት ከመፍታት ይልቅ የመጠፋፋትና የእልሸኝነት መንገድ መከተል በተመረጠበት የፖለቲካ ትግል ውስጥ ተሳታፊ መሆን ተጨማሪ ጥፋት ከመሥራት ውጪ ሌላ ፋይዳ እንደሌለው በመግለጽ ራሳቸውን ከፖለቲካ አመራር ሰጪነት "በቃኝ" በማለት መወሰናቸውን የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የውጪ ግንኙነት ሐላፊ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም ይፋ" አድርገዋል" ሲል እስከ አስነበበት ጊዜ ድረስ በጠንካራ ፖለቲካ ተሳትፏቸው ይታወቁ እንደ ነበር ይታወሳል። በቅንጅት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥም አባል፣ በጉራጌ ዞን ችሃ ምርጫ ክልል ተወዳድረው አሸንፈው እንደነበርም ይታወቃል።

## በማኅበራዊ ድረ ገፆች ሳይቀር:-

"ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ምሁር ሁሉ ራሱን ሸብቦ፣ የሕዝብ ጉዳይ አያገባኝም ባለበት ወቅት ሐሳባቸውን በአደባባይ ሲናገሩ ከነበሩት ጥቂት ምሁራን መካከል ግንባር ቀደሙ፤ ዜጎች ሲፈናቀሉ ጉዳያቸውን በነፃ ለፍርድ ቤትና ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ሲያቀርቡ የኖሩ ዕውቅ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ናቸው። እንደ አንድነት፣ ሰማያዊ፣ መኢአድ የመሳሰሉ ፓርቲዎች (ሁሉም ምርጫ ቦርድ ሳያፈርሳቸው) በጭቆናው ዘመን ሲንቀሳቀሱ ዶ/ር ያዕቆብ መካሪ ሆነው አገልግለዋል። የኢትዮ ኤርትራውን ጦርነት ተከትሎ በነበረው የአልጀርስ ክርክር በወቅቱ ገዥዎቹ የውጭ አገር ጠበቃ በውድ እንቅጠር ሲሉ ዶ/ር ያዕቆብ በነፃ ልከራከር ብለው አገር ወዳድነታቸውን ያሳዩ ሰው ናቸው።

"ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ስለ ዜጎች በነፃ ተከራክረዋል። ሌሎች ዝም በአለቡት ወቅት እሳቸው ስለ አገር ብዙ ብለዋል። ስለ ሕዝብ ስቃይ ተናግረዋል። ስለ ሕዝብ አብሮነት ሰብከዋል። "አሰብ የማን ናት?" ከእኚህ ሰው አእምሮ የተወለደች በመሆኗ፤ ጉዳዩን በቅርብና በጥልቀት በሚያውቅ ሰው ለመዘጋጀቷ ሕያው ምስክሮች ናቸው።

## ወደ «አሰብ የማን ናት?» (የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ) እንመለስ

አገራዊና ሕዝባዊ ጉዳትን፣ ከመጠቀም የአለፈ የባለቤትነት መብትን፣ ታሪክን ከሁሉም በላይ የሕግ ፅንሰ ሐሳብንና ሕጋዊ መደላድልን ተንተርሶ ለንባብ የበቃው ‹‹አሰብ የማን ናት?›› መጽሐፍ፤ "የአሰብ ጉዳይ የፈሰሰ ውሃ ሳይሆን የተዳፈነ እሳት ነው፤» የሚል ትንቢታዊ ሐሳብ የሰፈረበት መጽሐፍ በመሆኑ በመሰል ርእሰ ጉዳይ ላይ ከተዘጋጁ መጻሕፍት እጅጉን ይለያል።

አሰብን ማጣትና የባሕር በር ተጠቃሚ አለመሆን በኢኮኖሚ፣ በዲፕሎማሲና በፖለቲካው ዘርፍ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ዐይን ከሰበከት እያገላበጠ የአሳየ፤ ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን የፈተሸ መጽሐፍ በመሆኑ ከእስከ ዛሬዎቹ፣ ኢትዮጵያን ከተመለከቱና አሰብን አሳልፎ የሰጠውን ቡድን ከኮነኑ ሥራዎች ይለያል።

ከኤርትራ ጋር በታሪክም ሆነ በሕግ አግባብ የማትገናኘው አሰብ በስጦታነት

> በዓለም 44 ወደብ የሌላቸው ሀገሮች አሉ። ከ 44 ቱ የድሃ ድሃ የሚባሉት 13 ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። በመሆኑም ለኢትዮጵያ የወደብ አስፈላጊነት በጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም።

የቀረበችው ኢፍትሐዊ በሆነ አግባብ ነው። በተለይም አቶ መለስ በ1979 ዓ.ም. ኤርትራን አስመልክቶ በጻፉት መጽሐፍ፤ «ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ማለት ትክክለኛና ሳይንሳዊ ነው . . . ኢትዮጵያ የ3 ሺሕ ዓመት ታሪክ የላትም» ማለታቸውን በግልጽ የሚናገረው፤ የዶ/ር ያዕቆብ "አሰብ የማን ናት? መጽሐፍ እውነት እውነቱን እንድናውቅና ለታሪክ ፍርድም ይመች ዘንድ ፍንትው አድርጎ በማስቀመጡ ይለያል።

በአልጀርስ ስምምነት ወቅት ኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ዕድሏ ሰፊ የነበረ ቢሆንም ፍላጎት በአለማሳየቷ እንዳማረን የቀረ መሆኑን የሚነግረን «አሰብ የማን ናት?» መጽሐፍ በተዋቀረባቸው 13 ምዕራፎች በሙሉ ሞጋች ሆኖ በመቅረቡም ከጥንካሬዎቹ የሚደመር ነው።

ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ጦርነት (መጽሐፉን ጨምሮ ብዙዎች ትርጉም የለሽና አሳዛኝ ጦርነት ይሉታል) አድርጋ ከአሸነፈች በኋላ ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች ይዛ እንደ ነበር "አሰብ የማን ናት?» መጽሐፍ ያስታውሳል። ያንን ከፍተኛ ወታደራዊ ድል እና የማይገኝ ዕድል ጨብጦ አሰብን ለማስመለስ መጠቀም ሲገባ በአንድ ሰው ትእዛዝ መሠረት ያ ሊሆን እንዳልቻለ እና አገርና ሕዝብን ለከፋ ሐዘንና ኪሳራ የዳረገ፣ ብሔራዊ ጥቅምን ያሳጣ መሆኑን መጽሐፉ በማስረጃ ያቀርባል።

ኢትዮጵያ በታሪክ ውስጥ የነበራትን የባሕር በር ባለቤትነት መነሻ የአደረገ፤ ኢትዮጵያውያን በባሕር በር ባለቤትነታቸው ላይ የገጠማቸውን ተግዳሮትና የአደረጉትን መራር ትግል የዘከረ፤ የባሕር በር መኖርና አለመኖር በአንድ አገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚያስከትለውን ጥቅምና ጉዳት፣ በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ላይ የአለውን ሚናና ሌሎችንም የዳሰሰ፣ የኤርትራ መገንጠልን ተከትሎ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ አገር የመሆኗን ጉዳይ በስፋት የቃኘ፣ የኢትዮኤርትራን ጦርነት እና የአልጀርሱን የድንበር አከላለል ስምምነት . . . ወዘተ በጥልቀት በመመርመር እውነቱን ይዞ የቀረበም መጽሐፍ ነው።

በአሰብ ወደብ ጉዳይ ላይ በተለየ መልኩ የተለየ አጽንዖትን በመስጠት የአብራራ፤ በመግቢያው እ.አ.አ በታኅሣሥ 2000 ዓ.ም. በአልጀርስ የተፈረመው የወሰን መካለል ስምምነት አገራችን አሰብን የራሷ ግዛት የማድረግ ዕድል እንደነበራትና በኢትዮጵያ ድክመት ዕድሉ እንደአመለጠ በመግለፅ፤ በገጽ 9 ላይ "የኢትዮጵያን የባሕር በር ማስመለስ የሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ ብሔራዊ ግዴታ መሆኑን በማስረጽ፤ ይህም እንዲሆን እያንዳንዱ ዜጋ ዐቅሙ የሚፈቅደውንና የሚችለውን እንዲያደርግ፤ የሚል አገራዊ ጥሪን የአቀረበ ነው።

"በስምምነቱ ወቅት ኢትዮጵያን ከወከሉት ተደራዳሪዎች መካከል በሕግ አማካሪነትና በጥብቅና ዘርፍ የተሰማራ ኢትዮጵያዊ ሰው አልነበረም።" በማለት የዐይን ምስክርነታቸውን የሚሰጡት ደራሲው ዶ/ር ያዕቆብ «የድርድሩ ዋና አጋፋሪ ሚስተር አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ አልጄሪያ ከሻዕቢያና ከጀብሃ ጋር ለነበራት ግንኙነት ፓሊሲ ቀራጺና ለኤርትራ መገንጠል ሌት ተቀን የሠሩ ሰው መሆናቸው እየታወቀ በዝምታ ታልፏል» በማለትም ይገልጹታል።

የአልጀርሱን ውል ከወቅቱ የተዋዋዮቹ ዐቅም ልዩነት፣ ከውሉ ኢፍትሐዊነትና ሌሎችም መሠረታዊ ጉዳዮች አንጻር ውድቅ የሚያደርገው ይህ የዶ/ር ያዕቆብ መጽሐፍ፤ በድርድሩ ኢትዮጵያ 9 ሚሊዮን ዶላር መከስከሷንም በስላቅ እያነሣ «ወደው አይስቁ» እንል ዘንድ ያደርገናል፤ "አሰብ የማን ናት?" መጽሐፍ።

"ኢትዮጵያ የባሕር በሯ አሰብ እስከአልተመለሰላት ድረስ ኢሕአዴግ ከየትኛውም በጎም ይሁን መጥፎ ሥራዎች የባሕር በር ማዘጋቱ ከሁሉም በላይ ጎልቶ ይወጣል። አሰብ ለኢትዮጵያ እስከአልተመለሰ ድረስ ዘመናት አልፈው ዘመናት ሲተኩ በጊዜው ኢሕአዴግ ማን ነበር ሲባል መልሱ መንገዶችን፣ ትምህርት ቤቶችን ወይንም ሐኪም ቤቶችን የአነጸው አይሆንም። መልሱ «የኢትዮጵያን የባሕር በር የአዘጋው መንግሥት ነው የሚሆነው።» በማለትም መጻሐፉ ትንቢት ይነግረናል።

በመጀመሪያው አንቀጽ "ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች በአገር ውስጥ ብቅ ያሉ አምባገነን መሪዎች የጫኑባቸውን በደሎች ሰው ሠራሽም ሆኑ ተፈጥሯዊ ችግሮች በትዕግሥት ያስተናገዱ ሲሆን፤ ኢትዮጵያውያን በትዕግሥት የማይመለከቱት ነገር ቢኖር የድንበር መደፈርን ነው ማለት ይቻላል። የሚለው «አሰብ የማን ናት?» መጽሐፍ፤ እንዳለው ሁሉ ዛሬ ላይ ስለ አሰብ ጉዳይ ዳግም ምናልባትም ከፍ ለአለና ለተጋጋለ የውይይት ዐውድ ቆስቋሽ ሆኗል።

በወቅቱ በመጽሐፉ ላይ አስተያየታቸውን ይሰጡ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ጸሐፍት በርካቶች ነበሩ። የወርልድ ፕሬሱ ጸሐፊ "የዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ‹አሰብ የማን ናት?› መጽሐፍ ዶክተሩን የሚያስመሰግን፣ ኢትዮጵያውያንን የሚያነቃቃ ነው። መጽሐፉን እያነበብኩ እያለሁ ይሰማኝ የነበረው ስሜት በመዳን ላይ ያለ ቁስል ዳር ዳሩን ሲያኩት የሚሰጠውን ዓይነት ስሜት ነበር። (የምታውቁት ካላችሁ) በማለት የመሰከሩለት ከመሆኑም አኳያ እንመልከተው ካልን፤ አሁንም "አሰብ የማን ናት?" መጽሐፍን የተለየ ብቻ ሳይሆን፣ የሥነልቦና ሕክምና (ሳይኮቴራፒ) ሆኖ ሁሉ እናገኘዋለን።

"የኢትዮጵያና የኤርትራ ድንበር ማካለልን በተመለከተ ብያኔ የተካኼደበት የአልጀርሱ ስምምነት መሠረት የአደረገው የኢትዮ ጣልያን የቅኝ ግዛትን ስምምነት ነው" እንደሚሉት፤ እንደ ዶ/ር ያዕቆብ አገላለጽ በቀይ ባሕር፣ በተለይ በአሰብ የኑክሌር መሣሪያ ቢጠመድበትና የጠላት ጦር ቢሰፍርበት፣ ለህልውናችን ስጋት የሚፈጥር ሁኔታ ቢጠነሰስ ኢትዮጵያ ልታደርገው የምትችለው ምንም ነገር አይኖርም። ዐረቦች ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ብቸኛ የቀይ ባሕር ተቀናቃኛቸው የነበረችውን ኢትዮጵያ ከባሕሩ አካባቢ አግልለው ቀይ ባሕርን የዐረብ ባሕር ለማድረግ ሲታገሉለት የነበረውን ዓላማቸውን አሳክተዋል። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ደረቅ እውነቶችና በወቅቱ ኢትዮጵያ በገዛ ልጇቿ የተፈፀመባትን ደባና ክህደት ለትውልድ ግንዛቤ በሚያመች መልኩ ማቅረቡ ደራሲውን ከማስመስገንም ባለፈ ሥራቸውን ይበል ያሰኘዋል።

በኢትዮጵያ ላይ በፍጥነት የተሠራውን ሸፍጥም "የባሕር በርን የሚዘጋ፣ ባድመን፣ ኢሮብን፣ ጾረናን፣ ከፊል አፋርንና ሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶችን ለኤርትራ አሳልፎ የሚሰጥ ውዝግብ በ285 ቀናት ውስጥ መጠናቀቁ የጊዜ ሰሌዳውን አጠያያቂ ያደርገዋል። በሌላ በኩል ድርድሩ የተካኼደባት አገር አልጀርስ (አልጄሪያ) የኤርትራን መገንጠል ከጥንስሱ ጀምሮ ትደግፍ የነበረች ከመሆኗም ባሻገር የድርድሩ አጋፋሪ የነበሩት ሚስተር አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ (የወቅቱ የአ.አ.ድ ሊቀመንበር) ለኤርትራ መገንጠል የሃገራቸው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ የሠሩ ናቸው። ሌላው ቀርቶ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከኢትዮጵያ እንዲነሣ ጥረው አልተሳካላቸውም።" በማለት በ"አሰብ የማን ናት? ምዕራፍ ስድስት ሥር አስፍረውት፣ ለትዝብትም አብቅተውት እናገኛለን።

የ "አሰብ የማን ናት?" መጽሐፍ አዘጋጅ ዶ/ር ያዕቆብ "አሰብ ኢትዮጵያ ከአልተጠቀመችበት የግመል ውሃ ማጠጫ ይሆናል" የሚለውን የወቅቱ ባለሥልጣናት ሁኔታዎችን የአላገናዘበ አባባልም በአሁኑ ሰዓት የኤርትራ መንግሥት ወደቡን ለሳኡዲና ሌሎችም አገሮች አከራይቶት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። ይኽ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያንም ሉዓላዊነት ስጋት ውስጥ እንዳስገባውም ይገልፃሉ። ይህ ሁሉ ኢትዮጵያውያንን ሊያሳስብና ወደ መፍትሔም ሊሄዱ እንደሚገባ ያሳስባሉ።

ጸሐፊው ከሸገር ታይምስ ጋር ቆይታ በአደረጉበት ወቅት፤ «በቀጣናው ኃያላን አገሮች የጦር ሰፈር እየገነቡ ናቸው። አገሮቹ የጦር ሰፈር እየገነቡ ያሉት ደግሞ ኢትዮጵያ የወደብ አማራጮቼ በምትላቸው

አካባቢዎች ነው። ይኼ የኃያላን አገሮች እንቅስቃሴና ከበባ ኢትዮጵያን የት ድረስ ያሰጋታል?›› ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ:- “ምንም አያጠራጥርም፣ አሰብ ላይ ሳኡዲ ዐረቢያና ኢሚሬትስ የጦር ሰፈር ሠርተዋል። ከዚያም ግብጽ አሁን ሱማሌ ላንድ ላይ እንደዚሁ የጦር ሰፈር ለማቋቋም ውይይት እያደረገች ነው። ግብጽም ሆነ ሌሎቹ የዐረብ አገሮች ጅቡቲ ዉስጥ ብዙ እንቅስቃሴ አላቸው።

አንዳንድ ሰፈሮችንም ሠርተዋል። ከዚያም አልፎ ግብጽ ቀጣናውን አልፎ እንዲያውም ከደቡብ ሱዳን አንድ ስምምነት ተደርጓል። ስምምነቱ ምን እንደሆነ ብዙ ሰው አያውቅም። ስለዚህ አሁን ኢትዮጵያ ቀለበት ውስጥ ገብታለች። ተከባለች ማለት ነው። ስለዚህ በተከበበችበት ሁኔታ ከእነዚህ የጦር ሰፈሮች መሠራት በተጨማሪም ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ግብጽ አውሮፕላን ተሸካሚ የጦር መርከብ ገዝታለች። እና ይኼ ሁሉ ለምንድነው ግብጽ የአስፈለጋት? የሚለው ጥያቄ ሲነሣ የኢትዮጵያ ሁኔታ እዚያ ውሰጥ መግባቱ የሚያጠራጥር አይደለም። በማለት መመለሳቸውን ስናስተውል በጉዳዩ ላይ የጸና አቋም የያዙ ከመሆናቸው ባሻገር፤ ችግሩን በውል ከመረዳት አኳያ ከብዙዎች የተሻለ ዕቅም ያላቸው ምሁር መሆናቸውን እንገነዘባለን።

በምዕራፍ ሰባት ሥር ደግሞ በአልጀርሱ ድርድር ወቅት ኢትዮጵያን የወከለው ቡድን በአብዛኛው ይከራከር የነበረው ለኤርትራ ነበር። የኢትዮጵያ ድንበር በተሰረዘው “ውል መሠረት ከምሥራቅ 60 ኪ.ሜ ገባ ብሎ ስለነበረ የምሥራቅ ጠረፍ የሚባለውን ከደሴቶቹ ሳይሆን ባሕሩ ከሚያልቅበት የየብሱ ጫፍ እንዲጀምር ተከራክረዋል። ከዚህም በላይ ቡሬን ድንበር አድርጎ በማካለል ከ60 ኪ.ሜ በላይ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቀዋል። ኢትዮጵያን የወከለው ቡድን ጾረና የኤርትራ ነች ብሎ ድርቅ በማለቱ ካርታው ልዩ ቅርጽ ሠርቶ ጾረና ወደ ኤርትራ መከለሏ በካርታ ሳይቀር በመጽሐፉ ላይ ተመላክቷል።

በዚህ መንገድ ከጣልያን የተቀላቀለችው ኤርትራ ‹‹የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት›› ተብላ ስትገነጠል “ባለህበት እርጋ የተባለው የድኅረ ቅኝ ግዛት መርሕም አልተከበረም። የድንበር ኮሚሽኑ መሬቱን ሲያከፋፍል የተለያዩ የሰብአዊ መብቶችን (የዜግነት መብቶችን) እንዳሻው በመከፋፈል ጥሷል። የኢትዮጵያ ሰራዊትም በጦርነቱ ወቅት የአሰብ ወደብን መቆጣጠር ሲችል በገዢዎቻችን ትእዛዝ ወደ ኋላ አፈግፍጓል።

በአልጀርሱ የድርድር ሂደት የኢትዮጵያን ሽንፈት ዕውቁ ምሁር ፕሮፌሰር ክላፋም ‹‹ኢትዮጵያ ሽንፈትን ከድል መንጋጋ ፈልቅቃ አወጣች›› በማለት የገለፁት መሆኑን በዚሁ መጽሐፍና በዚሁ ምዕራፍ ላይ አስፍረውት ይገኛል።

ግራና ቀኝ በጠላት የተከበበቸው ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል የሚያስችል የጦር መሣሪያ ከውጭ በባሕር ማስገባት የግድ ይላታል። ይሁን እንጂ፣ ባለ ወደቡ አገር ከፈለገ ይህን ያህል ብቻ ይበቃሃል ብሎ ማስተላለፍ ላይ ገደብ ሊጥልበት ይችላል። እናም የሉዓላዊነት ጉዳይ ዘወትር በቋፍ ላይ ይንጠለጠላል ማለት ይሆናልና ልብ ያለው ልብ ይበል፤ አእምሮ ያለውም ያስብ ዘንድ አጥብቃ አሳስባለች፤ “አሰብ የማን ናት? መጽሐፍ።

> ## ኢትዮጵያውያን
> በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች በአገር ውስጥ ብቅ ያሉ አምባገነን መሪዎች የጫኑባቸውን በደሎች ሰው ሠራሽም ሆኑ ተፈጥሯዊ ችግሮች በትዕግሥት ያስተናገዱ ሲሆን፤ ኢትዮጵያውያን በትዕግሥት የማይመለከቱት ነገር ቢኖር የድንበር መደፈርን ነው ማለት ይቻላል።

እንደ ‹‹አሰብ የማን ናት?›› መጽሐፍ ከሆነ ወረራም ሌላው ስጋት ነው። ጄኔራል ናፒየር ዐፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት ወደ አገራችን የገባው በቀይ ባሕር ወደብ ነው። ወራሪዎች ከስትራቴጂክ አንጻር ከየብሱ ባሕሩን ይመርጣሉ። ምክንያቱ ደግሞ የቀለለ መሆኑ ሲሆን፤ መጽሐፉ ይህንንም እንድናስብ ማድረጉ ለየት የሚያደርገው ሆኖ፣ ስለ ዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነቱ ጉዳይ የሚመለከተው ሁሉ ቆም ብሎ ያስብ ዘንድ የሚያስገድድ ነጥብ በመሆኑ ሌላው የ ‹‹አሰብ የማን ናት?›› ጥንካሬና ብቃት ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

“. . . ኢትዮጵያ ያለወደብ ቀረች ብለን የምንቆጭበትና የምናዝንበት ምክንያት የለም፤ ከአሉት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና በ1983 ዓ.ም. “የአሰብ ወደብ ወደ ኢትዮጵያ መካለል እንዳለበት ታሪክም፣ ሕግም ያስገድዳል” (ምዕራፍ አራትን ይመለከቷል) ለሚለው ለፕሮፌሰር ዐሥራት

ወልደየስ አስተያየት "ታሪክና ሕግ የሚሉትን ዝባዝንኬ ለትምህርት ቤት ይተዉት፤ ይህ ፖለቲካዊ ጉዳይ በጦር ሜዳ ተፈትቷል።» በማለት መልስ ከሰጡት ኢሳያስ አፈወርቂ በተቃራኒ የቆሙትና "በአንድ ሰው (የመለስ) የዐይን ጥቅሻ ኢትዮጵያ በ60 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቀይ ባሕረ ሰላጤ ሙሉ ለሙሉ ተገለለች ከሚሉት (በ"አሰብ የማን ናት? ላይ እንደ ተጠቀሰው) ፕሮፌሰር ፀጋዬ መብራሕቱ ጋር የሚስማሙት ዶ/ር ያዕቆብ፤ የአልጀርሱን ጉድ (ስምምነት የሚሉትን) በተመለከተም "የድንበር ውዝግብ በሚፈጠር ጊዜ አገሮች ጉዳያቸውን ወደ ዓለም አቀፍ ፍ/ቤት ይወስዳሉ። ይህ ፍርድ ቤት የቅኝ ግዛት ውሎችን ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን፣ የተደረጉ ውሎችን፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን፣ የሕግ ልሂቃን የጻፏቸውን ጽሑፎች በሙሉ ይመለከታል። ሂደቱ ባለቀ ጊዜ ያልቃል እንጂ አያጣድፍም። (ከላይ "በ285 ቀናት ውስጥ . . ." ያልነውን ያስታውሷል) በማለት ያሰፍሩና የእኛኑ ጉድ አስመልክተውም፤ «ወደዚህ ፍ/ቤት መሄድ አልተፈለገም።» ሲሉ እውነቱን ወድደን ሳይሆን ተገድደን እንድንውጠው ያደርጉናል።

በተለይ በመጽሐፉ ምዕራፍ አምስት ሥር "እነዚህ [በ1900፣ በ1902 እና በ1908 በተፈራረሟቸው የኢትዮ-ጣልያን የቅኝ ግዛትን ስምምነቶች] ጥንታዊ ውሎች ኢትዮጵያ ላይ በጣልያን በግድ በመጣላቸው፣ ጣልያን ውሉን ጥሳ ኢትዮጵያን በመውረሯ፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጣልያን ቅኝ ግዛቷን በመነጠቋ እና ኢትዮጵያና ኤርትራ የኋላ ኋላ በመዋሐዳቸው በተደጋጋሚ የተሰረዙ ውሎች ናቸው። የኢሕአዴግ መንግሥት ግን ይህንን እውነታ ሽሮ በአልጀርሱ ስምምነት በኢትዮ-ጣልያን በተሻሩ ውሎች ለመቀጠል መስማማቱ በድንበር ማካለሉ ሥራ የወደብ ባለቤትነታችን ሊረጋገጥ ቀርቶ ቤተክርስቲያንና የመቃብር ቦታው፣ ከዚያም በላይ አንድ ትምህርት ቤት ለሁለት እንዲከፋፈሉ ሆነዋል።" የሚል ሰፍሮ መገኘቱ የ «አሰብ የማን ናት?» መጽሐፍን ዘመን አይሽሬነት ከወዲሁ ይናገራልና የደራሲው ሥራ ይለያል ስንል ያለ ምክንያት አይደለም።

ለባሕር በርና የባሕር በርን ለማስከበር ሲባል በዐፄ ዮሐንስ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ዐፄ ምኒልክ የተከፈለውን መሥዋዕትነት ብቻ ሳይሆን፣ በንግሥት ዘውዲቱ፣ በዐፄ ኃይለ ሥላሴና በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ሥርዓትም የባሕር በርን ለማረጋገጥ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ‹አሰብ የማን ናት?› መጽሐፍ ይተርካል። ከቅርብ ጊዜው ኢሕአዴግ በስተቀር የእስከ ዛሬዎቹ የአገሪቱ መሪዎች የአሰብ ጉዳይ የህልውና ጉዳይ መሆኑን በመረዳት ሲከፍሉ የኖሩትን መሥዋዕትነት የሚዘረዝረው ይህ መጽሐፍ ተግባሩን፣ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው «አንድም ስሕተት፥ ሲከፋም ክህደት» በማለት ያስቀምጠዋል።

ከርቀትና ቅርበት አኳያ አሰብን የመጠቀም ፋይዳን በተመለከተም "ኢትዮጵያ የምትከራያቸው የጎረቤት አገር ወደቦች ርቀታቸው ከአዲስ አበባ፣ ከ910 ኪ.ሜ. (ጅቡቲ) እስከ 1804 ኪ.ሜ. (ሞምባሳ) ይደርሳሉ። የአሰብ ወደብን ብንጠቀም ግን 640 ኪ.ሜ. ብቻ (ከኢትዮጵያ የአሁኑ ክልል ደግሞ 60 ኪ.ሜ. /የእግር መንገድ ርቀት/) ወይም ከጅቡቲ አንፃር የአንድ ቀን የመኪና ጉዞ መቅረብ ትችላለች" በማለት በመጽሐፉ ምዕራፍ አንድ ሥር ሰፍሮ ይገኛል።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፡ ". . . ኢትዮጵያ ያለወደብ ቀረች ብለን የምንቆጭበትና የምናዝንበት ምክንያት የለም። . . ." ሲሉ የተናገሩትን ከሥሩ በመናድ "ወደብ የሌላቸው ድሃ ሃገራት የውጭ ንግዳቸው ከ33 እሰከ 43 በመቶ ሊቀንስ ይችላል። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ ለወደብ ኪራይ በየቀኑ ከ 3 ሚሊዮን ዶላር (በዚያ ጊዜ ስሌት፤) ይህ የዶላር ቁጥር ዛሬ ስንት እንደሆነ ባናውቅም ከእጥፍ በላይ እንደሚሆን ግን መጠራጠር አይቻልም) ታወጣለች። ከዚህም በከፋ መንገድ በኢኮኖሚ ዕድገት አንድ ወደብ ያለው አገር በ24 ዓመት ኢኮኖሚው እጥፍ ማደግ ሲችል፣ ወደብ የሌለው ግን 36 ዓመት ይፈጅበታል። ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ከሆኑ አገሮች መካከል በሕዝብ ብዛት አንደኛዋ ስትሆን ብሔራዊ ደኅንነቷ በዚሁ ምክንያት ስጋት ላይ ወድቋል።" በማለት ገና በጠዋቱ፣ በመጽሐፉ ምዕራፍ አንድ በማስፈር ተቆጭተው ያስቆጫሉ።

በአንድ ወቅት ዶ/ር ያዕቆብ ከቢቢሲ አማርኛው ፕሮግራም ጋር በአደረጉት ቆይታ፤ "ጅቡቲ፣ ሶማሊያ እና ሶማሌላንድ የዐረብ ሊግ አባል አገሮች ናቸው። እነዚህ አገሮች እርስ በእርስም ቅርበት አላቸው። እንዲሁም ጅቡቲ ከበርካታ አገሮች ጋር ስትራቴጂካዊ ትስስርን ፈጥራለች።

"ወደቦቿን ቻይናዎች፣ እንግሊዞች፣ ፈረንሳዮች እና ግብጾች ይጠቀሙታል። ግብጽም ብትሆን ወታደራዊ ማዕከል በኤርትራ መሥርታለች። ይህ ብቻ ሳይሆን ግብጽ በደቡብ ሱዳንም ወታደራዊ ማዕከል አላት" በማለት መግለፃቸው የአሰብ ወደብን መጠቀም አለመቻል ሉዓላዊነትን አደጋ ላይ መጣል መሆኑን ከፍ አድርገው ማሳየታቸው እንደሆነ በወቅቱ ተነግሯል። ኢትዮጵያ እያንዳንዱ ውሳኔዋን ከጂኦፖለቲካዊ ጥቅም አንጻር መፈተሽ ያለባት መሆኑም እንደዛው።

ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን፤

**«ነገር በሆድ ማመቅ፣**
**ለትውልድ መርዝ መጥመቅ፤»**
**እንዳለው፤ ወይም ደበበ ሰይፉ:-**
**በትን ያሻራህን ዘር፣**
**ይዘኸው እንዳትቀበር።**

ሲል እንደአሳሰበው፤ ዶ/ር ያዕቆብም የሚያውቁትን በሆዳቸው መቋጠርና ለትውልድ መርዝ ማስቀመጥን ባለመፈለጋቸው ሊመሰገኑ ይገባል። ሥራቸውም ዐይን ገላጭ፣ ልብ አስደንጋጭ፤ ጊዜ ከማይሽረው (timeless/ ሊሆን መቻሉ ላይ መጠራጠር አይቻልም) ነውና ከሌሎቹ መለየቱ ላይ አጽንዖት ቢሰጠው ቢያንሰው እንጂ የሚበዛበት አይሆንም። በመሆኑም የአገር ባለውለታ ናቸው ብሎ መደምደም ያስችላል።

## በመጨረሻም ወደ ተሰነዘረው አስተያየት እንምጣ::

"በዓለም 44 ወደብ የሌላቸው ሀገሮች አሉ። ከ 44 ቱ የድሃ ድሃ የሚባሉት 13 ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። በመሆኑም ለኢትዮጵያ የወደብ አስፈላጊነት በጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። እንደሚሉት፤ እንደ «አሰብ የማን ናት?» መጽሐፍ ደራሲ አስተያየትና የመፍትሔ ሐሳብ አሰብን ሁለቱም አገሮች በጋራ ይዘውት ሁለቱም ጣምራ ሉዓላዊነት (joint sovereignty) እንዲኖራቸው ሊስማሙ ይችላሉ። ለዚህም ሕንድና ፓኪስታን የሚፋጠጡበት የካሽሚር ግዛት፣ ፈረንሳይና ስፔን ለ700 ዓመታት የሚያስተዳድሯትን አንዶራ የተባለች አገር በምሳሌነት ይጠቅሳሉ።

ሌላው የዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም የመፍትሔ ሐሳብ፤ "ከኤርትራ ጋር ሰላም መሥርቶ መደራደር ነው። ኤርትራ ከእናት አገሯ ኢትዮጵያ ጋር በ1952 በፌዴሬሽን ስትቀላቀል "የኢትዮጵያ ሕጋዊ የሆነ ወደ ባሕር የመዝለቅ መብቷ እንዲጠበቅ ኤርትራ በፌዴሬሽን ተቀላቅላለች" ይላል የተባበሩት መንግሥታት ሰነድ። ኢትዮጵያ ደኅንነቷን ለማረጋገጥ ከኤርትራ ጋር ተደራድራ አሰብ ወደብ ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ያስፈልጋታል" የሚል ነው።

በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ መካከል የሚፈጠር አለመግባባትም፤ ልክ እንደ እስከ ዛሬው ሁሉ በመነጋገር የሚፈታ እንደሆነ፤ የወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ ሊከሠቱ የሚችሉ አለመግባባቶች ወቅታዊ ሁኔታን የሚከተሉ በመሆናቸው ጥርስ የሚያናክስ እንደማይሆን የሚያሳዩ ጥናቶችና የባለሙያዎች አስተያየቶች መኖራቸውን በመጥቀስ በ «አሰብ የማን ናት?» መጽሐፍ ላይ ያለንን አስተያየት እናጠቃልላለን።

# ግብረ ሰዶም

## የትውልድ ጠንቅ፤ የዘመን ፈተና

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

በአገራችን በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየተስፋፋ መሄዱ ይነገርለታል። የምዕራባውያኑ ምክንያታዊ አመለካከትና የዘመን አመጣሹ ቴክኖሎጂ ተጽዕኖ ለድርጊቱ መበራከት ዋቢ ሆኖ ይጠቀሳል፤ ‹‹ግበረሰዶማዊነት››።

ሃይማኖታዊ መዛግብት እንደሚያስረዱት፤ የግብረሰዶም ታሪክ ከ 4 ሺህ ዓመታት በፊት በዮርዳኖስ ሸለቆ ከተቆረቆሩት ከተሞች አንዷ ከሆነችው የሰዶም ከተማ ይነሣል። በአቅራቢያዋ ትገኝ የነበረችው ገሞራም የዚሁ ታሪክ አካል ሆና ትጠቀሳለች።

በቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 19 የሰፈረው ቃልም ስለ ዘመኑ እውነታ በግልጽ ይጠቁማል። በዚህ ዘመን የሰዶምና ገሞራ ሰዎች ተፈጥሮና ሃይማኖት ከሚፈቅዱት የተቃራኒ ፆታ ግንኙነት የዘለለ ግብር ነበራቸው። በዚህ የኃጢአት ድርጊታቸውም ፈጣሪን በእጅጉ ያስከፉና ያሳዝኑ ነበር። ፈጣሪ ይኸንን ሐዘን ግን በዝምታ ብቻ አላለፈም።

ድርጊታቸው የእግዚአብሔርን ትዕግሥት በእጅጉ ተፈታተነ። አምላክ በራሱ ፍጥረታት እንዲያዝንና፣ እንዲቆጭም ምክንያት ሆነ። አብዝቶ የቆየው የእግዚአብሔር ትዕግሥት አንድ ቀን ተቋጨ። ሐዘን ቁጣው በእጅጉ አየለ። ይህ ብቻ አልበቃም። በሁለቱ ከተሞች ላይ እሳትና ዲን አዝንቦ ሰዎቻቸውን ከምድረ ገጽ አጠፋ።

‹‹ሰዶምና ገሞራ›› ይሏቸው ከተሞች ከጥልቅ የጨው ባሕር ተሸፍነው እስከ ወዲያኛው ጠልቀው ጠፉ። የከፋ ግብራቸው፣ ነውር የሚባል አሻራቸው ግን ዛሬም በስማቸው ታትሞ የዘመናችንና የትውልዱ ፈተና መሆኑን ቀጥሏል።

አቶ ብርሃኑ ራቦ የሞሽን ማማከርና ሥልጠና ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም የሕይወት ክህሎት አሠልጣኝ ናቸው። የአፈንጋጭነት ልማዶች በሁለት እንደሚከፈሉ ይገልጻሉ። ‹‹አዎንታዊና አሉታዊ አፈንጋጭነት›› በሚል።

አዎንታዊ አፈንጋጭነት፤ አንድ ሰው በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሚያየው እውነታ በመነሣት የራሱን አቋም ይዞ ‹‹እምቢኝ›› ሲል የሚያፈነግጥበት ሂደት ነው። ይህ ሰው እንዲህ ማድረጉ ፋይዳው ለአገርና ለወገን፣ ህልውና ለማኅበራዊ ሕይወትና ቀጣይ ግንኙነት፣ ለሰውልጆች ጤናማ መሠረት የሚረዳ እስከሆነ ማፈንገጡ ጤናማ ነውና አዎንታዊ ይሆናል።



አቶ ብርሀኑ ራቦ

ይህ እውነታ አመለካከትን በመገንባት፣ ሐሳብን በማቃናት፣ መልካምነትን በመዝራት የማኅበረሰቡ ጣራና ግድግዳ የመሆን ጥንካሬ አለው። ከዚህ ባለፈ አንድ ሰው ወይም ቡድን ለሞራልና የኅሊና ፍርድ፣ ለማኅበረሰቡ አኗኗርና ዘይቤ ተቃራኒ ሆኖ ማኅበረሰቡ የተሰፋበትን ድር የሚበጣጥስ፣ የቆመበትን መሠረት የሚንድ ሆኖ ሲገኝ ድርጊቱ በአሉታዊ ማፈንገጥነት ይገለጻል።

ይህ መሰሉ ማፈንገጥ ከማኅበረሰቡ ማንነት ተቆርጦ የመውደቅ ባሕርይ አለው። በአንድም በሌላ የማንነት ህልውናን በግልጽ የመጉዳት ልማድን ይከተላል። ድርጊቱ ከአስተሳሰብ ባለፈ በሰው ልጆች ጤናማ ሕይወት እንደጠንቅ ተፈርጆ የሚታይ ነው።

አቶ ብርሃኑ እንደሚሉትም፤ የዓለም ጤና ድርጅት ‹‹ጤና›› የሚለውን ትርጓሜ የሚያየው በአካል መታመም ላይ ብቻ አይደለም። ማፈንገጥ ይሉትን ልማድ የአንድ ሕመም መገለጫ አድርጎ በማስቀመጥ ጭምር እንጂ።

አንድ ሰው በንግግርና በአስተሳሰብ፣ በመንፈሳዊ ሕይወትና፣ በሞራላዊ ሁነት ከመደበኛ ማንነቱ አፈንግጦ ሲገኝ የጤናማነት ጸጋ አይኖረውም። በምትኩ ድርጊቱ ከሕመም ተፈርጆ በማፈንገጥ ባሕርይው ይገለጻል።

ይህ ዓይነቱ ልምምድ እንዴት ይመጣል? የሚለው ሲመረመርም ምላሹ ከብዙ አቅጣጫ ያደርሳል። አሁን የአለንበት ዘመን ዓለም በአንድ መስኮት የሚተያይበት፣ ሚስጥርና ገበናውን የማይደባበቅበት ጊዜ ነው። ይህ እውነታም አንዱ ማኅበረሰብ በሌላው ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድር ዕድሉን ያሰፋል።

በምጣኔ ሀብት፣ በፖለቲካና በቴክኖሎጂ ምጥቀት የበላይነት ያለው አካል ምንግዜም ለመደመጥ የበላይነቱን መውሰድ ይፈልጋል። ሁሌም የእሱ በሆነ ጉዳይ ላይ እንዲጨበጨብለት የማድረግ ኃይልም ከእሱጋር ነው። በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ የተናገረው እንዲጸድቅ፣ የተነፈሰው እንዲታመንለት ይፈልጋል። ማንም ከፊቱ እንዳይቆም የማስገደድ ጉልበቱም ኃያል መሆኑ ግልጽ ነው። አቶ ብርሃኑ እንደሚሉት ምዕራባውያን ማለት እንደዚህ ናቸው። ብዙዎችን በተለየ ተጽዕኖ ተብትበው የበታቾቻቸውን በመሸበብ መግዛትና፣ ማሸነፍን ይሻሉ።

ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ ለማኅበረሰቡ ሞራል፣ ባህልና ስሜት ያልተመቹና የአልተለመዱ አፈንጋጭ ድርጊቶች እንዲስፋፉ በር ከፋች ይሆናል። የሰው ልጅ እጅግ የተከበረ ፍጥረት ሆኖ ሳለ አፈንጋጭነትን በመለማመዱ ብቻ እንደ ዕቃ ይሸጣል፣ ይሸቀጣል።

ግብረ ሰዶማዊነት በመንፈሳዊና በታሪካዊ ሂደት የራሱ መነሻ አለው። አቶ አበራም ይህንኑ እውነታ በማስረጃዎች ያረጋግጣሉ። እሳቸው የዘመኑን ግብረሰዶም ሲገልጹት ድርጊቱ ታስቦበትና ታቅዶ በመከወኑ ከጥንቱ እንደሚለይ በማሳየት ነው።

ግብረ ሰዶማዊነት የሰው ልጆች ዘራቸውን እንዳይተኩና ሞራላዊ ማንነታቸውን እንዲጥሉ፣ መንፈሳዊ ኃያልነታቸውን እንዲያጡና ተፈጥሯዊ ጸጋቸውን እንዲነጠቁ ያደርጋል። ከዚሁ ተያይዞም ለአልተገቡ ዓላማዎች ተገዢ እንዲሆኑ የማስገደድ ኃይል አለው።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የበለፀገች አገር ናት። ዓለም የሚያውቃት ግን በኢኮኖሚ ዐቅም ኋላ ከሚባሉት ሀገራት ፊት ተሰልፋ ነው። ምንግዜም በሥልጣኔ የበለጸጉት ኃያላን በድህነት የሚገኙ አገሮችን ሊጠቀሙባቸው ዕድል ያገኛሉ። በዓለም የሚገኙ ክፉ አፈንጋጭ ድርጊቶችን ለመዝራትም በቀላሉ የሚመነዝሩት ዶላር ብዙ ርቀት ያራምዳቸዋል።



መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁ

ተፈጥሮን ተቃርኖ ያለወጉ መገኘት ‹‹ማፈንገጥ›› ተብሎ ብቻ የሚታለፍ አይሆንም። ይህ የነውር ድርጊት በጤና ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በእጅጉ የከፋ ነው።

በአገራችን ስጋት ሆኖ ለተጋረጠው ግብረሰዶማዊነት አንዱ ምክንያት ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ ስለመሆኑ ባለሙያው ይናገራሉ። አንዳንድ ሰዎች የተሻለ ዕውቀት ቢኖራቸው እንኳን በባዕዳን ምርኮ ለመያዝ ቅርብ ናቸው። ለአልተገባ ዘመናዊ እሳቤ መታለላቸውም ራስን ለሚያዋርድ፣ ባህልና እምነትን ለሚጥስ አፈንጋጭነት አሳልፎ ይሰጣቸዋል።

መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊና አነቃቂ መልእክቶችን በማስተማር ይታወቃሉ። የአፈንጋጭነትን ክፉ ባሕርያት በእጅጉ አነውረው፣ በጎ የሚባሉ አፈንጋጮችን ሲጠቅሱ ዛሬ ዓለማችን ለምትገኝበት ታላቅ ለውጥ ምክንያት መሆናቸውን በማስታወስ ነው።

እንዲህ ዓይነቶቹ ከሚሊዮኖች መካከል ተነጥለው በልዩነት ማፈንገጣቸው በርካታ በጎ ለውጦችን ለማምጣት አስችሏል።

የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ዘመን አንሥቶ ከሰማያውያን መላእክት፣ ከምድራውያን አራዊትና እንስሳት ተለይቶ አእምሮና ልቦና ተሰጥቶታል። ሰው ማለት ነፍስና ሥጋ ተዋህዶ የተሰጠ የወል ስም ስለ መሆኑ መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ይናገራሉ።

ሰው በስጋው ግዙፍ ነው። ይወልዳል ይዋለዳል፣ ይበላል ይጠጣል፣ ያገባል ይፈታል፣ ይታመማል ይሞታል። ከነፍስ አኳያ የሰው ልጅ ማንነት ሲቃኝም ሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች ይኖሩታል። ሰው በባሕሪው በበጎነት ሲቀረጽ፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ ርኅራኄ፣ ይቅርታን ይላበሳል። ይህ ዓይነቱ እውነታ ሁሌም ለነፍስ ምግብ ነው። በመልካም ይመዘገባል።

መጋቤ ሐዲስ እሸቱ እንደሚሉት እግዚአብሔር የሰው ልጅን ከፈጠረበት ጊዜ አንሥቶ እነዚህን ሁለት ባሕሪያት አስታርቆ እንዲኖር ሕግ ሰጥቷል። ይህ ሕግ ውስጣዊው ከውጫዊው ስሜት ተስማምቶ፣ እንዲጣመር የሆነ ነው። ወንድና ሴት በተፈጥሮ ማንነታቸው ፍጹም ይለያያሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ ፍላጎታቸው ጭምር በአንድ አይገለጽም። ይህ የሆነው እግዚአብሔር በሁለቱ መለያየት መሐል ሊፈጥረው የሚሻ ፍላጎት ስለአለ ነው።

አንዲት ሴት ወንድ ስታይ እንድትደነግጥ፣ ወንድም ሴቲቱን ሲመለከት በውበቷ እንዲሳብ የአደረገው የተፈጥሮው እውነታ ነው። እንዲህ መሆኑ ደግሞ በኃጢአትና ኃጢአተኝነት አያስፈርጅም። እንደመጋቤ ሐዲስ ገለጻ ይህ ጉዳይ የመሳሳብ ጸጋ ነው። ኃጢአት ሊሆን የሚችለው ይህን በተፈጥሮ የተሰጠን ጸጋ ያለቦታው ጥቅም ላይ የአዋሉት ከሆነ ነው።

ወንዱ የራሱን ጾታ ሲያይ ከደነገጠ፣ ሴቷም መሰሏን ስትመለከት ልውደድ ላፍቅር፣ ከአለች ድርጊቱ ክፉ አፈንጋጭነት ነው። እንደ መጋቤ ሐዲስ እሸቱ አባባል ሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎች በተፈጥሮ ቢለያዩም በአምላክ የተቸራቸው አካል አንዱ ለሌላው እንዲስማማ ሆኖ ተዘጋጅቷል። የዘመናችን ፈተና ግብረ ሰዶማዊነት ግን ይህን ሕግ በእጅጉ የሚጥስ ነው። የጥሰቱ መገለጫም ሰማያዊ፣ ማኅበራዊና ሰብአዊ መሠረትን የሚንድ ሆኖ ይገኛል።

የሴት ተፈጥሯዊ ጸጋ ዘርን መቀበል እንደመሆኑ ወንድም ዘርን እንዲያቀብል ሆኖ ተፈጥሯል። የዚህ ተፈጥሯዊ ሽግግር በተቃራኒው መተግበር ግን በግልጽ ተፈጥሮን መቃረን ነው። መጋቤ ሐዲስ እሸቱ እንደሚሉት ሴት ለወንድ፣ ወንድም ለሴት ብቻ እንዲሆኑ የተፈጠሩ ናቸው።

ተፈጥሮን ተቃርኖ ያለወጉ መገኘት «ማፈንገጥ» ተብሎ ብቻ የሚታለፍ አይሆንም። ይህ የነውር ድርጊት በጤና ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በእጅጉ የከፋ ነው። ሥነልቦናዊ ጉዳቱ የሚኖረው ስብራት ደግሞ በቀላሉ አይጠገንም። የሚያስከትለው ውስጣዊ ጸጸትም እንዲሁ።

መጋቤ ሐዲስ በዚህ ዓይነቱ ሕይወት ወደውና ፈቅደው ከሚያልፉት በርካቶቹ ጉድፈቻ ለመውሰድና ርዳታን ለመለገስ እጆቻቸው ሰፊ ነው። ከዚህ በስተጀርባ ሊኖር የሚችለው ድብቅ ተልእኮ እንዳለ ሆኖ አብዛኞቹ በዕድሜያቸው ማምሻ የሚከሠት ጭንቀትን ለማካካስ ሲሉ በጎነትን የሚከተሉ ናቸው።

ውስጣቸው የሚፈጠረውን ጫጫታ ለማስታገሥ በሚል በሚከፍቷቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችም «ግብረ ሠናይ» መባልን ይሻሉ። መጋቤ ሐዲስ እንደሚሉት ግን እንዲህ ዓይነቶቹ ድርጊቶች ጤናማና በጎ የሚባሉ አይደሉም። የፈጣሪን ሕግ በመጣስ የሰውን ምግባር የሚንዱና የሞራል ግጭት የተጠናወታቸው ናቸው።

በሠለጠነው ዓለም የምግብ፣ የልብስ፣ የመጠለያ ችግር የለም። ቴክኖሎጂው በሁሉም ሰው እጅ ለመድረስ ፈጣንና ቀላል የሚባል ነው። ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት ግን አብዛኞች በድብርትና ጭንቀት ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ለዚህ ዋንኛው ምክንያትም በርካቶች በግብረ ሰዶማዊነት ሕይወት የመገኘታቸው ምስጢር ነው።

መጋቤ ሐዲስ በእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ኃጢአት ምድራችን የተፈተነችበትን ክፉ አጋጣሚ በምሳሌነት ይጠቅሳሉ። በቅዱስ መጽሐፍ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው በምድራችን ታላላቅ የሚባሉ መቅሰፈቶች ወርደዋል። አንደኛው እግዚአብሔር በሰዶምና ገሞራ ሰዎች ተግባር ተቆጥቶ ምድርን በንፍር ውሃ የቀጣበት ነው።

ኢትዮጵያውያን ከምንታወቅበት ባህል ሃይማኖትና ነባር ትውፊት አኳያ ማንነታችንን ልንጠብቅ ይገባል የሚሉት መጋቤ ሐዲስ እሸቱ፤ አገራችን በአሁኑ ጊዜ በሚያስፈልጓት በርካታ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ልናተኩር ግድ እንደሚል ይጠቅሳሉ።

በአሁኑ ዘመን ለትውልዱ ፈተና ሆኖ የተጋረጠውን ግብረ ሰዶማዊነት ለመታገል የሃይማኖት አባቶችና ፖለቲከኞች፣ መንግሥትና ሚዲያ፣ ቤተሰብና ማኅበረሰብ በእኩል ተሳትፎ ሊንቀሳቀስ ይገባል። መጋቤ ሐዲስ እሸቱ በአትኩሮት ያስተላለፉት መልእክት ነው።

እንደ እስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ፤ አላህ የሰው ልጆችን ወደምድር ሲያመጣ ማንነታቸውን በተፈጥሮ ላይ መሥርቶ ነው። የእስልምና ሃይማኖት መምህሩ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ እንደሚሉትም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተሰጠው የሕይወት መመሪያና ሕግ ሰዎች በእምነትና ሥነ-ምግባር ታንጸው እንዲኖሩ ያስገድዳል።

ይህ ይሆን ዘንድም ሃይማኖታዊ መመሪያዎች ተደንግገዋል። መመሪያዎቹ የሰው ልጆች በሁሉም ዘመን፣ ቦታና ወቅት በሁለንተናዊ ማንነታቸው፣ ክብራቸውንና እምነታቸውን እንዲጠብቁ የሚያዙ፣ የሚያስገነዝቡ ናቸው።

እነዚህን እውነታዎች መሠረት የአደረጉ የፈጣሪ ትእዛዛት ደግሞ በሁሉም በኩል ጠቀሜታዎች አላቸው። እንደሕግ የተከለከለው ጉዳይም እንዲሁ ፍጥረቶቹን ከጉዳት የሚጠብቅና የሚታደግ ነው። ኡስታዝ እንደሚሉት፤ በእስልምና ሃይማኖት ሕግ ጋብቻ ከተቀደሱ ተግባራት መካከል አንደኛው ነው። ፈጣሪ በፈቀደው አግባብ የሚደረጉ ግንኙነቶች መልካም ትስስር አላቸው። መውለድ መዋለድ፣ ራስን መተካት ይኖራልና እውነታዎቹ በቅድስና መዝገብ በክብር ተጽፈዋል።

“

**በቅዱስ ቁርዓን** እንደተገለጸው፤ የሎጥ ዘመን ሕዝቦች የፈጣሪ ቁጣ የወረደባቸው ነበሩ። በዘመኑ የፈጸሙት ጸያፍ ድርጊት ለኃጢአታቸው ማሳያ ለትውልዳቸው መቀጣጫ ሆኗል።



ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ

ከዚህ በተቃራኒ የሚታወቁ ልቅ ግንኙነቶች ነባሩን ማንነት የሚያጠፉ፣ የተወገዙና፣ የተጠሉ ናቸው። በእስልምና ሃይማኖት ሕግ በእንዲህ ዓይነቱ ጸያፍ ድርጊት የሚሳተፉ ቢኖሩ በእምነቱ ከፍተኛ ተብለው ከሚታወቁ ወንጀሎች መሐል አንዱን እንደፈጸሙት ይቆጠራል። እነሱም እንደ ከባድ ወንጀለኞች ይታያሉ።

እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ድርጊታቸው በእነሱ ብቻ አይቆምም። የተወገዘ ተግባራቸውን ወደሌሎች ሊያጋቡ ይፈጥናሉ። ኡስታዝ እንደሚሉት፤ በእምነቱ የተቀመጠው ሕግ ድርጊታቸውን በዝምታ የሚያልፍ አይደለም። ስለ ኃጢአታቸው ዋጋ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያዛል።

በቅዱስ ቁርዓን እንደተገለጸው፤ የሎጥ ዘመን ሕዝቦች የፈጣሪ ቁጣ የወረደባቸው ነበሩ። በዘመኑ የፈጸሙት ጸያፍ ድርጊት ለኃጢአታቸው ማሳያ ለትውልዳቸው መቀጣጫ ሆኗል። በእስልምና አስተምህሮት ይህ ታሪክ ለእምነቱ ተከታዮች ታላቅ ማስተማሪያ ይሆናል። በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚንጸባረቅ አፈንጋጭ ልማድ፣ ተፈጥሮን የሚቃረን ነው። የሰው ልጆችን ጤናማ ግንኙነት የሚሰብር በመሆኑም ተሞክሮው ለማንም ጠንቅ ይሆናል።

ድርጊቱ ተፈጽሞ ሲገኝ የማያዳግም ርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በቁርአንና የሐዲስ ትውፊት መመሪያ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል። በሼርያ ሕግም

እስከ መገደል የሚያደርስ የሞት ፍርድ ውሳኔ አለው።

የገደብ አልባ ነጻነቶችን መስፋፋት ከታላቅ ስጋት የሚቆጥሩት ኡስታዝ አቡበከር ለዚህ ስጋት ልጓሙ ሥነ ምግባር መሆኑን ይናገራሉ። እንደ እሳቸው እምነት አፈንጋጭነት ተፈጥሯዊ ባለመሆኑ ለሥነ ምግባር ተገዢ አይደለም። ለማኅበረሰባዊ ግንኙነቶችና ለጤንነትም አደጋ ይሆናል።

በእስልምና ሕግ ራስንም ሆነ ሌሎችን መጉዳት ፈጽሞ የተፈቀደ አይደለም። በተፈጥሮ የተሰጠን ጸጋ አክብሮ መያዝም አንዱ ግዴታ ይሆናል። በአግባቡ ከተቀመጠው እሳቤ መውጣት ደግሞ ሕግን መጣስ፣ መመሪያን መተላለፍ ነው።

ዛሬ ከሌሎች ዓለማት አልፎ በአገራችን ስጋት መሆን የጀመረው ግብረሰዶም ለትውልድ ጠንቅን የሚያወርስ ተግባር ነው። ኡስታዝ እንደሚሉት ከአደጉት አገሮች መውሰድ የሚገባን በርካታ በጎ ተግባራት አሉ። ይህን እውነት ተሻግሮ የማንነትን ዕሴት፣ ትውፊት፣ እምነትና፣ ባህል የሚጋፉትን ክፉ ድርጊቶች እጅ ዘርግቶ መቀበል መልካም አይደለም። ይህ ምርጫ ከሆነ ግን የትውልዱን አደጋ የሰፋ ያደርገዋል።

በእስልምና የሺሪያ ሕጎች መሠረት የሚዳኙ ጥፋተኞች ሁሉ ሌሎችን ለማስተማር ምክንያት ናቸው። ቃሉ የሚያስተምረውም «እናንተ አስተንታኝ የሆናችሁ የዓዕምሮ ባለቤቶች ተፈጥሮን በሚያዛቡ ሰዎች ላይ በሚወሰዱ ርምጃዎች ሕይወት አላችሁ» ሲል ነው።

የገደብ አልባ ነጻነቶችን መስፋፋት ከስጋት የሚቆጥሩት ኡስታዝ አቡበከር ለዚህ ስጋት ልጓሙ ሥነ ምግባር መሆኑን ይናገራሉ። እሳቸው ሥነ ምግባር የሌለው ማኅበረሰብ እንደወደቀ ይቆጠራል ባይ ናቸው።

የነብዩ መሐመድ አስተምህሮትና ሁሉም ነብያቶች የሚስማሙበት አንድ መመሪያ አለ። «የምታፍረው ከሌለ ሁሉንም ነገር ሥራ» የሚል ቃል። ይህ ቃል በሰው ልጅና በፈጣሪ መካከል ያለውን ግርዶሽ እያሳየ ሥነ ምግባርን የሚያስተምር ነው።

እንደ ኡስታዝ አመለካከት በዓለማዊ ሕግ ላይ የሚኖረው ቅጣት የማያዳግም መሆን አለበት። እንዲህ መሆኑ ትውልድን ለመታደግ፣ ማንነትንም ለማትረፍ ያግዛል።

ከሃይማኖት አስተምህሮቶችና፣ ቤተ እምነቶች ጥረት ባሻገር የትምህርት ሥርዓቱ በወጉ ሊጠናና ሊፈተሽ ይገባል። ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብና አካባቢ በትውልድ ሥነ ምግባር ላይ አበክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። የኡስታዝ አቡበከር መሐመድ ምክር ነው።

> በእስልምና ሕግ ራስንም ሆነ ሌሎችን መጉዳት ፈጽሞ የተፈቀደ አይደለም። በተፈጥሮ የተሰጠን ጸጋ አክብሮ መያዝም አንዱ ግዴታ ይሆናል።

ፓስተር ቸርነት በላይ የጋብቻ አማካሪና የወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መሪ ናቸው። ፓስተር ቸሬ የአፈንጋጭነትን ድርጊት ከሃይማኖትና ባህል አኳያ ሲቃኙት የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ያስቀድማሉ። እሳቸው እንደሚሉት ይህ ዓይነቱ አፈንጋጭነት ከተፈጥሮ ጋር ፍፁም ማመፅን ያመላክታል።

ድርጊቱ ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ ከመሆኑ ባሻገር ራሱን ተፈጥሮ እንደማጥፋት ጭምር ይቆጠራል። እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥር «ብዙ ተባዙ» በሚል ዘርን ለማስቀጠል፣ ሕይወትን ሥርዓት ለማስያዝ ነው። የሰው ልጆች ይህን ሕግ መተላለፋቸው ደግሞ በፈጣሪያቸው ላይ እንደማመፅ ይቆጠራል።

ፓስተር ቸሬ አፈንጋጭነትን ከአገራችን ባህል አኳያ ሲያጤኑት ድርጊቱ በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት እንደሌለው በማሳየት ነው። አምላክ በአልፈቀደው ፆታዊ ግንኙነት ያለ ወጉ ሆኖ መገኘት በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ጠብ ያሳያል። ይህ እውነት ሲመረመርም ፓስተር ቸሬ ደጋግመው እንደሚሉት የሰው ዘርን እንደ ማጥፋት ነው።

ለዚህ ድርጊት መስፋፋት በዋነኛነት የሚጠቅሱት ምክንያት የመንፈሳዊነት መሰንጠቅን ነው። በእሳቸው እሳቤ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ዝቅጠት ውስጥ በሚገባ ጊዜ ይህ ዓይነቱ ድርጊት አንዱ ማሳያ ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ የሮሜ ሰዎች ምዕራፍ 1 ላይ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱ መጠን ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ተጠቅሷል።

እንዲህ ዓይነቶቹ በዋንኛነት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላሽቀው ከፈጣሪ በሚያጋጭ ሐሳብ ላይ ሲገኙ ለዚህ ዓይነቱ ድርጊት እጅ ይሰጣሉ። የሰው ልጅ አምላኩን የማያውቅ፣ በሥርዓት የማይኖርና ያለገደብ የሚኖዳ ከሆነ ክቡር የሚባለው ፍጡር እንደ እንስሳ የሚሆንበት ዕድል ይፈጠራል።

እኛን በመሰሉ የአፍሪካ አገሮች የምዕራባውያንን ሥልጣኔ እንደ ፈጣሪ ስጦታ አምኖ የመቀበሉ ልማድ ተበራክቷል። ይህ ዓይነቱ ተጽዕኖ ውድቀታቸውን ጭምር በእኩል እንድንቀበል እያስገደደን ነው። ፓስተር ቸሬ እንደሚሉት እኛ ከእነሱ እየወሰድን ያለው ሥልጣኔያቸውን

ብቻ አይደለም። ከዚህ በስተጀርባ እኛነታችንን፣ ነባር ዕሴቶቻችንን፣ እምነት ባህላችንን እየተነጠቅን መሆኑ ጭምር መታወቅ አለበት።

ፓስተር ቸሬ በዘመናችን አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሚስተዋለውን የወንድና ሴት ትምህርት ልየታን ፈጽሞ አያምኑበትም። በእሳቸው የሕይወት ተሞክሮም በልጃቸው የትምህርት ቤት ቆይታ ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ አግኝቷቸዋል። እሳቸው ወንዶች ከሴቶች፣ ሴቶችም ከወንዶች ተለይተው መማራቸውን አይፈቅዱትም። ይህ ዓይነቱ ልምምድ ልጆች ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ ግንኙነት ውስጥ እንዲገቡ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል ከሚል ስጋት አድርሷቸዋል።

አንዳንዴ ያለገደብ የሚኖር ቅርበትም ለአልተገባ ግንኙነት አሳልፎ ይሰጣል። በዚህ ጉዳይ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር በግልጽ መሞገታቸውን ጭምር ያስታውሳሉ።

በአፈንጋጭ ባሕሪያት ላይ የክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ ሰዎች ፈጣሪን እንዲያውቁ ከማድረግ እንደሚጀምር ፓስተር ቸሬ ይገልጻሉ። የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ማለት የእግዚአብሔርን ሐሳብ በማክበር፣ ዘርን ማስቀጠል ስለመሆኑ ማሳወቅ ግድ ይላል። ትምህርቱ ያለአንዳች መሸፋፈን ግልጽና ቀጥተኛ ሆኖ መድረስ አለበት። ችግሩን እያወገዙ ማስተማርም ጉዳዩ በተከሠተ ጊዜ ከሚኖር መሯሯጥና ግራ መጋባት ይታደጋል።

የአፈንጋጭነት ድርጊት አዲስና አሁን ላይ ብቻ የተከሠተ አይደለም። እስከዛሬም በበርካታ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ስለመኖሩ መረጃዎች ያረጋግጣሉ። ጉዳዩን ምስጢር በማድረግ በዝምታ የመሸፋፈኑ ሐቅ ግን ኅብረተሰቡን ዋጋ እያስከፈለው ነው። በአንድም ይሁን በሌላ በዚህ አጋጣሚ ያለፉ በርካቶች ስሜታቸው የተጎዳ፣ ውስጣቸው የተሰበረ ነው። ፓስተር ቸሬ ይህ ዓይነቱን እውነታ በአንድ ማሳያ ያረጋግጡታል።

ጉዳዩ ከአንዲት ወላጅ እናት ጋር ይያያዛል። በቅርቡ ነው። በውጭ አገር የምትኖር ሴት ነች። የዓሥራስድስት ዓመት ልጅ አለቻት። ልጅት ከቀናት በአንዱ ለእናቷ እንደእሷ ሴት የሆነች ባልንጀራዋን የፍቅር ‹‹ጓደኛዬ›› ስትል አስተዋወቀቻት።

ሁሌም ይህ ዓይነቱ እውነት የወላጆችን ቅስም ይሰብራል። በተቃራኒው ደግሞ በዚህ ሕይወት ውስጥ የሚገኙትን ‹‹መብታችን›› ነው ሲሉ አደባባይ እንዲወጡ ጉልበት ይሰጣል። ፓስተር ቸሬ ይህ ሁሉ የሆነው እውነታዎች በምስጢርና በማለባበስ መያዛቸውና እንደዋዛ መታለፋቸው ነው ይላሉ።

ለዚህ መሰሉ ነውርነት ምክንያቱ የፈረሰ መንፈሳዊ ማንነት፣ የአልበረታ ማኅበራዊና ቤተሰባዊ ግንኙነት ነው። ይህ ችግር እንደ ሰደድ እሳት እንዳይስፋፋ የሃይማኖት ተቋማትና ቤተሰብ አበክረው ሊተጉ ይገባል።

ፓስተር ቸሬ በግብረሰዶም የአፈንጋጭ ባሕርይ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በመድኃኒትም ይሁን፣ በመንፈሳዊ ሕክምናው መታገዝ እንዳለባቸው ያምናሉ። የሃይማኖት ተቋማት ድርሻ እንዳለ ሆኖ ኅብረተሰቡ ለራሱ ነባር ዕሴት ሊታዘዝ፣ መንግሥትም ተገቢውን ሕግ በአግባቡ ሊያስፈጽም ግድ ይላል።

በአዲስ አበባ ፖሊስ የሕዝብ ግኙኙነት ዳይሬክተር ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ ግብረ ሰዶማዊነት ከኢትዮጵያ ሕግ አኳያ ወንጀል መሆኑን ይገልጻሉ። በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ከአንቀጽ 6 ፡ 29 እስከ 31 እንደተደነገገው ድርጊቱ ወንጀል መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚያስከትለው ተጽዕኖ ጭምር በግልጽ ሰፍሯል። ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ሕጉን



ፓስተር ቸርነት በላይ

**እግዚአብሔር**
ወንድና ሴት አድርጎ
ሲፈጥር ‹‹ብዙ ተባዙ››
በሚል ዘርን ለማስቀጠል፣
ሕይወትን ሥርዓት
ለማስያዝ ነው።

> በከተማዋ በድብቅ የተከፈቱ አንዳንድ ቤቶች የግብረ ሰዶም ማካሄጃ መሆናቸው ተደርሶበት ሕጋዊ ርምጃ ተወስዷል።



ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ

አጣቅሰው እንደሚሉት ይህ ተጽዕኖ አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ፣ አእምሯዊና ለንጽሕና ክብር ተቃራኒ የሚባል ነው።

በዚሁ አንቀጽ ላይ በአጽንዖት እንደተጠቀሰው ግብረ ሰዶም ለተፈጥሮ ባሕርይ ተቃራኒ መሆኑ በተለይ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ሕፃናት ላይ ውጤቱን የከፋ ያደርገዋል። በአገራችን የግብረ ሰዶማዊነት ወንጀል እየተስፋፋ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን የሚጠቅሱት ዳይሬክተሩ ለድርጊቱ መበራከት ምክንያት ናቸው የሚባሉትን እውነታዎችን ጭምር ይጠቁማሉ።

እንደ ኮማንደር ማርቆስ እሳቤ ይህ ከኢትዮጵያዊ ማንነት ያፈነገጠ፣ በነውርነት የሚፈረጅ ድርጊት እንዲስፋፋ ሰበቡ የባዕዳን ተጽዕኖ ነው። ከዚሁ ተያይዞ ትውልዱ የማኅበራዊ ሚዲያ ጥገኛ የመሆኑ አጋጣሚ ለሁኔታዎች መመቸት ዕድል ፈጥሯል።

ይህን በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀልነት የሚፈረጅ ድርጊት ብዙኃኑ እንደ ቀልድ በማየት በምንቸገረኝነት ማለፉ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል። የዚህ ግዴለሽነት መደጋገም ለወንጀሉ መበራከት ዋነኛ ምክንያት ስለመሆኑም ኮማንደሩ ያስረዳሉ። በአንዳንድ ወጣቶች ዘንድ ድርጊቱን የዘመናዊነት መገለጫ አድርጎ የመውሰድ እሳቤ አለ።

ኮማንደር ማርቆስ ግብረ ሰዶም ወንጀል በመሆኑ በድርጊቱ የተጠረጠሩትን በሕግ አግባብ መያዝ የፖሊስ ተቀዳሚ ተግባር መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህ ባሻገር ፖሊስ በወንጀሉ ድርጊት የተፈረደባቸውን ሰዎች አስተማሪ የሕግ ውሳኔ ይፋ የማድረግ ሐላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።

ለፖሊስ ከሚደርሰው መረጃ ለማወቅ እንደሚቻለው በአብዛኛው የግብረ ሰዶም ወንጀል የሚፈጸመው በሕፃናት ላይ ነው። ድርጊቱ በዐዋቂዎችም ላይ ይፈጸማል። ኮማንደሩ እንደጠቆሙት በከተማዋ በድብቅ የተከፈቱ አንዳንድ ቤቶች የግብረ ሰዶም ማካሄጃ መሆናቸው ተደርሶበት ሕጋዊ ርምጃ ተወስዷል።

ኮማንደር ማርቆስ ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ተቃራኒ በሆነ ድርጊት መገኘት ወንጀል እንደመሆኑ በሕግ አግባብ ሊዳኝ እንደሚገባ ያሠምሩበታል። በዚህ ነውርነት የሚገኙ ሰዎች ሲያጋጥሙም ኅብረተሰቡ ተገቢውን መረጃ ለፖሊስ ማድረስ ይጠበቅበታል።

ወላጆች፣ መምህራንና መላው ኅብረተሰብ የወንጀሉን መስፋፋት ለማስቆም እጁ ሊተባበር ግድ ነው። ይህ የወንጀል ድርጊት በዝምታና ቸልተኝነት ሲታለፍ ችግሩ የሁሉንም በር ያንኳኳልና። የኮማንደር ማርቆስ ታደሰ መልእክት ነው።

# ብርሃን

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

> ከብዙ ቀናት በኋላ አንድ ረፋድ ውስጤ የሚመላለስን ሐሳብ ተከትዬ ከቢሮዬ ወጣሁ። እንደነገሩ ነው የለበስኩት። የመሥሪያ ቤታችን እብድ መሳይ ሠራተኛ ነኝ። በዚህ ዝርክርክነቴ እዛች ጣኦት መሳይ ቆንጆ ሴት ፊት ስቀርብ ደፋርነቴ ነው የሚመጣብኝ።

እግዜር ግን ለሴትነት አዳልቷል። እውነት አዳልቷል..። ካልሆነ በአጠገቧ ሳገድም ለምን ትገዝፍብኛለች?

በሴትነቷ ፈር ውስጥ የብርሃን ጎርፍ ይንፎለፎላል። በምሽት ጉያዋ ውስጥ ምስል አትማ እንደምትንፏቀቅ ጨረቃ የብርሃን ምንጭ ከቀይ ፊቷ ላይ ይፈልቃል። እንደአራስ ገላ ከሊጥ የተማሰለ የሚመስል፣ እንደመስተዋት ርቃን ብርሃን የሚያስተላልፍ ውብ ፊት እግዜርን የማማበት ተፈጥሮዋ ነው። በክረምት ጎሾ በዳመነ ሰማይ ደረት ላይ እንደሚብለጨለጭ የመብረቅ ብልጭታ ሲያዩዋት ነፍስ ታዘማለች። ትካዜዬ ወንዝ የሚሻገረው በእሷ ነው። በአየኋት ቅጽበት ቀን ሙሉ የምተክዘው ትካዜ አለኝ።

ብርሃናማ ናት..እንደጨረቃ። የውበት ጸዳል የሚንቦገቦግበት ፊት። ሰው ሆኖ ብርሃናማ መሆን ይቻላል? ሁሌ ከእጇ የማይጠፋው የአፈንጋጩ የኦሾ ፍልስፍና እንኳን የእሷን ውበት ያክል አላስለፈለፈኝም። ማማር ስትወድ። አንድም ቀን ከላመል ጉድፍ ጋር አላየኋትም። ደሞ ዘናጭ ናት..ከሰውነቷ ጋር ያበሩ፣ ውበቷን ያጎሉ ደመቅማቃ ልብሶች ታዘወትራለች። ጸጉሯ አጭር ነው..ፊትሽ ለአጭር ጸጉር የሚሆን ነው ተብላ ረጅም ጸጉሯን ያሳጨደችው ይመስለኛል። ብርሃናማ ፊት ከብርሃናማ ዐይኖች ጋር ፊት ለፊቴ ሲደነቀሩ አልደነባበርም፤ ለቀን ሙሉ የሚሆነኝን የሐሳብ ስንቅ ከውብ ፊቷ ላይ እቃርማለሁ። የሆነ ልማድ አላት..አንድን ሰው ለረጅም ጊዜ የማየት። በዛ ዐይንና ውበት ለረጅም ጊዜ መታየትን ዳዋውን አስቡት? በውበቷ በኩል ስርየት የሌላቸውን ትላልቅ ኃጢአቶችን ሠርቻለሁ። ካህን ፊት ቀርቤ ብናዘዛቸው መዳኛ የማላገኝባቸውን ኃጢአቶች። ጸንቼ ሰንብቼ መሰነካከያዬ የእሷ ፊት ነው።

ምናን ከምን አወዳድሬ እንደማተልቅ ባላውቅም ዐይኖቿ በውበቷ ሰማይ ላይ ብርሃንን የሚረጩ የሴትነቷ ማሾ ይመስሉኛል። ከፀሐይ የተዛመደች ይመስል፣ ከተሲያት የተቆራኘች ይመስል በዐይኖቿ በኩል የሚፋጅ ተፈጥሮ አላት። እንደዛ ባያምሩ በዛ ልክ አትወደስም የሚል ሐሳብ ይመጣልኛል። ሰንብቶ ደግሞ ከተፈጥሮዋ ላይ ግማሹ ቢደበዝዝ በውበት ማንም አይበልጣትም፤ የሚል ሞጋች ሐሳብ ይፈጠርብኛል። ሰማይ ላይ ተንጠልጥላ ዓለምን እንዳወገገችው ጨረቃ ለልቤ ከተማ ፀሐዬ ናት።

ስትለብስ ዝርክርክ ናት ልበል? እንጃ እርግጠኛ አይደለሁም..። ከአለባበሷ ተርፎ አሊያም ተዛንፎ ወይ ባቷን ወይ እንብርቷን ወይ ገላጣ ጀርባዋን፣ ወይ ደረቷን፣ ወይ የወገቧን ዙሪያ ሳላየው ቀርቼ አላውቅም። በቋፍ ላለ ለእኔ ዓይነቱ ልክፍተኛ ያን ውብ ገላ ማየት ሌላ ፈተና ነበር። በአየሁት የሆነ ነገሯ ሁሉ ምራቄን እውጣለሁ። የሴት ገላ አይቼ ለጉሮሮዬ ዕዳ የሆንኩበት በእሷ ውበት ነው።

የከፋው ነገር እኔን አትወደኝም። አንድ ቢሮ ውስጥ ለዓሥር ስንሠራ የማታወራው ከእኔ ጋር ብቻ ነው። ዓለም ላይ የሰው ልጅ ሁሉ አልቆ እኔና እሷ ብቻ ብንቀር የምትጎራበተኝ አይመስለኝም። እኔ ፊትና ሌሎች ወንዶች ፊት ሁለት ዓይነት ናት። የምትደናበረውና የምትመናቀረው እኔን ስታይ ነው። አንድ ቀን ቀናኝ..ፊትለፊቴ ተረከዛማ ጫማዋ ተበጠሰ። በሁለት እጅዋ እንደእሷ መንገደኛውን የሚያስቀላውጡ መልከኛ ፔስታሎችን አንጠልጥላለች። (እገምታለሁ ልብስ ነው የያዘችው። በየሳምንቱ ዓርብ በሥራ በኩል ገበያ ወጥቶ የአማራትን የመሸመት አመል አላት) ተረከዛማ ጨማዋ ተበጠሰ። እኔን ርዳታ ከመጠየቅ ውጪ ምንም ምርጫ እንደሌላት በማሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ የምታወራብትን አጋጣሚ በኩፈሳ ስጠብቅ እግሯን እየጎተተች አልፋኝ ሄደች። እንደዚህ የጠላችኝ ምን በድያት ነው? ወደሚል የሐሳብ አዘቅት ተወረወርኩ።

ከብዙ ቀናት በኋላ አንድ ረፋድ ውስጤ የሚመላለስን ሐሳብ ተከትዬ ከቢሮዬ ወጣሁ። እንደነገሩ ነው የለበስኩት። የመሥሪያ ቤታችን እብድ መሳይ ሠራተኛ ነኝ። በዚህ ዝርክርክነቴ እዛች ጣኦት መሳይ ቆንጆ ሴት ፊት ስቀርብ ደፋርነቴ ነው የሚመጣብኝ። ከአእምሮ እንጂ ለአካል ግድ የለኝም።

ማሰብ እወዳለሁ። በሆነ ርእሰ ጉዳይ ላይ መወያየትና መከራከር የምዝናናበት ተፈጥሮዬ ነው። አንዳንዶች አለባበሴን አይተው በሩቁ የማይረባ ያደርጉኛል። የተረዱኝ ደግሞ በግድም ለወዳጅነት ይመርጡኛል። እንደእኔ ነፍሱን በሐሳብ ያከሳ ሰው አላውቅም። አእምሮ አፍ ቢኖረው በአግባቡ የተጠቀመብኝ ሰው ብሎ ይኩራራብኝ ነበር። እኔ ስወጣ ጀምበር ስትገባ ከመንገድ ተገናኘን። ፀሐያማው ቀዬ ጠይም ደመና ለበሰ። ወዲያው ማካፋት ጀመረ። የተረገመ ቀን አልኩ። እንደሐሳቤ ሳይሆን ሲቀር እንዲህ የምለው መርገምት አለ። ጥሩ ለአለበሰ፣ ሐሳባዊ ለሆነ ሰው ፀሐይ ሆነ ደመና ምን ሊበጀው? ከካፊያው ሽሽት ከመሥሪያ ቤታችን አቅራቢያ ወደሚገኝ ገብቼበት ወደማላውቅ ካፌ ሰተት አልኩ። ዝናቡን ከራሴ ላይ ላራግፍ አንገቴን እየወዘወዝኩ እና ትከሻዬን እያንዘፈዘፍኩ ወደሆነ ባዶ ወንበር ተምዘገዘኩ። ተደላድዬ ሳልቀመጥ እንዲሁም ሐሳቤን ፈር ሳላሲዝ አንዲት ጸጉሯን ቀለም ያጠጣች፣ ደረቷ ላይ የእሾህ አክሊል ያለበትን የኢየሱስን ምስል የአተመች ሴት ልትታዘዘኝ ፊቴ ተዘባና ቆመች። ማንም ከዚህ በፊት እንዲያ ባለ ዝብናኔ አስተናግዶኝ አያውቅም። በዝብናኔዋ አልተቀየምኳትም ይልቅስ አዲስ ሐሳብ አጋባችብኝ እንጂ። ‹ወተት አልኩ› ብዙ ሳላለፋት። ካፌ ገብቼ ከወተት ውጪ የምጠጣው ነገር የለም። አንዳንድ ወዳጆቼ ሲቀልዱብኝ የእናት ጡት ስላልጠገበ ያንን እየተካ ነው ይሉኛል። እኔ ምን ገዶኝ..አንድ ብርጭቆ ወተት ለመጨረስ በሚሳቀቁ ቄንጠኛ ወዳጆቼ ፊት ሁለት..ሦስቱን ደርግሜ እመለሳለሁ። ከእንስሳ የላም አፍቃሪ ነኝ። ከሰው ደግሞ የራሴና የኢየሱስ። ያቺን የመሥሪያ ቤታችን ቆንጆ ዘናጭ ሴት ሦስተኛ ላደርጋት ከራሴ ጋር ምክክር ላይ ነኝ።

ከቡሀቃ መለስ ባለ አንዳች በሚያክል ጥንታዊ ብርጭቆ ትኩስ ወተት መጣልኝ። በዛ ዘመነኛ ቤት ውስጥ ያን ብርጭቆ መኖሩ ዙሪያ ገባዬን እንድቃኝ አደረገኝ። ቤቱ ባህላዊ ቤት እንደሆነ በተቀመጥኩበት ወንበርና፣ ግድግዳው ላይ በተሰቀሉ አንዳንድ ባህላዊ ጌጦች አረጋገጥኩ። ትልቁ ብርጭቆ ውስጥ ይመጥነዋል ብዬ ያሰብኩትን ስኳር በስሌት ጨምሬ ወደአፌ አስጠጋሁት። በአንዲት ቀብራራ ሴት የመጣ ነጭ

> ማሰብ እወደለሁ። በሆነ ርእሰ ጉዳይ ላይ መወያየትና መከራከር የምዝናናበት ተፈጥሮዬ ነው። አንደንደች አለባበሴን አይተው በሩቁ የማይረባ ያደርጉኛል።

ወተት..ወደሆዴ ሲሰርግ በተለየ እርካታ ነበር። ተስገብግቤ ጠጣሁት። እንደዛሬ ወተት ጠጥቼ አላውቅም..። አጠጣጤን እየታዘበች ይሆን እንጃ ላጋሳ ቀና ባልኩበት አስተናጋጇን ዐይኗን አነጣጥራብኝ አገኘኋት። ደረቷ ግድም በእሾህ አክሊል ኢየሱስን ወደአንድ ጎን አዘንብሎ አየሁት። ካልጠፋ ቦታ የዓለምን ንጉሥ እዛ ቦታ ማኖሯ ፈጣሪ በንፍር ውሃ ሊጠብሰን እያኮበኮበ እንደሆነ እንዲሰማኝ አደረገኝ። በሴት ርቃን ላይ፣ ለዛውም በጡት ሰፈር ኢየሱስን ተሥሎ ሳየው ስምንተኛው ሺ መድረሱን አወኩ። ‹ከፍቅሯ ነው ከድፍረቷ ያን ማድረጓ?› ስል ጥያቄ መጣብኝ። ከማንም ቀድሞ ኢየሱስ ያያት ዝሙተኛዋ መቅደላዊት ፊቴ ላይ አንጃበበች።

ከቀይ ዳማ ሽሽት ከጠይምነት መለስ ያለ መሐል ላይ ያለ ስም የሌለው መልክ አላት። ከውበቷ ሁሉ ቶሎ ዐይን ውስጥ የሚገባው ጡቷና ቆፍጣናነቷ ነው። የሐበሻ ቀሚስ ለብሳ ቢሆን ፊቴ የቆመችውና የምትታየኝ እቴጌ ጣይቱ በወጣትነቷ ትሆን ነበር። ጡቶቿ ለእይታ እንዲመቹ ሆነው መልኩን በሚያሳብቅ ጥቁር ጡት ማሲያዣ ተጠፍረዋል። ደረቷን ለሁለት ገምሰው ተነፋፍተው እና አጮልቀው። ከአንዱ ልቀው ለዘላለም እንዲታወሱ በኃጢአተኛ ሴት መላ ተዘባነዋል። አማረችኝ። ከወተቱ ጋር እሷን የሚያሰኝ መስተፋቅር ሰታኝ ይሆን? አይቻት የማላውቃትን ሴት በአንድ ጊዜ መከጀሌ ስል አሰብኩ። ከሴት ውበት መድከሚያዬ ጡት ነው። ትልቅ ጡት ያላት ሴት ሰፊ ዓለሜ ናት። ሴት ጡት ከሌላት ሴት አትመስለኝም። አብሬአት ተጋድሜ እንኳን አምሮቴን ለማውጣት የማውቃቸውን ትልቅ ጡት ያላቸውን ሴቶች በሐሳቤ አምጥቼ ነው የምረካው። የዚህ ዓለም ዕድለኛዋ ሴት ትልቅ ጡት ከትልቅ መቀመጫና ከትሑት ልብ ጋር ያላት ናት የሚል ምልከታ አለኝ።

ሒሳብ ልከፍላት በዛውም በደንብ ልረዳት በምልክት ጠራኋትና መጣች። ስትራመድ ለማንም ዝቅ እንዳትይ ተብላ የአደገች ነው የምትመስለው። ቆፍጣናነቷ ተጋብቶብኝ ትሕትናዬን ነጥቆ ‹ሒሳብ ስንት ነው?› ስል ተጀነንኩባት። ለሠላሳ ብር ወተት ያን ያክል መጀነን..

‹ተከፍሏል› አለችኝ። በማውቀው ቆፍጣናነቷ።

ምን እንደአስደነገጠኝ እንጃ ተከፍሎልኝ የማያውቅ ይመስል ድንግጥ አልኩ። ማን አባቱ ነው የከፈለልኝ በሚመስል አኳኋን ፊቷ ላይ አንጃበብኩ። የጠጣሁበትን ባላገር ብርጭቆ አንሥታ፣ የአዝረከረኩትን ወተት ጠረጴዛውን አባብሳ ከፊቴ እብስ አለች። ቁፍጣኔዋ ራሷ የከፈለችልኝ እንደሆነ እንዳስብ አደረገኝ። ደግሞ አሁን የመጣ አይደለም ስገባ ጀምሮ የማውቀው ቁፍጣኔ ነው። ከዐይኔ ከመሰወሯ በፊት ‹ማነው የከፈለው? ስል ዘለግ ያለ ድምፄን ወረወርኩላት። ትታኝ ትሄዳለች ብዬ ስፈራ ጣቷን ከገባሁ ጀምሮ ወደአላየሁት ቦታ ቀስራ ወደከፈለችልኝ ሴት ጠቆመችኝ። እኔና ሐሳቤ፣ እኔና ምኞቴ..ዘላለሜ ሳይቀር እዛ ቦታ የጨው ሐውልት ሆነን የበደንን ይመስለኛል። ከአልሆነ ለምን መራመድ አቃተኝ? በዛ ቦታ ለክፍለ ዘመናት የቆምኩ ይመስለኛል። ብርሃናማዋን የመሥሪያ ቤታችንን ሴት እያስተዋልኩ። ፊቷን ለግድግዳው ሰጥታ፣ እጇን ደረቷ ላይ አጣጥፋ በሆነ ሐሳብ ተወስዳለች። የማውቀው ፈገግታዋ የለም። ግድግዳውን እያናገረች መሰለኝ። ሊስማት ከንፈሯ ሥር በደረሰው ግድግዳ ቀናሁ። ግድግዳውን ባደረገኝ አልኩ።

አመሰግናለሁ ሳልላት ወጣሁ..

የያዝኩትን መጽሐፍ ረስቼ ኖሮ በነጋታው ቢሮ አምጥታ ስትሰጠኝ ከፈጣሪ ስጦታ የተበረከተልኝ ነበር የመሰለኝ።




# በፈተና የአልተበገሩ

## ወርቃማ እግሮች!

# በፈተና የአልተበገሩ
# ወርቃማ እግሮች!

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተወዳደሩባቸው ዓለም አቀፍ መድረኮች ታሪክ ሲሠሩ ኖረዋል፣ ዛሬም እየሠሩ ይገኛሉ። የቀደመን ታሪክ የሚቀይር ትልቅ ታሪክ በወርቅ ቀለም የሚጽፉም ጥቂት አይደሉም። የዘመናችን አዲሲቷ አንጸባራቂ ኮከብ አትሌት ትዕግሥት አሰፋ ከእነዚህ አንዷ ነች። ከጀግናው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ጀምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በወንዶች ማራቶን የዓለምን ክብረወሰን ደጋግመው አንሥተዋል። በሴቶች ግን ይህን ታሪክ መሥራት የቻለች አትሌት ከወር በፊት ፈልጎ ማግኘት አይቻልም ነበር። ይህ ታሪክ ከወር በፊት በበርሊን ማራቶን በአዲስ ታሪክ ተተክቷል። ትዕግሥት አሰፋ ፈታኙን ርቀት ለማመን በሚከብድ ብቃት በ2:11:53 ሰዓት አጠናቃ አዲሲቷ የማራቶን ንግሥት በመሆን ዘውዱን ደፍታለች። የሠራችው አዲስ ታሪክ አሁንም ድረስ የስፖርቱን ባለሙያዎችና የዓለም መገናኛ ብዙኃን እያነጋገረ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ይኽንን ታሪክ የሠራችበት መንገድና የተጓዘችበት ረጅም የሕይወት ውጣ ውረድ ለበርካቶች የጽናት ተምሳሌት፣ የአልሸነፍ ባይነት ጥግ ሆኖ ዓለም ተደንቆበታል።

## የትናንቷ ትዕግሥት

ሙሉ ስሟ ትዕግሥት አሰፋ ተሰማ ይባላል። የተወለደችው እኤአ በ1994 መጋቢት ወር ሱሉልታ ነው። ከአምስት ወንድምና እኅቶቿ ለቤተሰቧ ታናሽ ልጅ ናት። ሩጫን የጀመረችው ገና ዕድሜዋ ሳይጠና አፈር ፈጭታ በአደገችባት ሆለታ ነው። ረጅሙ የአትሌቲክስ መንገድ የጀመረውም በአራዳ ምሥራቅ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ውድድር ላይ ነው። ‹‹በስፖርት የትምህርት ክፍለ ጊዜ ስሮጥ የተመለከተኝ መምህር ነው አትሌቲክስ እንድጀምር የመከረኝ›› ትላለች ወደ ስፖርቱ የገባችበትን አጋጣሚ ስታስታውስ። የመምህሯን ምክር የተቀበለችው አዳጊ በክለብ ታቅፋ የአትሌቲክስ ጉዞዋን ስትጀምር ጊዜ አልፈጀባትም። ሩጫ ተፈጥሮ የአደለቻት መክሊቷ መሆኑን መረዳት የጀመረችውም በጊዜ ነበር። ‹‹ልጅ እያለሁ የትም ቦታ ስሄድ በሩጫ ነው፣ ሱቅ ዕቃ ለመግዛት ስላክ እንኳን በሩጫ ነው፣ በእርምጃ መጓዝ አልወድም። በአገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ መሮጥ ይቀናኛል›› ትላለች የያኔዋ አዳጊ ወጣት የአሁኗ የማራቶን ንግሥት። በሆለታ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ100 እና በ200 ሜትር የተጀመረው የትዕግሥት የአትሌቲክስ ሕይወት ጎለበተ። በአገር አቀፍ ውድድሮች መሳተፍም ቀጣዩ ርምጃዋ ሆነ።

በ2001 ዓ.ም. በተካኼደው የኢትዮጵያ ሻምፒዮና በ200፣ በ400 እና በ400 ሜትር ዱላ ቅብብል ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈችው ትዕግሥት ጅማሬዋ በወርቅ የደመቀ ነበር። በዚህ ውጤቷ የግላቸው ለማድረግ የቋመጡ ክለቦች ጥቂት አልነበሩም። እሷ ግን አሻፈረኝ ብላ ወደ ሆለታ መመለስን መረጠች። በ2003 ዓ.ም. ዳግም በኢትዮጵያ ሻምፒዮናም በአጭር ርቀት መድመቋን ቀጠለች። አሁን ግን የኦሮሚያ ፖሊስ አትሌትክስ ክለብ የአቀረበላትን ጥያቄ መግፋት አልፈለገችም፣ ክለቡን መቀላቀሏ እውን ሆነ።

## የዓለም አቀፍ ውድድሮች ጅማሬ

ወጣቷ የአጭር ርቀት ተስፈኛ አትሌት ከክለቧ ጋር በሒደት ብቃቷን እያሳደገች እኤአ 2012 ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ አገሯን ወክላ የምትሳተፍበት ዕድል አገኘች። ይህም በሱዳን የተካኼደው የምሥራቅ አፍሪካ ሻምፒዮና ሲሆን በ400 ሜትር ሁለተኛ ሆና በማጠናቀቅ ነበር የተቋጨው። ትዕግሥት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በማይደፍሩት በአጭር ርቀት

> እኤአ በ2016 የፖርትላንድ ኦሪገን የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ በ8 መቶ ሜትር አገሯን ወክላ ተወዳድራለች። ይሁን እንጂ ከመጀመሪያው ዙር የማጣሪያ ውድድር ማለፍ አልቻለችም። በተመሳሳይ ዓመት በሪዮ ኦሊምፒክ በርቀቱ ኢትዮጵያን ወክላ ለመወዳደር ብትበቃም ከመጀመሪያው ዙር ማጣሪያ ማለፍ አልቻለችም።

ሱዳን ላይ የአጠለቀችው የብር ሜዳሊያ በዚያው ዓመት ወደ አፍሪካ ሻምፒዮና መድረክ አሸጋግሯታል። በቤኒን ላይ በተካኼደው ሻምፒዮና በ400 እና በ4 በ400 ሜትር ምርጥ ተፎካካሪ መሆኗን አስመሰከረች። ይህም አገሯን ደጋግማ የመወከል ዕድሏ እያደገ እኤአ በ2013 በሞርሺየስ የአፍሪካ ወጣቶች ሻምፒዮና በ800 እና በ 4 በ400 ሜትር 2ኛና 3ኛ ሆና ልታጠናቅቅ አስቻላት። በማራቶን ታላቅ ስኬት ከአስመዘገበችበት በርሊን ከተማ ጋር የተዋወቀችውም ከዘጠኝ ዓመት በፊት የአጭር ርቀት ራጭ እያለች ነበር። ይህም በአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና 4ኛ ሆና በአጠናቀቀችበት ተመሳሳይ ወር በርሊን ላይ በ8 መቶ ሜትር የአሸነፈችበት አጋጣሚ ነው።

እኤአ በ2016 የፖርትላንድ ኦሪገን የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ በ8 መቶ ሜትር አገሯን ወክላ ተወዳድራለች። ይሁን እንጂ ከመጀመሪያው ዙር የማጣሪያ ውድድር ማለፍ አልቻለችም። በተመሳሳይ ዓመት በሪዮ ኦሊምፒክ በርቀቱ ኢትዮጵያን ወክላ ለመወዳደር ብትበቃም ከመጀመሪያው ዙር ማጣሪያ ማለፍ አልቻለችም። ይሁን እንጂ በማጣሪያው የውድድር ዓመቱን የራሷን ፈጣን ሰዓት በ2:00:21 አስመዝግባለች። እኤአ እስከ 2016ቱ ሪዮ ኦሊምፒክ ድረስም ኢትዮጵያን ወክላ በተሳተፈችባቸው ውድድሮች የጎላ ባይሆንም ውጤታማ ነበረች።

## ከባዱ ፈተና

ትዕግሥት ከሪዮ ኦሊምፒክ በኋላ በትልልቅ ውድድሮች አልታየችም። የአሁኗ የማራቶን ንግሥት ከባድ ፈተናም ከዚህ ይጀምራል። እኤአ ከ2014 ጀምሮ በገጠማት የእግር ሕመም በተለይም የተረከዝ ጅማት ሕመም ምክንያት እስከ ሪዮ ኦሊምፒክ ድረስ ከጉዳት ጋር በመታገል ነበር ስትወዳደር የቆየችው። ትዕግሥት የገጠማት ሕመም እየጠነከረ በመምጣቱም እኤአ 2017 ሙሉ በሙሉ ከውድድር ለመራቅ አስገድዷታል። በ2018 መጨረሻ ወር ግን ከሕመሟ ጋር እየታገለች በቅጡ እንኳን ሳታገግም አንድ ውድድር ብቻ በ10 ኪሎ ሜትር ሮጣ ሁለተኛ ሆና ነበር የአጠናቀቀችው።

እኤአ በ2019ም የእግሯን ሕመም እያስታገሠች ከመወዳደር ወደኋላ አላለችም። ሦስት ውድድር አድርጋ በዓመቱ መጨረሻ በቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ሕመሙ እየተሰማት ርቀቱን 68:24 በሆነ ሰዓት ሮጣ እንደጨረሰች ባሰባትና በሸክም ወጣች። እዚያው ስፔን ወደ






ሕክምና በተወሰደችበት ወቅት ነበር ሐኪሞች በአትሌቲክስ ሕይወቷ ላይ ተስፋን እንድትቆርጥ የሚያደርጋትን ሐሳብ ያረዷት። በወቅቱ ሐኪሞች ‹‹ከአሁን በኋላ የትራክ (መም) ሩጫ በስፓይክ ጫማ መሮጥ አትችይም›› ሲሉ ለዓመታት በተጋችበት የአትሌቲክስ ጉዞዋ ብሩህ ተስፋ ላይ ውሃ የቸለሱት። ትዕግሥት ተስፋ ሳትቆርጥ በሌሎች የአውሮፓ አገራት በተለይም በጣልያን በአደረገችው ሕክምና ተመሳሳይ ምክር ነበር የተሰጣት። ይባስ ብለው የተረከዝ ጅማቷ በመበጠሱ ቀዶ ሕክምና ማድረግ ስለማትችል ሩጫን እርግፍ አድርጋ ትታ በሌላ የሥራ ዘርፍ እንድትሰማራ ሐኪሞች ደግመው ነግረዋታል። በሰላም ለውድድር ከቤት የወጣችው አትሌትም በሁለት ክራንች ተደግፋ ወደ ሀገሯ ለመመለስ ተገደደች። በዚህ ሁኔታ ጥቂት የማይባሉ ወራት ነጎዱ። ትዕግሥት እነዚህን የፈተና ወራት እንደ ስሟ ታግሣ አሳለፈች። ተስፋ ግን አልቆረጠችም ‹‹ዳግም እችላለሁ እሮጣለሁ›› በማለት በእምነት በጽናት ቆመች። ‹‹ሐኪሞች ያሉኝን ደግሜ ለአእምሮዬ አልነገረውም፣ ሩጫ ፈጣሪ የሰጠኝ ስጦታ ነው አልተውም›› በማለት መንፈሷን አጠንክራ ታገለች። ለ4 ወር በሁለት ክራች ተደግፋ ለመንቀሳቀስ ከተገደደች በኋላ ቀስ በቀስ ለውጥ እያሳየች መጣች። ለሁለት ወር በአንድ ክራች መጓዝ ጀመረች። እሱንም አሽቀንጥራ ጥላ ሙሉ በሙሉ መራመድ ጀመረች። በክራንች እየሄደች ግን ዋናና፣ ጂምናዚየም እየሠራች በጠንካራ ሥነ ልቦና መታገሏን አላቆመችም ነበር። ከባዱ ፈተና የአትሌቲክስ ሕይወቷን ተስፋ እንዲያጨልምባት አልፈቀደችም። ቀላል ልምምዶችን እየሠራች ቀስ በቀስ እስክትጠነክር መታገሥ ነበረባት። በዚህ ሁኔታ እኤአ 2020 የውድድር ዓመት ሙሉ በሙሉ ሕመምን ለማሸነፍ በሚደረግ ትግል አለፈ። እኤአ በ2021 ከግማሽ ዓመት በኋላ ልምምድ ተጀመረ።

## የትዕግሥት ትንሣኤ

ታጋሿ አትሌት ለሰባት ዓመታት ከሕመሟ ጋር ታግላ የተስፋ ጮራ መመልከት ጀምረች። ይህ ወቅት ለእሷ እንደ ትንሣኤ ነው። ለአንድ አትሌት ያን ያህል ዓመት ከውድድር ርቆ መቆየት ቀላል አልነበረም። ሕመሙ አካላዊ ብቻ ሳይሆን ሥነ ልቦናዊም ጭምር ነው። ያም ሆኖ ብርቱዋ አትሌት ፈታኙን ጊዜ ድል አድርጋ

እኤአ ከ2021 ኢጋማሽ በኋላ ወደ ውድድር ተመልሳለች። ትዕግሥት ወደ ውድድር ስትመለስ ፊቷን ሩጫን ከጀመረችበት አጭርና መካከለኛ ርቀት ወደ ጎዳና ላይ ውድድሮች አዞራ ነው።

ከረጅሙ የጉዳት ዘመን ተመልሳ በአደረገቻቸው ሦስት የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድሮችም ሦስቱንም በማሸነፍ ይበልጥ በራስ መተማመኗን አሳደገች። የመጀመሪያ ዓለም አቀፍ ውድድሯ ዱባይ ላይ ሲሆን 34:35 ሰዓት ነበር የሮጠችው። ሁለተኛ ውድድሯን ጀርመን ላይ አድርጋም 31:45 በመሮጥ ሦስት ደቂቃ ገደማ አሻሽላለች። ከዚህ በኋላ ትዕግሥትን የሚያቆማት አልተገኘም። በሁለት የግማሽ ማራቶን ውድድሮች ድል ቀናት።

ዛሬ ላይ በማራቶን ገናና ስም የአተረፈችበትን የማራቶን ውድድር ግን መሮጥ የጀመረችው ከሁለት ዓመት በፊት ነበር። በሳኡዲ ዐረቢያ መዲና ሪያድ ማራቶን ለመጀመሪያ ጊዜ የ42 ኪሎ ሜትር ውድድሯን የአደረገችው ትዕግሥት በ2:34:01 ሰዓት ሰባተኛ ደረጃን ይዛ ነበር የአጠናቀቀችው።

ከመጀመሪያው የማራቶን ውድድር ውጤቷ በኋላ ድምፅዋን አጥፍታ ስትዘጋጅ የቆየችው ይህች ድንቅ አትሌት እኤአ በ2022 በርሊን ማራቶን ሦስተኛውን የዓለም ፈጣን ሰዓት አስመዝግባ ታሸንፋለች ብሎ የጠበቀ አልነበረም። በተለይም የበርሊን ማራቶን በርቀቱ ገና ሁለተኛ ውድድሯ እንደመሆኑ ከአላት ትንሽ ልምድና በመጀመሪያ ውድድሯ ከአስመዘገበችው ደካማ ሰዓት አኳያ እንኳን ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ ለጠንካራ ተፎካካሪነትም ያጫት አልነበረም።

በዓለም ታላላቅ ከሚባሉ የማራቶን ውድድሮች አንዱና ዋነኛው በሆነው የበርሊን ማራቶን በወንዶች በርካታ የዓለም ክብረ ወሰኖች ቢሰበሩም በሴቶች ረገድ ያለው ታሪክ ተቃራኒ ነው። ማንም ያልጠበቃት ኢትዮጵያዊት አትሌት ግን 2:15:37 ሰዓት በማጠናቀቅ በአንድ ውድድር ሦስት የተለያዩ ክብረ ወሰኖችን መጨበጥ ቻለች። አንዱ የውድድሩን ክብረ ወሰን የሆነውን ሰዓት ከሁለት ደቂቃ በላይ የአሻሻለችበት ሲሆን፣ ሌላኛው የኢትዮጵያ የማራቶን ክብረ ወሰን የጨበጠችበት ነው። ቀሪው ደግሞ በታሪክ ሦስተኛውን ፈጣን ሰዓት የአስመዘገበችበት ነው።

ትዕግሥት በዚህ ውድድር ቀድሞ በማራቶን ከአስመዘገበችው ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ያላነሰ መሻሻል ማሳየቷ ለማመን የሚከብድ ነበር። ይህም በማራቶን ታሪክ ከኬንያዊቷ ብሪጊድ ኮስጌ እና ከእንግሊዛዊቷ ፓውላ ራድክሊፍ ቀጥላ ስሟ በክብረ ወሰን ማኀደር እንዲሰፍር አድርጓታል። በኢትዮጵያ የሴቶች ማራቶን ታሪክ ከአንድ ደቂቃ በላይ ክብረ ወሰኑን የአሻሻለች የመጀመሪያዋ አትሌትም ሆናለች። ይህ ከዓመታት በፊት «ከዚህ በኋላ አትሌቲክስ ይቅርብሽ» ተብላ ለነበረች አትሌት ትልቅ ስኬት ቢሆንም የትዕግሥት የሩጫው ዓለም ታምራቶች በዚህ አላበቃም።

> ስፔን ወደ ሕክምና በተወሰደችበት ወቅት ነበር ሐኪሞች በአትሌቲክስ ሕይወቷ ላይ ተስፋን እንድትቆርጥ የሚያደርጋትን ሐሳብ የአረዷት። በወቅቱ ሐኪሞች «ከአሁን በኋላ የትራክ (መም)ሩጫ በስፓይክ ጫማ መሮጥ አትችይም» ሲሉ ለዓመታት በተጋችበት የአትሌቲክስ ጉዞዋ ብሩህ ተስፋ ላይ ውሃ የቸለሱት።

## የስኬት ማማ

ትዕግሥት እኤአ በ2022ቱ የበርሊን ማራቶን 2:15:37 በመግባት የቦታውን ክብረ ወሰን ሰብራ ሶስተኛውን የርቀቱ ፈጣን ሰአት ስታዝመዘግብ ዳግም ያንን ብቃቷን ትደግማለች ብሎ የጠረጠረ አልነበረም። ብርቱዋ አትሌት በዘንድሮው የበርሊን ማራቶን ተመልሳ የሠራችው ታሪክ ግን ለራሷም ቢሆን አስገርሚታል። «እውነት ለመናገር በተወሰነ መልኩ ክብረ ወሰኑን የማሻሻል ፍላጎት ነበረኝ፤ ከአሠልጣኜ ጋርም ክብረ ወሰኑን ለመስበር ዕቅደን ነው የተዘጋጀነው። ጥሩ አቋም ላይ ብገኝም በዚህ ደረጃ አሻሽላለሁ ብዬ ግን አልጠበኩም፤ ዕቅዱ 2:12:13 ሰዓት ለመሮጥ ነበር» ትላለች።




ተደጋግሞ የማይሰበረውን የሴቶች ማራቶን ክብረወሰን 2:11:53 በማጠናቀቅ አንክታዋለች። ቀደም ሲል የርቀቱ ክብረ ወሰን እኤአ በ2019 የቺካጎ ማራቶን በኬንያዊቷ አትሌት ብሪጊድ ኮስጌ 2:14:04 የተያዘ ነው። ትዕግሥት ይህን ክብረ ወሰን ብዙዎች ለማመን በከበዳቸው ድንቅ ብቃት ከ2:11 ደቂቃ በላይ አሻሽላዋለች። በማራቶን ታሪክ በዚህ ያህል ልዩነት ክብረ ወሰን ማሻሻል የማይታሰብ ነው። በሴቶች ማራቶን በሰፊ ልዩነት ክብረ ወሰን የተሻሻለው ከአርባ ዓመታት በፊት ነው። ይህም እኤአ በ1988 አሜሪካዊቷ አትሌት ጆአን ቤኖይት 2:25:29 የነበረውን ክብረወሰን ወደ 2:22:43 ያወረደችበት ነው። ትዕግሥት ከእነዚህ ዓመታት በኋላ ማንም ሳያስበው የተከሠተች ኮከብ ነች። በእነዚህ ዓመታት በርካታ የምሥራቅ አፍሪካ ቁንጮ አትሌቶች የብቃታቸው ጥግ ላይ ደርሰው ይህን ማሳካት አልቻሉም። እሷ ግን በርቀቱ ያውም ገና በሦስተኛ ውድድሯ አሳክታዋለች። እኤአ በ1981 መጨረሻ ላይ በአሠልጣኝ ንጉሤ ሮባና አትሌት አዲስ ገዛኸኝ የተጀመረው የኢትዮጵያ የሴቶች ማራቶን ታሪክ ርቀቱን ለማጠናቀቅ የፈጀው ጊዜ 3:00 ነበረ። አሁን ላይ ትዕግሥት ምናልባትም ለበርካታ ዓመታት እንዳይደፈር አድርጋ ሰቅላዋለች። እሷ ግን በዚህ ብቻ የምትቆም አይደለችም፤ ከዚህም በላይ የብቃቷን ጥግ ለዓለም የማሳየት ህልም አላት። ይህንንም በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ስታልፍ ተስፋ ሳይቆርጥ ከጎኗ ከነበረው አሠልጣኟ ገመዶ ደደፎ ጋር እንደምታሳካው

**ትዕግሥት በ2022ቱ**
የበርሊን ማራቶን
2:15:37 በመግባት
የቦታውን ክብረወሰን
ሰብራ ሦስተኛውን የርቀቱ
ፈጣን ሰዓት ስታዝመዘግብ
ዳግም ያንን ብቃቷን
ትደግማለች ብሎ የጠረጠረ
አልነበረም። ብርቱዋ
አትሌት በዘንድሮው የበርሊን
ማራቶን ተመልሳ የሠራችው
ታሪክ ግን ለራሷም ቢሆን
አስገርሟታል።

አትጠራጠርም። የራሷን የዓለም ክብረ ወሰን ‹‹በእርግጠኝኛት አሻሽለዋለሁ›› ትላለች። 42 ኪሎ ሜትሩን ከ2:10 በታች ማጠናቀቅ ይቻላል በማለትም በቀጣይ ዓመታት የማይደፈረውን ለመድፈር ዕቅድ አላት።

## የፓሪስ ኦሊምፒክ ተስፋ

ትዕግሥት የአስመዘገበችው የዓለም ክብረ ወሰን ሌላ የጤና እክል ከአልገጠማት ከዓመት በኋላ በሚካሄደው የ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን እንድትወክል የሚያስችላት ነው። ‹‹ይህ ስኬት በኦሊምፒክ ቡድኑ እንደሚያካትተኝ አምናለሁ›› ስትልም ከፊት ስለሚጠብቃት ታላቁ የውድድር መድረክ ትናገራለች። ከዚያም በላይ ግን የእሷ የዓለም ክብረ ወሰን በርካታ ሴት ኢትዮጵያውያን ወጣት አትሌቶችን ተነሣሽነት እንደሚጨምር ታምናለች። ‹‹በርሊን ላይ የአሳየሁት ብቃት ለበርካታ ወጣት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ተነሣሽነት ይፈጥራል ብዬ አስባለሁ። ይህ ደግሞ አገራችን በቀጣይ ለሚኖራት የኦሊምፒክ ተሳትፎ ትልቅ ዐቅም ይሆናል›› ብላ እንድታምንም አድርጓታል።

ብርቱዋ አትሌት ከወደቀችበት ተነሥታ በአስመዘገበቻቸው ስኬቶች ለብዙዎች የተስፋ ስንቅ ሆናለች። በሕይወት ጉዞ የቱንም ያህል የከበደ ፈተና ቢገጥም ተስፋ መቁረጥ እንደማያስፈልግ ሁነኛ ምሳሌ ሆናለች። ለዚህም በክለቧ የምክትል ኢንስፔክተርነት መዓርግ ተሰጥቷታል።